# ሥነ-ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ISBN ቁጥር -

ዋጋ ብር -

ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

7ኛ ክፍል

ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

7ኛ ክፍል




በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

## የጥንቃቄ መልዕክት

**ተማሪዎች!**

**ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!**

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፉ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

ማሳሰቢያ፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

# ሥነ-ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ማስተዋል ጌታ ማስረሻ

ዮሐንስ ታደሰ በትሬ

**አርታኢዎች**

አሰፋ ሰማው ፈንታዬ

ጃምቡየ ሰርጡ

**ቡድን መሪ**

አሰፋ ሰማው ፈንታዬ

**ዲዛይነር**

አትርሳው ጥግይሁን ወረቀት



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# ማውጫ


መግቢያ ..................................................................................................... v

ምዕራፍ 1

ጥበባዊ ግንዛቤ

1.1. መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያንና የዲዛይን መርሆች ሚናና ተግባር ..................................................................................................... 2

1.1.1 መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን ሚናና ተግባር ...................... 3

1.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች እና ውዝዋዜዎች ...................................... 14

1.2.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች ................................................... 14

1.2.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ................................................ 20

1.3 የቴያትር ጥበባት ......................................................................... 23

1.3.1 የቴያትር አለባዊያን ................................................................ 25

1.3.2 የቴያትር አይነቶች.................................................................. 25

1.4 የፊልም ጥበብ.............................................................................. 27

1.4.1 የፊልም ጥበብ አለባዊያን ........................................................ 28

1.4.2 የፊልም ጥበብ አይነቶች........................................................... 29

ምዕራፍ 2

የፈጠራ ችሎታን መግለፅ

2.1. ቀለም ቅብ እና ህትመት................................................................ 34

2.1.1 የቀለም ቅብ ........................................................................... 34

2.1.2 ለቀለም ቅብ ተግባር የምንጠቀምባቸው የቀለም አይነቶች ምንነት.... 35

2.1.2 ህትመት................................................................................. 43

2.1.3 ኪነ ቅርፅ ............................................................................... 48

2.2 የሙዚቃ ንባብ.............................................................................. 53

2.3 ባህላዊ ውዝዋዜን መተግበር .......................................................... 67

2.4 የቴያትር እና የፊልም ጥበባት ሀሳቦችን ማፍለቅ ...................................... 68

ምዕራፍ 3

ታሪክ እና ባህል

3.1 የአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ ......................................................... 75

3.1.1 በአማራ ክልል የሚገኙ የሙዚቃ ባለሞያዎች የህይወት ታሪክ እና ስራዎቻቸው ...................................................................................... 78

3.2 የአማራ ክልል ውዝዋዜ ባለሙያዎች ታሪክ ........................................ 84
3.3 የኢትዮጵያ ታላላቅ የሙዚቃ ባለሙያዎች እና ስራዎቻቸው.................... 87
3.3.1 የቅዱስ ያሬድ የሕይወት ታሪክ ................................................ 87
3.3.2 የቅዱስ ያሬድ የዜማ አይነቶች ............................................. 89
3.3.2 የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶችና ትርጉማቸው............................... 90
3.4 በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ አጀማመር.............................................. 92
3.5 የኢትዮጵያ ታላላቅ የእይታዊ ጥበብ ባለሙያዎች ................................. 98
3.6 በኢትዮጵያ የሚገኙ ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶች ................................ 110
3.6.1 ሀገር በቀል የሆነ ይዘት ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎች .................... 114
3.6.2 ሀገር በቀል የሆነ ይዘት ያላቸው ጥንታዊ መዛግብት......................... 116
3.6.3 ሀገር በቀል በሆነው ጥንታዊ ጥበብ እና እውቀት የተሰሩ የሸክላ ስራዎች.... ........................................................................................ 118
3.7 ሀገር በቀል እውቀትን በቴያትር እና በፊልም መግለፅ ............................ 122

## ምዕራፍ 4

## ሥነ ውበታዊ ጠቀሜታ

4.1 የእይታዊ ጥበባት ጠቀሜታ........................................................... 127
4.2 የክውን ጥበባት ጥቅሞች ............................................................. 131
4.2.1 ክውን ጥበባት ለማህበራዊ ህይወት ያላቸው ጠቀሜታ...................... 131
4.2.2 በህፃናት ማህበራዊ እድገት ላይ ያለው ጠቀሜታ............................. 133
4.3 ሀገር በቀል የስነ ጥበባት ስራዎች ................................................... 135
4.3.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ........................ 143

## ምዕራፍ 5

## ሥነ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና

5.1 መኖሪያ ቤትን፣ አካባቢን በሸክላ እና በሴራሚክ ስራዎች ማስዋብ ........... 149
5.2 እይታዊ ጥበብ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለው ትስስር እና ጠቀሜታ........... 152
5.3 የሙዚቃ ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና................ 156
5.3.1 ሙዚቃ ትምህርት ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር የሚያደርገው እገዛ... ........................................................................................ 160
5.4 ትኩረት የሚሹ እና ወቅታዊ ጉዳዮች .............................................. 162

# መግቢያ

## ሥርዓተ ትምህርቱን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተካሂደዋል:: ከእነዚህም አንዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተካሄደው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ዋናው ነው:: ይህ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ርእሶች ዙሪያ የተካሄዱት ጥናትና ምርምሮች ሥርዓተ ትምህርቱ በይዘት የታጨቀ፣ በትምህርት አይነቶች ብዛት የተወጠረ፣ በአብዛኛው ይዘት ማስታዎስን ትኩረት ያደረገ፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ህይወትና ኑሮ፣ ምርታማነት እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀት ጋር ያልተቆራኘ፣ ተማሪዎች ተገቢውን ግብረገባዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበሱ ያላደረገ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እና ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ከማስተናግድ አኳያ ክፍተት ያለበት መሆኑ ተመላክቷል:: በተጨማሪም ስርዓተ ትምህርቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማለትም ለመማር መማርን፣ በጥልቀት ማሰብና ችግር ፈችነትን፣ የፈጠራ አስተሳሰብና አዳዲስ ግኝቶች ማፍለቅን፣ ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ መሪነትና ውሳኔ ሰጭነትን፣ የቴክኖሎጂ እውቀትን እና የባህል ማንነትና አለማቀፋዊ ዜግነትን ማስጨበጥ የማይችል መሆኑን በማመላከት የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻል እና ለውጥ እንዲካሄድ የሚያመላክቱ ምክረ-ሃሳቦችን ሰንዝረዋል::

ይህንን መነሻ በማድረግም ሰፊ የውይይት እና የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ህብረተሰቡ እንዲወያይ በማድረገ የለውጥ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ወደ ትግበራ ተገብቷል:: ከእነዚህ የለውጥ መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ዝግጅት ተድርጓል::

በዚህም መሠረት አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚያግዙ ሰነዶች ማለትም የተማሪው የባህሪ ገጽታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፣ የይዘት ፍሰት፣ ተፈላጊ የመማር ብቃት እና መርሃ-ትምህርቶች እንደ ሀገር ተዘጋጅተዋል:: በእነዚህ ሰነዶች መነሻነትም በክልላችን የመጀመሪያ ደረጃ(ከ1ኛ-6ኛ) እና የመካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍሎች የየትምህርት አይነቶች የተማሪዎች መማሪያ እና የመምህራን ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል::

## የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል:: ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል:: በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል::

## ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ:: በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል:: መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው:: በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል::

## ውድ ወላጆች/ አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው:: ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል:: ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል:: በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ::

## የቃላት ፍች

1. **ስኬል**፦ የድምፅ ድርድር ስርዓት (ቅኝት)
2. **አሌግሮ**፦ ፈጣን የምት አካሄድ
3. **ታይ**፦ አንዱን ኖታ ከሌላኛው ኖታ ጋር አዋህዶ
5. **ኢትኖሚዚኮሎጂ**፦ ሙዚቃን ከሰው ልጅ አኗኗር ጋር ያለውን ቁርኝት የሚያጠና መስክ
6. **ዲያቶኒክ**፦ አውሮፓዊያን የሚጠቀሙበት ባለ ሰባት ድምፅ ድርድር ቅኝት
7. **ፔንታቶኒክ**፦ ባለ አምስት ድምጽ ድርድር ቅኝት
8. **ማርሽ**፦ የወታደራዊ የሰልፍ የሙዚቃ ስልት
9. **ቀማሪ**፦ የሙዚቃ ደራሲ /ጸሀፊ፣ አዘጋጅ/
10. **አማተር**፦ ጀማሪ የስነ ጥበባት ባለሙያ /ዎች/
11. **ካርቪንግ**፤- መቁረጥ፣ መጥረብ፣ መፈልፈል፣ መቦርቦር
12. **ሞዴሊንግ**፦ መገንባት፣ መጨመር
13. **አሰምብሊንግ**፦ ማገጣጠም፣ ማያያዝ
14. **ካስቲንግ**፦ ማስመሰል፣ ከዋናው ቅርፅ ላይ ሞልድ (ነጌቲቭ) ይዘት በማውጣት መስራት
15. **ቴክስቸር**፦ የነገሮች የልስላሴ እና የሸካራ ሁኔታ
16. **ፓሌት**፦ ቀለም ለማዋሀድ የሚያገለግል
17. **ኢዝል**፦ ለቀለም ቅብ ተግባር ካንቫሱን ለመያዝ የሚያለግል፣ ቆመን ወይም ተቀምጠን ለመስራት የሚያስችል
18. **ናይፍ**፦ በቀለም ቅብ ተግባር ቀለሙን በወፍራሙ በካንቫሱ ላይ ለመቀባት እና ቅቡ የተለያየ የቴክስቸር ይዘት እንዲኖረው ያደርጋል
19. **ጋለሪ ወክ**፦ የተለያዩ የእይታዊ ጥበባት ውጤቶች በሚገኙበት ስፍራ ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ ማየት፣ ማውራት፣ መነጋር
20. **ጋርደኒንግ**፦ የአትክልት ስፍራዎችን እና የተለያዩ የመሬት ገፅታዎችን ሳቢ.ናማራኪ

# ምዕራፍ 1



# ጥበባዊ ግንዛቤ

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ስነ-ጥበባዊ ክዋኔዎችን ትገነዘባላችሁ።
- የዲዛይን አለባዊያንና መርሆችን ሚና እና ተግባር ታውቃላችሁ።
- የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜዎችንና ሙዚቃዎችን ባህሪያት ትለያላችሁ።
- የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜዎች እና ሙዚቃዎችን ታደንቃላችሁ።
- የቴያትር እና የፊልም ጥበባት ምንነትን ትገነዘባላችሁ።

## መግቢያ

የስነ ጥበባት ትምህርት በውስጡ ክውንና እይታዊ ጥበባትን አካቶ የያዘ የትምህርት አይነት ነው። ሙዚቃ፣ ዳንስ /ውዝዋዜ/ና የቴያትር ጥበባት በክውን ጥበባት ውስጥ የሚጠቃለሉ ሲሆን እንደ ቀለም ቀብ፣ ፊልም፣ ኪነ ቅርፅና ሌሎች ስነ ስዕላዊ ጥበባት ላይ የሚያተኩሩት ደግሞ በእይታ ጥበባት የሚካተቱ ናቸው።

ምዕራፍ አንድ ትኩረት የሚያደርገው የተማሪዎችን ጥበባዊ ግንዛቤ ከፍ ማድረግ ሲሆን በስነ ስዕል ጥበብ ውስጥ መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አላባዊያን ሚናና ተግባር፣ የኢትዮጵያ ሙዚቃና ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ጥበባዊ ምልከታ ተማሪዎች እንዲረዱት ማድረግ ነው። በዚህ ምዕራፍ ስር የተካተቱት ለጥበባዊ ግንዛቤ ማሳደጊያ የሚረዱ የስነ ጥበባት ይዘቶችን ተማሪዎች በአካባቢያችሁ በሚከወኑ የስነ ጥበባት ስራዎች ላይ ትኩረት እንድታደርጉ ይመከራል።

ምልከታችሁ መሆን ያለበት ተግባቦት ያላቸው ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን፣ የተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ዲዛይኖችን፣ ሙዚቃዎችንና ውዝዋዜዎችን መሆን ይገባዋል።

በዚህ ሂደት ትኩረት የሚደረግባቸው ቁም ነገሮች ደግሞ የዲዛይን አለባዊያንን ሚና፣ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያለውን ቴያትራዊ ጥበብ፣ በሙዚቃዎችና ውዝዋዜዎች ውስጥ ያሉ ፈጠራዊ ተግባራትን ከጥበብ አንፃር መመልከትና ተግባራዊ እንድታደርጓቸው ይጠበቃል።

## የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

ተማሪዎች፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ በቡድን በመወያየት ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

1. ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን የተለያዩ የስነ ጥበባት ክዋኔዎችን ዘርዝሩ።
2. በአካባቢያችሁ የተለያዩ ዲዛይኖች ላይ ምን ምን ነገሮችን ትመለከታላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ የምትመለከቷቸውን ዲዛይኖች መሰረታዊ ነገሮችን ተናገሩ።

## 1.1. መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያንና የዲዛይን መርሆች ሚናና ተግባር

ተማሪዎች፣ ከላይ በተቀመጠው ንዑስ ርዕስ በ5ኛ እና በ6ኛ ክፍል በነበራችሁ የስነ ጥበባት ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት መሰረታዊ የእይታ ጥበብ አለባዊያን እና የዲዛይን መርሆች ምን ምን እንደሚባሉ፣ እንዴት ሊገለፁ እንደሚችሉ ተምራችኋል። በመሆኑም በዚህ የክፍል ደረጃ ትምህርት ደግሞ መሰረታዊ የእይታ ጥበብ አለባዊያንና የዲዛይን መርሆች ሚናና ተግባር በሚል ትማራላችሁ። በመሆኑም የእናንተን የመረዳት አቅም ለማጎልበት እንዲሁም በትምህርቱ ላይ ያላችሁን እውቀት ለማስፋት በቅድሚያ ዲዛይን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትማራላችሁ።

**ማስታወሻ፡-**

**ዲዛይን፡-** የነገሮች መጠን፣ ቅርፅ፣ ቀለም፣ ፎርምና ቴክስቸር ውበት ባለው እና በተደራጀ መልኩ አስውቦና አቅዶ በመደጋገም የሚሰራ የጥበብ ስራ ውጤት ነው፡፡

መሰረታዊ የዲዛይን መርሆች የሚባሉት ዲዛይኖችን መስራት የሚያስችሉ ህግጋት ናቸው፡፡

በአመጋገብ ስርዓታችን የምግቡን ጣዕም ለመጨመር የምንጠቀምባቸው ቅመማቅመሞች እንደሚያስፈልጉ ሁሉ ዲዛይኖች ሲሰሩ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ መርሆችና የእይታ ጥበብ አለባዊያን ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህ የእይታ ጥበብ አለባዊያንና የዲዛይን መርሆች የዲዛይኑን ስራ የተዋጣለት ለማድረግ በትክክለኛው ቦታቸው ላይ መቀመጥ ይገባቸዋል፡፡

ዲዛይን በባህሪው ዘርፈ ብዙ የሆኑ የአሰራር ሂደቶችን በመከተል በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚተገበር ነው፡፡ በመሆኑም የዲዛይን ውጤቶች በእለት ተእለት ተግባራቶቻችን በተለያየ መንገድ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ምሳሌ የመኖሪያ ቤት ቁሳቁሶችን ከቤቱ ስፋትና ጥበት አንፃር ምቹና ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግና ደስታን መፍጠር እንዲችሉ አድርጎ ማደራጀት ይቻላል፡፡

መሰረታዊ የዲዛይን አላባዊያን የሚከተሉት ናቸው፡፡

- መስመር
- ቀለም
- ዝርግ ቅርፅ
- ለስላሳ እና ሸካራ
- ቦታ
- ፎርም ናቸው

## 1.1.1 መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን ሚናና ተግባር

መሠረታዊ የእይታ ጥበብ አለባዊያን ከሚባሉት ውስጥ መስመር፣ ቀለም ዝርግ ቅርፅ፣ ቦታ፣ ፎርምና ለስላሳና ሸካራ ይጠቀሳሉ፡፡

## መስመር

መስመር ከእይታዊ ጥበብ አለባዊያን መካከል አንዱ ሲሆን በዋናነት በተለያዩ የዲዛይን ተግባራት እና ውጤቶች ላይ ልዩ ልዩ ውበቶችን ለመፍጠር እና በሰዎች ዘንድ የዲዛይን ውጤቶቹን መረዳት ለማስቻል፣ የተለያዩ የዲዛይን ክፍሎችን ለማሳየት፣ አጠቃላይ የዲዛይኑን ገፅታ በተለያየ ይዘት እና መጠን ለመከፋፈል፣ ከአንዱ የዲዛይን ክፍል ወደ ሌላኛው ያለውን የመጠን፣ የቅርፅ ይዘት ወሰን ለማመላከት ያስችላል። በአጠቃላይ መስመር በዲዛይን ስራዎች ላይ ልዩ ልዩ እይታዊ መልዕክቶችን፣ የሸካራ እና የልስላሴ ይዘትን፣ አስፈላጊ የሆኑ ድግግሞሻዊ ዲዛይኖችን ወዘተ ለማሳየት እና ለመወከል ያስችላል።



ሥዕል 1 የመስመር ተግባር

## ቀለም

ቀለም በተለያዩ የዲዛይን ተግባራት እና ውጤቶች ላይ ልዩ ልዩ ሀሳቦችንና መልዕክቶችን በመግለፅና በማሰተላለፍ የተጠቃሚውን ፍላጎት በዲዛይን ስራዎች ላይ ማሳየት ይቻላል። ለምሳሌ፡- ሞቃት ቀለማትን በመጠቀም የምንሰራቸው የዲዛይን ውጤቶች በተመልካቹ ዘንድ ቶሎ አይን ውስጥ የመግባት እና የመመረጥ ሁኔታቸው ከፍተኛ ነው። ሲታዩም ሞቅ ያለ እና አስደሳች ስሜትን ያጭራሉ። ቀዝቃዛ ቀለማትን በመጠቀም የምንሰራቸው የዲዛይን ውጤቶች ደግሞ ለእይታ የተረጋጋ ስሜትን የመፍጠር፣ ውስጥን የማየት፣ የማዳመጥ ስሜትን እና ፍላጎትን ያመጣሉ። ስለሆነም ተመልካቹ እንደስሜቱና ፍላጎቱ እንዲመለከተው ቀለም የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው።





ሥዕል 2 የቀለም ተግባር

## ቴክስቸር


ቴክስቸር በዲዛይን ተግባር ውስጥ የተለያዩ ተግባራቶች አሉት። የቤት ውስጥ ዲዛይነር ባለሙያ በአንድ ቤት ውስጥ የሚገኙ ነፃ ቦታዎችን፣ ልዩ ልዩ ክፍሎችን ውበት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ የበለጠ ሳቢና ማራኪ የሆነ ይዘት እንዲላበሱ የፋብሪካ ውጤቶችን፣ ድንጋዮችን፣ እንጨቶችን፣ ጀሶ ወዘተ በመጨመር አሰልች የሆነውን ሰፊውን እና ጠፍጣፋውን የቤቱን ውስጣዊ እና ውጫዊ ክፍሎች ስነ ውበታዊ እሴት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስችላል።



ሥዕል 3 የቴክስቸር ተግባር

## ዝርግ ቅርፅ


ዝርግ ቅርፅ በዋናነት ቀለምን እና የቀለምን ስነ ባህርይ መሰረት በማድረግ በተለያዩ የዲዛይን ስራዎች ላይ የዲዛይን ሁኔታ ለመወሰን፣ ለመምረጥና ስነ ውበታዊ ገፅታ እንዲይዝ ለማድረግ ያስችላል። በተጨማሪም የዲዛይኑን አጠቃላይ ይዘት ከተጠቃሚው ፍላጎት እና ሀሳብ በመነሳት ተግባራዊ በማድረግ መልካም ተግባቦት እንዲኖር ያስችላል።



ሥዕል 4 የዝርግ ቅርፅ ተግባር

## ቦታ

ቦታ በዲዛይን ቅድመ ንድፍ እና ተግባራቶች ላይ የዲዛይኑን ውክል የሆኑ ቦታዎችንና ክፍሎችን አጠቃላይ የዲዛይኑን ይዘት በጥልቀት ማየትና መረዳት ያስችላል። በተጨማሪም በዲዛይን ስራዎች ላይ የእይታ ቅደም ተከተሎችን በመፍጠር አጠቃላይ የዲዛይኑ ገፅ ላይ የሰፈሩትን ነገሮች በጥልቀት መገንዘብ ያስችላል።



ሥዕል 5 የቦታ ተግባር

## ፎርም

ፎርም ከእይታዊ ጥበብ አለባዊያን መካከል አንዱ ሲሆን ተግባራዊ በምናደርጋቸው ሊቀመጡ እና ሊወከሉ የሚችሉ ገፆችን ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ ባለ ሶስት አውታር መጠን ይዘታቸውን ያሳያል። በተለያዩ የዲዛይን ቅድመ ንድፍ ስራዎች ላይ ብርሀን እና ጥላን በመጠቀም ወደ ፊት የሚሰራውን ዋና የዲዛይን አካል ስፋት፣ ጥልቀት፣ ጠቅላላ እይታውን ቀድሞ ለመተንበይ እና ለማህበረሰቡ ለማስረዳት ለማሳወቅ ያስችላል።




ሥዕል 6 የፎርም ተግባር

### 1.1.2 መሰረታዊ የዲዛይን መርሆች ተግባር እና ሚና

#### ፓተርን

ከዲዛይን መርሆች መካከል አንዱ ሲሆን በዋናነት መደበኛ በሆነ መልኩ በአንድ በተዘጋጀ ውስን ቦታ ላይ መስመሮችን፣ ሽፖችንና ቀለሞችን በመደጋገም በዲዛይን ስራችን ላይ የዲዛይኑን የእይታ ውበት የምንገልፅበት ነው።






ሥዕል 7 የፓተር አወቃቀር

## ንፅፅር


ከዲዛይን መርሆች መካከል አንዱ ሲሆን የተለያየ ባህሪ (ውክልና) ያላቸውን የዲዛይን ይዘቶች ሸካራ ለስላሳ፣ ጠቆር ያለ እና ነጣ ያለ ንፅፅር በመጠቀም በዲዛይኑ ውጤት ላይ ልዩነታቸውን በማመላከት ለተመልካቹ ደስ የሚል የእይታ ስሜት እና የእይታ ስበት የምናመላክትበት ነው።



ሥዕል 8 የንፅፅር አወቃቀር

## አፅንኦት

አጽንኦት በአንድ በተሰጠን ውስን ቦታ ላይ የምናስቀምጣቸው የዲዛይን ስራዎች መካከል አንዱን ገፅ የተለየ ትኩረት በመስጠት ወጥ የሆነ የዲዛይን ገፅታ በመጠናዊ ምደባ፣ በቀለም፣ በንፅፅር፣ በመጠን፣ በልዩነት፣ በመደጋገም ለተመልካቹ ወሳኝ የሆነውን ትኩረት የሚሻውን የእይታ ስበቱን የምናመላክትበት ነው።



ሥዕል 9 የአጽንኦት አወቃቀር

## ሚዛን

ሚዛን በአንድ በተሰጠን ውስን ቦታ ላይ የምናስቀምጣቸው የዲዛይን ስራዎችን የተመጣጠነ እይታዊ ስበት (አቅም) እንዲኖራቸው የምናደርግበት ሲሆን በተሰጠን ወስን ቦታ ላይ የሚቀመጡት ስራዎች ተመዛዛኝ በሆነ እና ባልሆነ መልኩ ሆኖ እኩል የእይታዊ ስበት ሀይል እንዲኖራቸው የምናደርግበት ነው።





ሥዕል 10 የሚዛን አወቃቀር

## ስኬል

ይህ የዲይን መርህ በአንድ በተሰጠን ውስን ቦታ ላይ የምናሰቀምጣቸውን የዲዛይን ስራዎችን በመጠን፣ በቁጥር፣ በገፅ ወ.ዘ.ተ ያላቸውን ልዩነት በማመጣጠን ወደ አንድ እይታዊ ስብስብ እንዲመጡ ተግባራዊ የምናደርግበት ነው።





ሥዕል 11 የስኬል አወቃቀር

## ውህደት

ውህደት ማለት በተሰጠን ውስን ቦታ ላይ የምናሰቀምጣቸውን የተለያዩ እና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው የዲዛይን ስራዎችን ለተመልካቹ አንድ እና ሙሉ የሆነ ስሜት መፍጠር እንዲችሉ እና ውህደት እንዲኖራቸው የምናደርግበት ነው።






ሥዕል 12 የውህደት አወቃቀር

## ምት እና ድግግሞሽ

ከዲዛይን መርሆች መካከል አንዱ ሲሆን በአንድ በተሰጠን ውስን ቦታ የተቀመጡትን የዲዛይን ስራዎች የተመልካቹን የእይታ ስሜት በመምራት የእይታውን ወሰን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የምናመላክትበት ነው። በአንድ የዲዛይን ስራ ላይ ምት እና ድግግሞሽን) ከምንገልፅባቸው መካከል ዝርግ ቅርፅ፣ ቀለም፣ ፎርም ወ.ዘ.ተ. ተጠቃሽ ናቸው።






ሥዕል 13 የምትና ድግግሞሽ አወቃቀር

## አንድነት

አንድነት ማለት በተሰጠን ውስን ቦታ ላይ ያስቀመጥናቸውን የተለያዩ ይዘት፣ ቀለም፣ ባህሪ ያላቸው ምስሎች በጋራ በመሆን እንዲታዩ እና ማስተላለፍ በተፈለገው ጉዳይ ላይ እንደ አንድ እንዲሆኑ የምናደርግበት ነው።





ሥዕል 14 የህብረት አወቃቀር

## ቫራይቲ

ከዲዛይን መርሆች መካከል አንዱ ሲሆን በአንድ በተሰጠን ውስን ቦታ ላይ የተለያየ ይዘት እና መጠን ያላቸውን አለባዊያንን በመጠቀም እና በማደራጀት ሳቢና ማራኪ የሆነ እይታዊ ስሜት የምንፈጥርበት ነው።





ሥዕል 15 የቫራይቲ አወቃቀር

## ተግባር- አንድ

ተማሪዎች፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህሩ(ሯ) ግለፁ። ተግባሮቹን ለማከናወን እርሳስ፣ ወረቀት፣ ከሰል፣ ክራዩን፣ ፓስቴል ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ተጠቀሙ።

1. መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አላባዊያን ሊያሳዩ የሚችሉ የተለያዩ የዲዛይን፣ የቀለም ቅብና የስዕል ስራዎችን ሰርታችሁ አሳዩ?
2. መሰረታዊ የዲዛይን መርሆችን ያካተቱ፣ ጥሩ ቅንብራዊ ሂደትን የያዙ እና የሚያሳዩ መሆናቸውን፣ የትኛው ስራ ከየትኛው የተሻለ እና ያነሰ መሆኑን ምክንያታዊ በመሆን ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?
3. በምትኖሩበት ቤትና አካባቢ ለተለያየ ተግባር እና አላማ ተብለው (ታስበው) የተሰሩ ልዩ ልዩ የዲዛይን ውጤቶችን (ስራዎችን) በመመልከት መሰረታዊ የዲዛይን አላባዊያንን አሟልተው መሰራታቸውን፣ የትኛው የበለጠ ለእናንተ ደስ የሚል ስሜት እንደሰጣችሁ በምክንያት አስደግፋችሁ ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

# 1.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች እና ውዝዋዜዎች

## 1.2.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች

### ተግባር ሁለት


1. በምትኖሩበት አካባቢ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ባህላዊ የሙዚቃ አይነቶችን ዘርዝሩ።
2. የባህላዊ ሙዚቃዎች መሰረታዊ ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ በምክንያት አስረዱ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ሙዚቃ ብዙ ዘመናትን ካሰቆጠሩ እና ከማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች መካከል አንዱ ነው። የኢትዮጵያ ሙዚቃ ከመላው አፍሪካ እና በተለይም ደግሞ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን መሰረቱም ሀይማኖት እና ሀገረሰባዊ እምነቶች ናቸው። በአጠቃላይ በአዓለም ላይ ያሉት ሙዚቃዎች በሁለት መንገድ ሊታዩ ይችላሉ አንደኛው መንፈሳዊ ይዘት ያለው ዜማ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዓለማዊ ይዘት ያለው ዜማ ነው።

**ማስታወሻ፡-**

ባህላዊ ሙዚቃ የሚባለው የአንድ ማህበረሰብ የማንነቱ መገለጫ የሆነው ባህሉን፣ ወጉን፣ ልማዱን እና ቋንቋውን ስርዓት ባለው መልኩ በግጥም እና ዜማ በማዋሀድ የሚያቀርብበት እንዲሁም ለረጅም ዘመናት በቅብብሎሽ የመጣ ሲሆን ማህበራዊ ክዋኔዎችን የሚያደምቅበት የማንኛውንም ግለሰብ የፈጠራ ባለቤትነትን የማያረጋግጥ ጥበባዊ ድርሰት ነው።

በእነዚህ ሙዚቃዎች የህበረተሰቡን ወግ፣ ልማድ፣ እምነት፣ አመለካከት፣ ቋንቋ በአጠቃላይ ባህሉንና እሴቱን ለረጅም ዘመናት ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ አፋዊ ወይም ቃላዊ በሆነ መንገድ ሲያስተላልፍበት ቆይቷል። እነዚህ የሙዚቃ አይነቶች ካለቸው ባህሪያት አንጻር ሀገረሰባዊ (ባህላዊ) እና ዘመናዊ ሙዚቃ በሚል በሁለት ዋና ዋና ምድቦች መክፈል ይቻላል።




ሀገረሰባዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃን ለመለየት በአብዛኛው የተለመዱት መንገዶች የሙዚቃው ግጥም፣ ዜማው፣ ስልተ ምቱ፣ የሙዚቃ መሳሪያው እና ሙዚቃው የሚቀርብበት አውድ ናቸው። የሀገረሰባዊ ሙዚቃ ግጥም የማህበረሰቡን ባህል፣ አካባቢ፣ ታሪክ፣ እምነት፣ ሀይማኖት ወዘተ የሚገልጽ እና ሀገርበቀል የዜማ ስልቶችን የሚጠቀም፤ ስልተ ምቱ ባህላዊ የሆነ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎቹም ከአካባቢው በተገኙ ግብአቶች የተሰሩ እና የማህበረሰቡን ባህል የሚያንጸባርቁ ናቸው።

የሀገረሰባዊ ሙዚቃ ግጥም፣ ዜማ እና ሙዚቃዊ ቅንብር በማህበረሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየ ሲሆን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ የሚታወቅ እና በተወሰነ አካባቢ ወይም ባህል ወስጥ የተገደበ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሀገረሰባዊ ሙዚቃ በተለያየ ቅርጽ የሚቀርብና ሁልግዜ ተለዋዋጭ ነው። ምክንያቱም ግጥሙ፣ ዜማው እና ቅንብሩ በቃላዊ እና በክወና ሂደት ከግለሰብ ወደ ግለሰብ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ በመሆናቸው ከዋኙ ሳያውቅ ወይም ሆን ብሎ ሊለውጣቸው ይችላል።

ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎች ከተለያዩ ማህበራዊ ስርአቶች ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ናቸው። ለምሳሌ ክብረ በዓላቶች፣ የሰርግ ስነ ስርአቶች፣ የጋራ ስራዎች፣ ጀግንነት (ፉከራ፣ ሽለላ እና ቀረርቶ)፣ ጨዋታዎች፣ እምነቶች ወዘተ በሚቀርቡበት ወቅት በሀገረሰባዊ ሙዚቃ ይታጀባሉ። በማህበረሰቡ ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦች ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎች በሚከወኑበት ወቅት የሰዎች የጋራ ተሳትፎ ያለበት ሲሆን እነዚህ ግለሰቦች ጥበቡን የሚከውኑት በአብዛኛው ለገቢ ማስገኛ ወይም ለንግድ ሳይሆን አንድን ማህበራዊ ስርአት ለማድመቅ በሚል የውስጥ ፍላጎት ብቻ ነው። የሀገረሰባዊ ሙዚቃ ግጥም፣ ዜማ፣ ቅንብር ወዘተ የግለሰብ የባለቤትነት ጥያቄ የሌለባቸው የህዝብ የጋራ ፈጠራ ውጤቶች ናቸው።

የኢትዮጵያ ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎች ካላቸው ባህሪ አንጻር መንፈሳዊ እና ዓለማዊ በሚል በሁለት መክፈል እንደሚቻል ከላይ አይታችኋል። መንፈሳዊ ዜማዎች የሚባሉት ሃይማኖታዊ እና ስርዓት አምልኮትን ለመፈፀም የሚከወኑ የተለያዩ መንፈሳዊ ዜማዎች አሉ። እነዚህም በአራት ዘርፎች ተከፍለዋል። እነሱም፦

1. የክርስትና እምነት መንፈሳዊ ዜማዎች (ግዕዝ፣ እዝል፣ አራራይ ወዘተ)
2. የእስልምና እምነት መንፈሳዊ ዜማዎች (መንዙማ፣ ነሽዳ፣ ባሮ)
3. ሀገረሰባዊ ሀይማኖቶች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች (እሬቻ፣ ማጋኖ)
4. የሀገረሰባዊ እምነቶች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ናቸው።

የሀገረሰባዊ ሀይማኖቶች ተከታይ የሆኑ ግለሰቦች ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑበት፣ በአምላካቸው ለተደረገላቸው ነገር ምስጋና የሚያቀርቡበት፣ አምላከቸው ከተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ከሆኑ አደጋዎች ቤተሰባቸውን፣ ሰብላቸውንና እንስሳቶቻቸውን እንዲጠብቅላቸው ወዘተ የሚለምኑበት የራሳቸው የሆነ መንፈሳዊ ዜማዎችን የሚያካትት ነው። በተጨማሪም በሀገረሰብ እምነቶች ላይ የሚከወኑ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ከዋኞቹ እምነቱ የሚፈልገውን ድርጊት በሚፈፀምበት ወቅት የሚያቀርቧቸው መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ናቸው።


ዓለማዊ የሀገረሰብ ሙዚቃዎች ማህበረሰቡ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ፍቅሩን፣ ጥላቻቸውን በተጨማሪም ሌሎች ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮች ላይ ባህሉን መሰረት በማድረግ የተሰማውን ስሜት ይገልጽባቸዋል። እነዚህ ሙዚቃዎች አንድ አይነት ስልት እና ዜማዊ በሆነ ግጥም እንዲሁም የራሱ የሆነ ስልተ ምት በመከተል የሚዜሙ በአብዛኛው ባለ አምስት ድምጽ ቅኝት ሲሆኑ ነገር ግን ኢትዮጵያ በርካታ የብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች ባህል እንዲሁም ሙዚቃዎች ያለባት በመሆኑ ከሁለት እስከ ሰባት የድምጽ ድርድር ስርዓት ያላቸው ቅኝቶችን የሚጠቀሙ ማህበረሰቦችም አሉ። በመሆኑም በተለያዩ ማህበረሰባዊ በዓላት ወቅት እና የእምነት ስርዓት ውስጥ የሚከናወኑ ህዝባዊ እና ሀይማኖታዊ ስርዓት ከበራዎችን ለማድመቅ የበዓላት ዘፈኖች ይዜማሉ። ለምሳሌ ሆያ ሆዬ፣ እንቁጣጣሽ፣ ቡሄ በሉ፣ አበባየሆሽ፣ ሚስቶዬ ሚስቶዬና የመሳሰሉት ሀገረሰባዊ ዘፈኖችን በምሳሌነት ማስቀመጥ ይቻላል።

# እንቁጣጣሽ

እንቁጣጣሽ እንኳን መጣሽ
በአበቦች መሀል እንምነሽነሽ
በመስከረም ወር .....አበባ
በአዲስ አመት....... አበባ
በአበቦች መሀል.......አበባ
እንጫዎት ............አበባ
ፍቅር እና ሰላም......አበባ
ይሁንልን ............አበባ
ምኞታችንም...........አበባ
ይሳካልን .............አበባ

## ባህላዊ ጨዋታ እንቁጣጣሽ








ሥዕል 16 ልጆች አዲስ አመትን በማስመልከት እንቁጣጣሽ ሲያከብሩ እና ሲጨፍሩ

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃዎች ውስጥ በስፋት የምንጠቀምባቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ድራም፣ ሳክስፎን፣ ትራምፔት፣ ፍሉት፣ ጊታር፣ ክላርኔት፣ ፒያኖ ወዘተ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሙዚቃዎቹ ዘመናዊ የሚያስብላቸው የሙዚቃ መሳሪያዎቹ ዘመናዊ ቴክኖሎጂንና ሳይንሳዊ ዘዴን ተጠቅመው የተዘጋጁ መሆናቸውና ከውጭ ሀገር ወደ ውስጥ የገቡ መሆናቸው እንዲሁም እንደ ባህላዊ መሳሪያዎች በአካባቢ ጥሬ እቃዎች ሊዘጋጁ ካለመቻላቸው በተጨማሪም ቅንብራቸው (ኮምፖዚሽን) እና ውህዳቸው (ሀርመኒ) ከአውሮፓ ሀገራት ጋር የተወሰደ ነው፡፡

በሌላ መልኩ አንድ ማህበረሰብ ሀገርን እና ህዝብን ለወራሪ ጠላት አሳልፎ እንዳይሰጥ በተለያዩ የጀግንነት ዘፈኖች ማለትም በፉከራ፣ በሽለላ እና በቀረርቶ በመጠቀም የጠላት ወገንን የመዋጋት ስሜት እንዲጨምር እና እንዲነሳሳ

በማድረግ የቀደምት አባቶቻችንን ሀገራችን ከጠላት ነፃ በማውጣት ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት እንዳትገዛ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አብርክተዋል ከነዚህም ውስጥ የባህላዊ የሙዚቃ ባለሙያዎች አዝማሪዎች ከፍተኛ ሚና ነበራቸው።




ሥዕል 17 የሀገር ፍቅርን እና ጀግንነትን የሚያበረታቱ የጀግንነት ዜማዎች

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች የሚከተሉትን ባህሪያትን ይዘው ይገኛሉ እነዚህም

- የመደብ ልዩነት የሌላቸው(የዘር፣ የከፍተኛ እና የዝቅተኛ ኗሪ፣ የፆታ ልዩነት)
- በአፋዊ (በቃል) ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ መሆናቸው።
- ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ውህደት ያላቸው መሆኑ
- ለረጅም አመታት በቅብብሎሽ ሲዘፈኑ የኖሩ መሆናቸው
- ደራሲያቸው እራሱ ማህበረሰቡ መሆኑ ናቸው።







ሥዕል 18 ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎች በተለያዩ ማህበራዊ ሁነቶች ላይ ሲከወኑ

## 1.2.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜዎች

ባህላዊ ውዝዋዜዎች አንድን ማህበረሰብ በራሱ ባህላዊ ሙዚቃዎች ታጅቦና ባህላዊ ባህሉን የሚያንጸባርቁ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማጌጥና አልባስትን ለብሰው በተለያዩ ማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ የሚያከናውኑት እስክስታ ማለት ነው።

በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች በመጠቀም ማህበረሰቡ ባህሉን፣ ፍልስፍናውን፣ ታሪኩን፣ የኑሮ መሰረቱን፣ የእለት ተእለት ድርጊቱን ወዘተ መነሻ በማድረግ በህዝባዊ የውዝዋዜ ቅንብር በተጨማሪም በተናጠል የፈጠረው እና በክዋኔ ከትውልድ ትውልድ እያስተላለፈ ያቆየው የጋራ ሀብቱ ነው። ይህን ውዝዋዜ ማህበረሰቡ የሚያከናውነው በዋናነት በሁለት ምክንያት ነው። ይኸውም አንደኛ ማህበራዊ ስርአቶቹን ለማስፈጽም ሲሆን ሁለተኛው ደገሞ ሀይማኖታዊ ስርአቶችን ለማድረግ ያስችለው ዘንድ ነው።

በጥንት ጊዜ በኢትዮጵያ በማህበራዊና ሀይማኖታዊ ስርአቶችን ለማስፈጽም የሚጠቀሙባቸው ባህላዊ ውዝዋዜዎች ቀደምት እና ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ሲሆኑ ልዩልዩ ክብረበአላት፣ ፌስትቫሎች፣ ሀይማኖታዊና እምነታዊ ክዋኔዎችን፣ ሙዚቃዎችና መሰል ሁነቶች ላይ የሚቀርቡ የተለያዩ ድርጊቶች በባህላዊ ውዝዋዜዎች ይታጀባሉ። በተለያዩ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ያሉ የሀገረሰብ ወዝዋዜ አይነቶች ከሚቀርቡበት ዓላማ አንጻር መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ውዝዋዜዎች በሚል በሁለት መክፈል ይቻላል። መንፈሳዊ ወዝዋዜዎች ከአቀራረብ አውዳቸው በመነሳት በአራት እንመድባቸዋለን እነሱም

1. በክርስትና ሀይማኖት ስርዓት ላይ የሚፈጸሙ
2. በእስልምና ሀይማኖት ስርአት ላይ የሚፈጸሙ
3. በሀገረሰባዊ ሀይማኖት ስርአት ላይ የሚፈጸሙ
4. በሀገረሰባዊ እምነቶች ስርአት ላይ የሚፈጸሙ ውዝዋዜዎች ናቸው።

ዓለማዊ ውዝዋዜዎች ደግሞ ከሚቀርቡበት ማህበራዊ አውድ በመነሳት የደስታ፣ የሀዘን፣ የጀግንነት፣ የአደን እና የመሳሰሉት በማለት መመደብ ይቻላል። በአገራችን በሚገኙ ማህበረሰቦች ባህል ውስጥ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ፦ ሰርግ፣ ለቅሶ (ሙሾ)፣ ጨዋታዎች ወዘተ የተለያየ የአጨፋፈር ስልት አይነት ባላቸው ውዝዋዜዎች ታጅበው ይቀርባሉ። የውዝዋዜዎቹ አጨፋፈርም በእግር፣ በትከሻ፣ በአንገት፣ ከወገብ በላይ ባለው የሰውነት ክፍል፣ ከወገብ በታች

ባለው የሰውነት ክፍል እንዲሁም በሙሉ የሰውነት ክፍል ወይም አካል ሊከወኑ ይችላሉ።

ውዝዋዜዎቹ ወደ ላይ በመዝለል፣ መሬት ላይ በመተኛት፣ በመሄድ፣ አንድ ቦታ በመቆም ወይም በሌሎች ስልቶች የሚከወኑ ሲሆኑ ከጾታ አንጻር ደግሞ የወንድ እና የሴት በሚል በተለያየ ስልት ይቀርባሉ። በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ባህል ውስጥ በርካታ ባህላዊ ውዝዋዜዎች አሉ። ከነዚህ ባህላዊ ውዝዋዜዎች መካከል የተወሰኑት በሚከተለው መንገድ ቀርበዋል።

#### 1.2.2.1 በአማራ ክልል የሚገኙ ባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶች እና ስያሜያቸው

በአማራ ክልል ልዩ ልዩ ማህበራዊ አውድ ያላቸው ውዝዋዜዎች እና ጭፈራዎች ይገኛሉ። እነዚህ ጭፈራዎች ትኩረት በሚያደርጉባቸው የሰውነት አካሎች እና የጨዋታ አውዶችን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ቢሆንም የሚመሳሰሉበት አጋጣሚዎችም አሏቸው። በክልሉ የሚገኙት አካባቢዎች ወሎ፣ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ሸዋ፣ ዋግህምራ፣ አዊ፣ ኦሮሞ (ኦሮሞ ብሄረሰብ) እና አርጎባ ወ.ዘ.ተ. ሲሆኑ የየራሳቸው ባህላዊ ውዝዋዜዎች አሏቸው። በመሆኑ የውዝዋዜዎቹ ስያሜዎች የሚመነጩት ከማህበረሰቡ አጠቃላይ ባህል እና ወግ በመሆኑ ስያሜዎቻቸው የማህበረሰቡ ስም ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም የወሎ ጭፈራ ትምትም፣ የጎንደር ድስቅና መንጥቅ፣ የጎጃም ነጠላና ዝናብ እንቅጥቅጥ፣ የሰሜን ሸዋ ዋንጫ ልቅለቃና ምንጃር፣ የራያ ላሌጉማና የዋግኽምራ ደግሞ የሴቶች ጭፈራ እስክስታ እየተባሉ ይጠራሉ። ይሁን እንጅ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ በርካታ ያልተጠቀሱ በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ ስያሜ ያላቸው ባህላዊ ውዝዋዜዎች ይገኛሉ።



ሥዕል 19 በአማራ ክልል ከሚገኙ ውዝዋዜዎች በከፊል

### 1.2.2.2 በሀገራችን የሚገኙ ውዝዋዜዎች

በኢትዩጵያ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች በአጨዋወት ስልታቸው እና በስልተ ምት አጠባበቃቸው ተመሳሳይነት ያላቸው ባህላዊ ጭፈራዎች ያሉ ሲሆን ለአብነትም የአዊ ብሔረሰብ ጭፈራ ከወላይታ ባህላዊ ጭፈራ ጋር ይመሳሰላል። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ከሚገኙ በርካታ የብሔር ብሔረሰብ ባህላዊ ጭፈራዎች ውስጥ ለአብነት የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

- የኦሮሞ ብሄረሰብ ጭፈራዎች የሚባሉት

  ረገዳ፣ ሸጎየ፣ ፎሌ፣ ደቺሳ፣ ሸቢሳ፣ ትሪ፣ ቡጡላ፣ ጫሳሮባ እና ጌሎ ባህላዊ ጭፈራ ወዘተ

- የትግራይ ባህላዊ ጭፈራዎች የሚባሉት

  የተምቤን፣ እንደርታ፣ ተልሂት፣ ሆራ ሰደሰይ ወዘተ

- የጉራጌኛ ባህላዊ ጭፈራዎች
- በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች የሚገኙ ባህላዊ ጭፈራዎች ደግሞ

  ሲሎ፣ ሌምቦ፣ ወላይታ፣ የአላባ፣ የመዠንገር፣ ዶርዚኛ ወዘተ

- በሱማሌ አካባቢ ሀያያዋ ሲዳወያ፣ ቡራንቡር፣ ዳንቶ ያሉ ወዘተ

በኢትዮጵያ የሚገኙት ከላይ የተዘረዘሩት ውዝዋዜዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም እንዳሉ ማወቅ ተገቢ ነው። በተጨማሪም በሁሉም ማህበረሰብ ባህል ውስጥ

የሚከወነው ሀገረሰባዊ ውዝዋዜ እያንዳንዱ እንቅስቃሴዎች የራሳቸው የሆኑ ባህላዊ ትርጉም አላቸው። በተጨማሪም ባህላዊ ውዝዋዜዎችን በአብዛኛው ከመልከዓምድራዊ ተፈጥሮ፣ ከእንስሳት እና ከሰዎች የእለት እለት እንቅስቃሴዎችን መነሻ ያደረጉ ናቸው። ለምሳሌ ዶሮ ውሃ ስትጠጣ ራሷን ዝቅ አድርጋ ውሃ በአፏ ከያዘች በኋላ ወደ ላይ አንገቷን ቀና በማድረግ ትውጣለች ይህንን የዶሮ ተፈጥሯዊ ድርጊት በመወሰድ የተሰራ ባህላዊ ውዝዋዜ በጎንደር አካባቢ ይዘወተራል። እንዲሁም በትግራይ አውርስ እና በሲዳማ ሌምቦ የተወሰደው ከወፍ እንቅስቃሴ ነው። ከማህበረሰቡ የእለት ከእለት ድርጊት መነሻ በማድረግ ደግሞ የጉራጌ፣ የጋሞ እና የምንጃር ውዝዋዜ ከፈረስ ግልቢያ የተወሰደ ሲሆን የአደን እና የእርሻ ስራን የሚገልጽ ነው። በአጠቃላይ ባህላዊ ውዝዋዜዎቹ በጾታ ረገድ ለብቻ (በተናጠል)፣ በጥንድ ወንድ እና ሴት በመሆን የሚጨፍሯቸው ናቸው።



ሥዕል 20 በኢትዮጵያ ከሚገኙ ውዝዋዜዎች በከፊል

## 1.3 የቴያትር ጥበባት

ቴያትር የሰው ልጆችን የእለት ከዕለት እንቅስቃሴ እና ክንውንን መነሻ በማድረግ በዋናነት ማህበራዊ፣ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሀይማኖታዊ ሀሳቦችን ውበት በተላበሰ አቀራረብ በመድረክ ላይ የምንገልፅበት እና የምናሳይበት የስነ ጥበባት ዘርፍ ነው። በተጨማሪም ከክውን ጥበባት ውስጥ የሚመደብ ሆኖ በዋናነት የተለያዩ ገፀ ባህሪያቶችን በተናጠል እና በህብረት (በጋራ) በመድረክ ላይ ትዕይንትን ለተመልካች የሚቀርብበት አንዱ ክውናዊ ጥበብ ነው።

## ማስታወሻ፡-

**ቴአትር የሚለው ቃል ቴያትሮን ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም ተመልካቾች እና የማሳያ ቦታ (ስቴጅ) በማሟላት ለተመልካቾች ድራማዊ እንቅስቃሴን፣ ሙዚቃዊ ቴአትርን፣ ውዝዋዜን፣ ህዝባዊ ክብረ በዓላት እና ፊልም የመሳሰሉት የሚታዩበት ትውናዊ የጥበብ ዘርፍ ነው።**

ቴያትር በዓለም ላይ መቼ እና የት እንደተጀመረ የዘርፉ ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ ባደረጓቸው ጥናታዊ ፅሁፎቻቸው እንደሚጠቁሙት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛው መቶ ክፍል ዘመን በጥንታዊ ግሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ድራማዊ ባህሪ ያለው ትዕይንት መቅረቡን ያሳያሉ።





ስዕል 21 የቴያትር ውስጣዊ ይዘትን የሚያሳዩ የቴአትር መድረኮች





ሥዕል 22 የቴያትር ማሳያ ቦታዎች ውጫዊ ገፅታ

### 1.3.1 የቴያትር አለባዊያን

መሰረታዊ የቴያትር አለባዊያን የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው።

- ሀሳብ
- ጭብጥ
- ገፀ ባህሪ
- መቼት
- ግጭት
- ድራማዊ ድርጊት
- ንግግር

ከላይ ከተጠቀሱት የቴያትር አላባዊያን መካከል የተወሰኑትን እንመልከት

1. ገፀ ባህሪ፦ ሲባል በታሪክ ውስጥ ተስለው የሚገኙትን ሰዎችን ለማለት ሲሆን እንስሳት፣ ግዑዝ ነገሮች፣ ረቂቅ ሀሳቦችና መንፈሳዊ ፍጡራን ባለታሪክ ከሆኑ እንደ ገፀ ባህሪያት ይቆጠራሉ::

2.መቼት፦ የቴያትሩ ታሪክ የሚከናወንበት ቦታ እና ወቅት መቼት እየተባለ ይጠራል:: መቼ እና የት እንደ ማለት ነው::

3.ጭብጥ፦ የቴያትሩ ሙሉ ታሪክ በዋናነት ለማስተላላፍ የተፈለገው ፍሬ ሀሳብ ጭብጥ ይባላል::

### 1.3.2 የቴያትር አይነቶች

ቴያትር የተለያዩ ዘውጎች ያሉት ሲሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

1. ቀልድ (ኮሜዲ) ቴያትር
2. ድራማዊ ቴያትር
3. ሙዚቃዊ ቴያተር
4. አሳዛኝ (ትራጄዲ) ቴያትር
5. ማህበረሰባዊ (ኮሚኒቲ) ቴያትር የመሳሰሉት ናቸው።

ተማሪዎች፣ ከላይ የቴያትር አይነቶች ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል የተወሰኑት

እንደሚከተለው በማብራሪያ ሀሳቦች ተደግፈው ቀርበዋል።

## ቀልድ (ኮሜዲ) ቴያትር

ቀልድ ወይም ኮሚዲ ቴያትር ማለት ቀልድ አዘል የሆኑ ገፀ ባህሪያትን እየፈጠረ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሌሎች የማህበረሰቡን ነባራዊ ሀቅ በቧልት እና በቀልድ መልኩ የሚያሳይ ሲሆን በግል እና በህብረት ሊከወን የሚችል ጥበብ ነው። ይህ የቴያትር ዘውግ ተመልካችን የሚያዝናና እና ደስታን የሚፈጥር ሆኖ በድፍረት የማይነገሩ ቁም ነገሮችን በስውር የሚያስተላለፍ ነው።

## ሙዚቃዊ ቴያትር

በድርጊት እና በንግግር የሚቀርቡ ቴያትሮች እንዳሉ ሁሉ ድርጊቶቹን እና ንግግሮቹን ወደ ምታዊ እና የተለኩ እንቅስቃሴዎች በመለወጥ እንዲሁም ንግሮቹን ከዜማዊ ባህሪያት ጋር በማዋሀድ የሚቀርብ ቴያትር ሙዚቃዊ ቴያትር ይባላል። በውስጡም ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ ዜማዊ ንግግር፣ ቅብብሎሽ እና ህብረ ዝማሬዎችን አካቶ የሚይዝ ነው።

## ድራማዊ ቴያትር

በአንድ በተወሰነ የደርሰት ሀሳብ ላይ ተነስቶ በውስጡ የተለያዩ ገፀ ባህሪያትን በማዋቀር የሚዘጋጅ ክውን የጥበብ አይነት ነው። ይህ የቴያትር አይነት በባህሪው በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቀናጅቶ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ይሆናል።

- በመድረክ
- በድምፅ እና በምስል
- በድምፅ ብቻ








ሥዕል 22 በመድረክ ላይ የሚቀርቡ ድራማዊ ተውኔቶች

## 1.4 የፊልም ጥበብ

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብሎም በዓለም የራሳቸው የሆነ ፊደል፣ ታሪክ፣ ባህል፣ እምነት፣ ጥንታዊ ሰልጣኔ ካላቸው ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ ናት። በሀገራችን ያሉ የፊልም ባለሙያዎች መነሻ የሚሆኑ ፅሑፎችን ለማዘጋጀት አይቸገሩም። ይህ ዘርፍ የራሱ የሆነ እውቀት፣ ክህሎትና ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም የሚተገበር ነው። በኢትዮጵያ የፊልም ጥበብ ከተጀመረ ረጅም ጊዜ ሆኖታል። ለመጀመሪያ ጊዜ በ1957 ዓ.ም በጥቁርና ነጭ ምስል የተሰራ ‹ሒሩት አባቷ ማነው› የሚለውና በደራሲ ኢላላ ኢብሳ የተዘጋጀው ፊልም በሀገራችን የፊልም ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ነው።

የፊልም ጥበብ አጀማመር በሀገራችን የቆየ ቢሆንም በተፈለገው መጠን ማደግ አልቻለም። ለኢትዮጵያ ፊልም አለማደግ ተፅዕኖ ካሳደሩ በርካታ ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት በዋነኝነት ይጠቀሳሉ።

- ዘርፉ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ በመሆኑ
- የማህበረሰቡ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እና በቂ የፊልም ባለሙያዎች አለመኖር ወ.ዘ.ተ.

ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች መሰረታዊ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ የሀገራችን የፊልም ጥበብ እድገት ሌሎች በፊልሙ ኢንዱስትሪ ያደጉት ሀገራት የደረሱበት የፊልም እድገት ደረጃ መድረስ እንዳይችል እንቅፋት ሆኖታል።

**ማስታወሻ፡-**

ፊልም ማለት ተከታታይነት ያለው ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ከድምፅ ጋር በመቅርፅ እና በማቀናበር ታሪክን በሚነግር መልኩ በቴሌቪዥን፣ በሲኒማ እና በተለያዩ አማራጭ የምስል ማሳያ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚታይ ጥበብ ነው። ፊልም አጠቃላይ ማህበራዊ እሴቶችን፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ክዋኔዎችን እንዲሁም ፍቅርን፣ መተሳሰብብን እና ሌሎች ማህበረሰባዊ ክስተቶችን ጥበባዊ እሴቶችን በመጨመር ለተመልካች የሚቀርብ እይታዊ ጥበብ ነው።

## 1.4.1 የፊልም ጥበብ አለባዊያን

በፊልም ስራ ውስጥ የሚካተቱ ዋና ዋናዎቹ የፊልም አለባዊያን የሚባሉት

1. ሴራ (ፕሎት)
2. መዋቅር
3. ገፀ ባህሪ
4. ቅንብር
5. ውበተ-ፊልም (ድምፅ፣ ሙዚቃ፣ መብራት፣ ካሜራ፣ መቅረፀ-ቦታ፣ ኤዲቲንግ)

## 1.4.2 የፊልም ጥበብ አይነቶች

በአለም ላይ እስካሁን ድረስ በፊልም የተለያዩ ዘውጎች ያሉ ሲሆን ከዚህ በታች ዋና ዋናዎቹን የፊልም አይነቶች የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው

1. ጀብዳዊ ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
2. ድራማዊ ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
3. የፍቅር ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
4. ቀልድ (አስቂኝ) ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
5. ድርጊታዊ ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
6. ዘገባዊ ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
7. ምርምራዊ ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
8. ሳይንሳዊ ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ
9. አኒሜሽን (የካርቱን) ይዘት ያለው የፊልም ጥበብ

ከላይ ከተዘረዘሩት የፊልም አይነቶች መካከል የተወሰኑት ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

1. የጀብዳዊ ይዘት ያለው ፊልም ምንነት፦ ይህ የፊልም አይነት በድርጊት ከተሞሉ ፊልሞች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በጥንታዊ ታሪኮች ላይ በመመርኮዝ ጀብደኛ የሆኑ ባለታሪኮች ተካተውበት የሚፃፍ ነው:: ጫካ፣ የቆየ መንደር፣ ዋሻ፣ በርሀ ወ.ዘ.ተ በጀብድ ለተሞሉ ፊልሞች ተዘውትረው የሚሰሩባቸው ቦታዎች ናቸው::

2. ቀልድ (አስቂኝ) ይዘት ያለው ፊልም ምንነት፦ ይህ የፊልም አይነት ባልተጠበቁ ተቃራኒ ክስተቶች እና ክንዋኔዎች የሚፈጠሩ ድርጊቶች እና ቀልድ የበዛባቸው ንግግሮችን ይዘው የሚተገበሩ ናቸው:: ታሪካቸውም ከጭንቀት እና ከፍርሀት በተቃራኒው መዝናናትን የሚፈጥር ሳቅ እና ደስታን መፍጠር በሚችሉ ገፀ ባህሪያት ተሞልተው የሚፃፉ ናቸው:: ለምሳሌ፦ የወንዶች ጉዳይ፣ ባለቀለም ህልሞች ወ.ዘ.ተ


3. ሳይንሳዊ ይዘት ያለው ፊልም ምንነት፦ ይህ የፊልም አይነት በድርጊት ተሞልተው የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ከታሪኩ ጋር በማቆራኘት የሚያሳይ ነው:: ከምድር ውጭ የሚደረጉ ሳይንሳዊ ምርምሮች፣ የተራቀቁ የኮምፒዩተር

ቴክኖሎጅዎች እና ሮቦቶችን በስፋት የሚጠቀም የፊልም አይነት ነው፡፡

**ለምሳሌ፡-**

1. A Trip to The Moon (ዘ ትሪፕ ቱ ዘ ሙን )
2. The Sixth Sense (ዘ ሲግዝ ሰንስ)
3. Star Wars (ስታር ዋርስ)
4. Back to The Future (ባክ ቱ ዘ ፊዩቸር) ወ.ዘ.ተ.

4. ድራማዊ ይዘት ያለው ፊልም ምንነት፡- ይህ የፊልም አይነት የሰው ልጅ በእለት ተእለት ኑሮው የሚያጋጥሙትን የህይወት ውጣ ውረዶችን እንዲያሳዩ ተደርገው የሚፃፉ ታሪኮች ናቸው፡፡ ፍቅራዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ እና ሀይማኖታዊ ፊልሞች የሚካተቱበት የፊልም አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቤቶች፣ ጤዛ፣ ስስት፣ ውሳኔ ወ.ዘ.ተ.






ስዕል 23 በሀገራችን ከሚሰሩ በርካታ ፊልሞች ውስጥ የተወሰኑትን የፎልም ፖስተሮች

| ተ.ቁ | የምዕራፉ ይዘት | ተረድቻለሁ | አልተረዳሁም |
|---|---|---|---|
| 1. | መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያንና የዲዛይን መርሆች ምንነታቸውንና አስፈላጊነታቸውን | | |
| 2. | መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን እና መርሆች በተለያዩ የስነ ጥበብ ተግባራት ላይ የአተገባበር ሂደትን | | |
| 3. | የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎች አመዳደብና አይነቶች እንዲሁም ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ | | |
| 4. | የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ስያሜዎችን | | |
| 5. | በክልሉ የሚገኙ ባህላዊ ውዝዋዜዎች አይነትና ስያሜ | | |
| 6. | የቴያትር ጥበባት ምንነትና አይነቶች | | |
| 7. | የፊልም ጥበባት ምንነትና አይነቶች | | |

## ማጠቃለያ

ነገሮችን በልዩ ሁኔታ አስውቦ የማደራጀት ጥበባዊ ተግባር ዲዛይን ይባላል። መስመር፣ ቀለም፣ ዝርግ ቅርፅ፣ ለስላሳና ሸካራ፣ ቦታና ፎርም የሚባሉት የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን ናቸው። ንፅፅር፣ ፓተርን፣ አፅንኦት፣ ሚዛን፣ ውህደት፣ ስኬል፣ ምትና ድግግሞሽ፣ አንድነትና ቫራይቲ ደግሞ የዲዛይን መርሆች ይባላሉ። የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን ለማንኛውም የዲዛይን ተግባር መሰረታዊ ሲሆኑ የዲዛን መርሆች የዲዛይን ስራዎችን በመስራት ሂደት ውጤቱ በተመልካች ዘንድ ሳቢና ማራኪ እንዲሆን የሚያስችሉ ናቸው።

ኢትዮጵያ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መገኛ የሆነች ሀገር ስትሆን የራሳቸው የሆነ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ቋንቋ እና ባህላዊ ሙዚቃዎች አሏቸው። በኢትዮጵያ ከሚገኙት ማህበረሰቦች መካከል በአማራ ክልል የሚገኙ ማህበረሰቦች ባህላዊ ውዝዋዜ ሀገራዊ እውቅናቸው ከፍተኛ ነው። ከእነዚህም መካከል የወሎ፣ የጎንደር፣ የሸዋ፣ የጎጃም፣ የዋግህምራ፣ የአዊ፣ የኦሮሞና የአርጎባ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ይገኙበታል።

# የማጠቃለያ መልመጃዎች

***ትዕዛዝ አንድ፦ ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።***

1. መሰረታዊ የእይታ ጥበብ አለባዊያን በዲዛይን ተግባራት ላይ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ ነው።
2. ባህላዊ ውዝዋዜዎች (ጭፈራዎች) ለህፃናት አካላዊና አዕምሮአዊ መዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።
3. በዲዛይን ተግባራት ላይ ውስን የእይታ ጥበብ አለባዊያን ብቻ መጠቀም የዲዛይን ስራዎችን ውጤታማ ያደርጋቸዋል።
4. ለተመልካቾች በእንቅስቃሴ፣ በሙዚቃና በውዝዋዜ በስቴጅ ሊቀርብ የሚችል የትወና ዘርፍ ቴያትር ይባላል።
5. ባህላዊ ሙዚቃ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የክውን ጥበብ ዘርፍ ነው።

***ትዕዛዝ ሁለት፦ ተማሪዎች ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች ግልፅ እና አጭር ምላሽ ስጡ***

1. የስነ ጥበባት ዘርፎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. የቴያተርና የፊልም አለባዊያን የሚባሉትን ዘርዝሩ።
3. ዲዛይን ማለት ምን ማለት ነው?
4. አራቱን የፊልም ዘውጎች ዘርዝሩ።
5. በክልላችን ውስጥ ከሚገኙት ባህላዊ የውዝዋዜ አይነቶች መካከል ሶስቱን ብቻ ጥቀሱ።

# ምዕራፍ 2

# የፈጠራ ችሎታን መግለፅ

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የቀለም ቅብ እና የህትመት ስራ ምንነትን ትገነዘባላችሁ
- ለቀለም ቅብ እና ለህትመት ስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ምንነት ትለያላችሁ።
- የክውን እና እይታዊ ጥበባት የመተግበር ብልሃቶችን ታውቃላችሁ።
- የባቲ እና ትዝታ ቅኝቶችን በመጠቀም የተለያዩ ድምፆችን መዘመር ትችላላችሁ።
- የኢትዮጵያ ህገረሰባዊ ውዝዋዜዎችን ትለያላችሁ።
- የስነ ጥበባት ችሎታችሁን ታዳብራላችሁ።
- ማህበራዊ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ ቃለ ተውኔት ማዘጋጀት እና መተወን ትችላላችሁ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የተካተቱት ይዘቶች መሰረታዊ የቀለም ቅብና ባህሪው፣ ቀላል የህትመት አይነቶች፣ ሶልፌጅ ናቸው። በመጨረሻም ፈጠራዊ ክህሎታችሁን ማሳደግ የሚያስችሏችሁን በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የህትመት ስራዎችን መስራት እና በተለያዩ ሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ ለቴአትርና ለፊልም ትወና ጥበብ የላቀ አሰተዋፅኦ ያለው ሀሳብ በማመንጨት ፈጠራዊ ክህሎታችሁን ማዳበር የሚያስችሉ ይዘቶች የተካተቱበት ነው። ለዚህ ተግባር ውጤታማነት የአስተማሪው፣ የተማሪዎች እና ወላጆችን ትብብር የሚጠይቅ

ነው።

## የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስተማሪያችሁ በሚነግራችሁ መሰረት ተወያዩ እና ሃሳባችሁን አስረዱ።

- ፈጠራ ማለት ምን ማለት ነው? ለመምህራችሁ ተናገሩ።
- በአካባቢያችሁ የተለየ ችሎታ የሚጠይቁ የስነ ጥበባት ስራዎች አሉ? ካሉ የተለዩበትን ምክንያት ተናገሩ።

# 2.1. ቀለም ቅብ እና ህትመት

## 2.1.1 የቀለም ቅብ

ተማሪዎች፣ በ6ኛ ክፍል በስነ ጥበባት ትምህርታችሁ ላይ በስፋት ስለ ቀለም ምንነት፣ ስለ ቀለም አፈጣጠር፣ ስለ ቀለማት አይነት ደረጃዎች፣ ስለ ቀለማት ባህሪያት ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ተምራችሁ ነበር። በዚህ የክፍል ደረጃ ደግሞ ስለ ቀለም ቅብ እና ህትመት ምንነት፣ ግብአት፣ የአሰራር ሂደት እና የተግባራት ቅደም ተከተልን በመጠቀም ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው የቀለም ቅብ እና የህትመት ስራዎችን እንዴት መስራት (ማከናወን) እንደሚቻል በዚህ ምዕራፍ ትማራላችሁ።

ቀለም ቅብ የእይታዊ ጥበባት ዘርፍ አንዱ እና ዋነኛው መገለጫ ነው። ይህ ዘርፍ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ጥንታዊው የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸውን የቀለም ቅብ ስራዎችን በዋሻ ውስጥ፣ በድንጋዮች ላይ፣ በእንጨት፣ በቆዳዎች ወ.ዘ.ተ. በመሳሰሉት ነገሮች ላይ በማስፈር በወቅቱ ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ልዩ ልዩ መልዕክቶችን ያስተላልፍበት እና ይገልፅበት እንደነበር በዚህ ዘርፍ ጥናት ያደረጉ ሙህራን እና የተፃፉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይህን የእይታ ጥበባት መገለጫ ዘርፍ ለመተግበር ዋናው ግብአታችን ቀለም ሲሆን ቀለም ቅብ የሚለውን መጠሪያ ስያሜ ያገኘው (የያዘው) ከዚሁ ቀለም እያልን የምንጠራውን ግብአት በመውሰድ ቀለም ቅብ የሚለውን መጠሪያ (ስያሜ) እንዲሰጠው (እንዲይዝ) ተደርጓል። በዚህ ዘርፍ ለመስራት (ለማጥናት)

የምንፈልጋቸውን ሀሳቦች እና የፈጠራ ስራዎችን ለማከናወን ለሀሳብ መነሻነት ሊያገለግሉን የሚችሉ እና የምንጠቀምባቸው በርካታ ነገሮች ቢኖሩም በዋናነት ግን በሁለት መልኩ ከፍሎ ማየት ይቻላል። ይህም

- ✍ ከምናየው (ከምንመለከተው፣ ከምንሰማው፣ ካስደሰተን፣ ካሳዘነን) ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ይዘት ካላቸው ነገሮች ወ.ዘ.ተ. ሀሳብ በመነሳት ሲሆን
- ✍ ከውስጣዊ እይታችን (ከምዕናብ፣ ከአዕምሮአችን) በማፍለቅ ተግባራዊ ይደረጋል።

ለቀለም ቅብ ተግባር የምንጠቀምባቸው በርካታ ግብአቶች ያሉ ቢሆንም ዋና ዋና እና አስፈላጊ የሚባሉትን እንመልከት።

- ቀለም
- ብሩሽ
- ፓሌት (ቀለም ማዋሀጃ)
- የቀለም ማቅጠኛ እቃዎች
- ሸራ (ካንቫስ)
- ልዩ ልዩ ይዘት እና ጥንካሬ ያላቸው ወረቀቶች
- ውሀ
- አኳራጅ (ቀለም ማቅተኛ ጋዝ)
- ቦርድ
- ኢዝል (የስዕል ሰሌዳ)
- ፎጣ (ቁራጭ ጨርቅ)

**ማስታወሻ፡-**

ተማሪዎች፣ ከላይ የተዘረዘሩት ለቀለም ቅብ ተግባራት የምንጠቀምባቸው ግብአቶች ሁሉም ይዘነው እንደምንነሳው ሃሳብ እና የተግባር አይነት በመለየት እና በማወቅ ለትትክክለኛው ተግባር እና አላማ በአግባቡ እና በትክክል መጠቀም መቻል አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

### 2.1.2 ለቀለም ቅብ ተግባር የምንጠቀምባቸው የቀለም አይነቶች ምንነት

ለቀለም ቅብ ተግባር የምናውላቸው በርካታ የቀለም አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል። በመሆኑም በዚህ ዘርፍ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉት እና የሚታወቁት የሚከተሉት ናቸው።

- የዘይት ቀለም
- የውሀ ቀለም
- አክረሊክ ቀለም
- ጓሽ ቀለም
- ቴምፐራ ቀለም
- ክራዮን፣ ፓስቴል፣ ከሰል ወ.ዘ.ተ.

### 2.1.2.1 የዘይት ቀለም ምንነትና የአሰራር ሂደት

ይህ የቀለም አይነት ለቀለም ቅብ ተግባር በስፋት ጥቅም ላይ ከሚውሉት እና ተመራጭ ከሆኑት መካከል አንዱ ነው። ይህን ቀለም ለቅብ ተግባር ስንጠቀምበት በዋናነት እንዴት ማቅጠን እንደሚቻል፣ የአቀባብ ቴክኒኩን እና ሌሎች መሰረታዊ ነገሮችን ማወቅ እና መገንዘብ ያስፈልጋል።

በመሆኑም የዘይት ቀለም በፋብሪካ ደረጃ ከሚመረቱት መካከል አንዱ ሲሆን ቀለሙን ለቅብ ተግባር ስናውል የሚከተሉትን ነገሮች ማወቅ እና መተግበር አስፈላጊ ነው። የዘይት ቀለምን ለማቅጠን (ለማዋሀድ) አኳራጅ፣ ነጭ ጋዝ፣ የምግብ ዘይት (ፈሳሽ) በመጠኑ መጠቀም አስፈላጊ ነው።

የዘይት ቀለሙን በስሱ እና በወፍራሙ በማዋሀድ መቀባት፣ ለዘይት ቀለም መቀቢያ ተብለው የሚዘጋጁ ጠንካራ የሆነ ይዘት ያላቸውን ብሩሾችን መጠቀም፣ ከብርሀን ወደ ጥላ፣ ከጥላ ወደ ብርሀን መቀባት። በዘይት ቀለም የተሰሩ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎች ሰርተን ከጨረስን በኋላ ቀለሙ ካለው ባህሪ የተነሳ ለመድረቅ ከ3-4 ቀን አንዳንዴም የሳምንት ጊዜ ሊወስድብን ይችላል።




ሥዕል 1 በዘይት ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

**ማስታወሻ፡-**

ተማሪዎች፣ የዘይት ቀለምን የአቀባብ ዘዴን በተመለከተ ከላይ በተገለፀው ሀሳብ የዘርፉ ባለሙያዎች የመቀቢያ ብሩሽን በመጠቀም መቀባቱ ተገቢ መሆኑን ይገልፃሉ። በተጨማሪ እጅን፣ ገመድን በመጠቀመም የዘይት ቀለመ ቅብን ማከናወን እንደሚቻል ይገልፃሉ።

- በእጃችን መዳፍ፣ በጣት በስሱ በውፍረመው በማሸት (በማፈናጠር) መቀባት
- በመለጠፍ እና በወፍራሙ (በናይፍ) መቀባት
- አነስተኛ መጠን ባላቸው ገመዶች ደግሞ በማሸት (በማፈናጠር) መቀባት



### 2.1.2.2 የውሀ ቀለም ምንነትና የአሰራር ሂደት

የውሀ ቀለም ለቀለም ቅብ ተግባር ከምንጠቀምባቸው ቀለማት አንዱ እና ዋነኛው ሲሆን የውሀ ቀለም የሚለውን ስያሜ ያገኘው ቀለሙን ለማዋሀድ ከምንጠቀምበት ከውሀ ነው። የውሀ ቀለምን በመጠቀም ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸውን የቅብ ስራዎች ለመስራት አስፈላጊ የሆኑት ግብአቶች የሚከተሉት ናቸው።

- የውሀ ቀለም
- የውሀ ቀለም ብሩሽ
- ፓሌት
- የውሀ ቀለም ወረቀት
- ቁርጥራጭ ጨርቆች
- ኢዝል፣ ቦርድ

የውሀ ቀለም የአሰራር ሂደት በውሀ ቀለም መስሪያ ወረቀቱ ላይ መስራት የፈለግነውን ነገር ንድፉን በእርሳስ (በብሩሹ) በስሱ መንደፍ በመቀጠል ቀለሙን በመጠኑ ውሃው ሳይበዛ በማቅጠን በውሀ ቀለም ብሩሽ ከብርሀን ወደ ጥላ (ከንጣት ቅብ ወደ ጥቁረት ቅብ) በዝግታ መቀባት በውሀ ቀለም ቅብ የአሰራር ሂደት ከአንዱ የቅብ ይዘት ወደ ሌላኛው ለመስራት ትዕግስት እና ጥንቃቄን ይፈልጋል። ምክንያቱም የውሀ ቀለም ሲበጠበጥ (ስናቀጥን) በውሀ ስለሆነና ውሀ ስላለው ቶሎ ስለማይደርቅ እንዲሁም የውሀ ቀለም ወረቀቱን ቶሎ ቶሎ ስናሸው የመፈግፈግ (የመነጨት፣ የመቀደድ፣ ቀለሙ የመቆሸሽ)

ሁኔታ ስለሚያጋጥመን ሲደርቅ ትንሽ ቆየት በማለት መቀባት ይኖርብናል።

ሥዕል 2 በውሀ ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

**ማስታወሻ፡-**

ለውሃ ቀለም ቅብ ተግባር የምንጠቀምባቸው ብሩሾች ለዘይት ቀለም ቅብ ተግባር ከምንጠቀምባቸው የተለየ ይዘት እና ባህሪ አላቸው። የውሃ ቀለም ብሩሾች ጫፍ ውፍራም፣ ብዙ እና ለስላሳ የፀጉር ይዘት አላቸው። ይሄም የሆነው በውሀ ያዋሀድነው ቀለም በውስጡ ውሀ ስላለው የብሩሾቹ ጫፍ ቀለሙን እና ውሃውን በምንፈልገው መጠን ለማንሳት(ለመያዝ) ያስችሉናል። በተጨማሪም ለስላሳ መሆናቸው የውሀ ቀለም ወረቀቱ ስንቀባ እንዳይነጭ፣ እንዳይቀደድ፣ እንዳይፈገፈግ ያደርጉልናል።

- የውሀ ቀለም ወረቀቱ ደግሞ በባህሪው ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀ በመሆኑ ቀለሙን ስንቀባ ውሀውን የመምጠጥ (የመያዝ) ባህሪ ስላለው እስኪደርቅ መጠበቅ አለብን
- የውሀ ቀለም የአቀባብ ቴክኒክ ፍሰት ይባላል

### 2.1.2.3 የአክረሊክ ቀለም ምንነት እና አተገባባር

ይህ የቀለም አይነት ለቀለም ቅብ ተግባር ከምንጠቀምባቸው እና በስፋት አገልግሎት ላይ ከሚውሉት መካከል አንዱ ነው። አክረሊክ ቀለምን በካርድ ቦርድ(ወፍራም ወረቀቶች)፣ በእንጨት፣ በብረት፣ በሴራሚክ ውጤቶች ወ.ዘ.ተ. በመሳሰሉት ነገሮች ላይ በመቀባት እና በመጠቀም ለማስዋብ (ለማስጌጥ) ተግባር ይውላል። ይህ ቀለም ለቀለም ቅብ ተግባር ለማዋል በውሀ በማቅጠን

(በመበጥበጥ) የምንጠቀምበት ሲሆን ወደ ቅብ ስራውም ከገባ በኋላ በፍጥነት የመድረቅ ባህሪ አለው። በተጫማሪም ውን (ርጥበትን) የመቋቋም እና ቶሎ ያለመበላሸት አቅም አለው። አክሪሊክ ቀለምን ለቀለም ቅብ ተግባር በብሩሽ ስንቀባ ከአንዱ ይዘት(ክፍል) ወደ ሌላኛው ለመሄድ በመደራረብ መቀባት ይቻላል።




ሥዕል 3 በአክሪሊክ ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

### 2.1.2.4 የጓሽ ቀለም


ይህ ቀለም በውሀ ሊዋሀዱ ከሚችሉት የቀለም አይነቶች መካከል አንዱ ነው። ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ የሚተገበር ነው። ጓሽ ቀለም ከ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ጥቅም ላይ መዋል እንደጀመረ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ጓሽ ቀለም በፍጥነት የመድረቅ ባህሪ (ጸባይ) አለው። በመሆኑም ቶሎቶሎ የመቀባት እድል ይስጣል።




ሥዕል 4 ጓሽ ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

### 2.1.2.5 ቴምፕራ ቀለም

ይህ ቀለም ለመጀመሪ ጊዜ በጥንታዊ ግብጻዊያን የተለያዩ ስነ-ጥበብዊ ስራዎችን በማስዋብ(በማስጌጥ)ተግባር ወቅት እንደተጀመረ እና ጥቅም ላይ እንደዋለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቴምፕራ ቀለም በውሀ ከሚቀጥኑ(ከሚበጠበጡ) ቀለማት የሚመደብ ሲሆን በፍጥነት የመድረቅ ባህሪ አለው። ቴምፕራ ቀለም በወረቀት፣ ጠንካራ ውፍራም ወረቀት፣ በፔፐርማሼ በመሳሰሉት ነገሮች ላይ በቡሩሽ በጣት በስፖንጅ በመሳሰሉት መቀባት ይቻላል።




ሥዕል 5 ቴምፕራ ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

### 2.1.2.6 ክራዮን ቀለም

ይህ ቀለም በብዛት ህጻናት ልጆች ከሚጠቀሙባቸው የቀለም አይነቶች መካከል ተመራጩ ነው። ሰዓሊያንም እንደ ሁኔታው የሚጠቀሙበት ነው ክራዮን ቀለም ብዙጊዜ በቾክ አልፎ አልፎ በፈሳሽ መልክ የሚዘጋጅ ነው። የአቀባብ ቴክኒኩም በማሸት እና በመፈግፈግ ነው።





ሥዕል 6 በክራዮን ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

### 2.1.2.7 ፓስቴል ቀለም

ይህ የቀለም አይነት ለቀለም ቅብ ተግባር ከምንጠቀምባቸው መካከል አንዱ ሆኖ በዋናነት በጠጣርነት መልክ(ጠመኔ) ይዞት የሚዘጋጅ ሆኖ በማሸት(በመፈግፈግ) ቴክኒክ የምንጠቀምበት ነው። ስስ እና ወፍራም(ጠንካራ) ይዘት ባላቸው የወረቀት አይነቶች ላይ መጠቀም ይቻላል።





ሥዕል 7 በፓስቴል ቀለም የተሰሩ የቀለም ቅብ ስራዎች

### 2.1.2.8 የከሰል ቀለም

ይህ የቀለም አይነት በባህሪው ግራጫ እና ጥቁር ይዘት በያዘ መልኩ የሚዘጋጅ ነው። ከሰል ቀለም እንደ ክራዮን፣ ፓስቴል ቀለሞች ሁሉ ስስ እና ወፍራም ይዘት ባላቸው ወረቀቶች ላይ በማሸት (በመፈግፈግ) ቴክኒክ ተግባራዊ የሚደረግ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው እና በቀለም ቅብ ተግባር በግብዓትነት የተመዘገበው በእንግሊዝ በ1606 እ.ኤ.አ ነው።





ሥዕል 8 በከሰል ቀለም የተሰራ የቅብ ስራ

**ማስታወሻ፦**

- ለቀለም ቅብ ተግባር የምንጠቀምባቸው የቀለም አይነቶች እንደየ ቀለማቶቹ ሁኔታ የተለያየ ባህሪ እና የአቀባብ ቴክኒኮችን በመጠቀም ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው።
- የቀለም መቀቢያ ብሩሾችም እንደየቀለማቶቹ አይነት እና ባህሪ እራሳቸውን ችለው በተለያየ ይዘት እና መጠን የሚዘጋጁ ናቸው።
- የዘይት ቀለም ብሩሾች በባህሪያቸው ከውሀ ቀለም ብሩሾች ጠንከር ያለ ይዘት ያላቸው ፀጉሮችን እና ጫፍ ላይ የሚገኘው የፀጉር መጠንም አነስተኛ(መጠነኛ) ነው።
- በቀለም ቅብ፦ የሰው ገፀምስል፣ የቤት ውስጥ ቁሳቀሱ ምስል ቅንብር፣ የቦታዎች ገፅታ (የከተማ፣ የገጠር) ቅንብር ምስል፣ የእንስሳት፣ የእፅዋት፣ የአዕዋፋት ምስል ማጥናት(መስራት) ይቻላል።





ሥዕል 9 ለቀለም ቅብ ተግባር የሚውሉ የተለያዩ ብሩሾች

## ተግባር -1

ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን ስለ ቀለማት ምንነት፣ ባህሪ፣ የአተገባበር ሂደት በጥልቀት እና በዝርዝር ተምራችኋል። ስለሆነም ከዚህ በታች የቀረቡትን የተግባር ስራዎች መነሻ በማድረግ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው የቀለም ስራዎችን ስሩ

1. የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ቅንብር
2. የሰው ገፀ ምሰል (የራስ ቅል የተወሰነ የደረት ክፍልን) ያካተተ
3. የመሬት (የቦታዎች) ገፅታ መልክአ ምድር ወ.ዘ.ተ.

## 2.1.2 ህትመት

ህትመት ከስነ ጥበብ ዘርፎች መካከል ግራፊክስ ጥበብ በምንለው ስር የሚካተት ሆኖ የራሱ የሆነ የአሰራ ሂደትን፣ ግብአትን፣ የተለያዩ የአሰራር ቴክኒኮችን በመጠቀም ተግባራዊ የሚደረግ ነው። ህትመት በባህሪው ብዙ አይነት ግብዓቶችን እና የአሰራር ዘዴዎችን በመጠቀም ከፍተኛ ትዕግስትን እና ጥንቃቄን በመተግበር ሀሳባችንን፣ ስሜታችንን፣ ልዩ ፈጠራዊ ተግባራቶችን የምናከናውንበት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ራሱን ከሰው ልጆች የአስተሳሰብ እድገት እና ፍላጎት ጋር በማዘመን በስፋት ተግባራዊ እየተደረገ ያለ የእይታ ጥበብ ዘርፍ ነው።

## የህትመት ታሪካዊ ዳራ

የህትመት ታሪካዊ ዳራን ስንመለከት ሙህራኑ በዚህ ዘርፍ በተለያያ ጊዜ እና ቦታ የፃፏቸው ፁህፎች፣ መላምቶች፣ ማጣቀሻ መፅሀፍት እንደሚጠቁሙት ረዘም ያለ ጊዜ ያለው እና ተመራጭ ጥበባዊ ዘርፍ መሆኑን በመደጋገም ይገልፃሉ።

የህትመት ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ በሙህራን እይታ በጥንታዊ ቻይናዊያን ከ206 ከክርስቶስ ልደት በፊትና እስከ 220 ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሀን በተባለ ስርወ መንግስት እንደተጀመረ የሚገልጹ እና ማስረጃ ለማቅረብ የሞከሩ ያሉ ሲሆን በስፋት ግን የህትመት ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ በርካታ የዘርፉ ሙህራን እንደሚስማሙበት ህትመት ለመጀመሪያ ጊዜ በተደራጀ እና በተሻለ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥንታዊ ግብፃዊያን ከ6ኛው እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተጀመረ ያስረዳሉ።

## የህትመት ምንነት

ህትመት ማለት አንድን ሊታተም የተፈለገን ነገር በሌላ ወረቀት፣ እንጨት ላይ ምስሉን ቀርፆ በማውጣት እና ቀለም በመቀባት ምስሉ እንዲያርፍ በተፈለገበት ቦታ ላይ በማጋጨት(በማላተም) እና በመደጋገም ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

## የህትመት አይነቶች

ተማሪዎች ህትመት ከግራፊክስ የእይታ ጥበብ ዘርፍ ውስጥ የሚመደብ እና በውስጡ በጣም በርካታ የሆኑ ዘርፎችን፣ የአሰራር ሂደቶችን፣ በርካታ ልዩ ልዩ ግብአቶችን በመጠቀም ተግባራዊ የሚደረግ ነው። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የህትመት አይነቶችን እንመለከታለን። የህትመት አይነቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ።


- የቀጥታ ህትመት
- ቅርፅ አውጥቶ ማተም

## ማስታወሻ፡-

ተማሪዎች፣ ህትመት የሚለውን ርዕሰ ጉዳይ በ5ኛ እና በ6ኛ ክፍል ላይ ተምራችኋል። በዚህ የክፍል ደረጃ ደግሞ በተወሰነ መልኩ ስለ ህትመት ምንነት እና ከህትመት መተግበሪያ ቴክኒኮች መካከል እስቴንስል ህትመት እና አስሮ ማቅለምን እንመለከታለን።

- ሌላው ሁሉም የህትመት አይነቶች የራሳቸው የሆነ ግብአት፣ የመስሪያ ስልት፣ የአሰራ መርህ፣ ቅደም ተከተልን በመጠበቅ ተግባራዊ የሚደረጉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

### 2.1.2.1 የስቴንስል ህትመትን በ3 የተለያዩ ቀለማት ማተም






ሥዕል 10 ሶስት እና ከዛ በላይ በሆኑ ቀለማት ስቴንስልን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል የሚያሳይ

### ለስቴንስል ህትመት አስፈላጊ ግብአቶች

- ወረቀት፣ እርሳስ፣ የጥርስ ቡርሽ፣ ወንፊት፣ ስፕሬይ
- መቁረጫ
- ቀለም
- መዳመጫ
- ጠረንጴንዛ
- ስፖንጅ፣ ብሩሽ፣ ጣውላ፣ ቁርጥራጭ

## የአሰራር ቅደም ተከተል

- በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰራውን ነገር ማሰብ፣ መምረጥ፣ መወሰን
- እንዲሰራ የተፈለገውን ሀሳብ በእርሳስ በወረቀት ላይ መንደፍ
- ከተነደፈው ንድፍ ላይ ተቆርጦ የሚወጣውን እና የማይወጣውን በመለየት በጥንቃቄ መቆራረጥ
- ስቴንስሉን ለማተም የምንፈልጋቸውን ሶስት የተለያዩ ቀለማቶችን ማዘጋጀት፣ በሚፈለገው መጠን ማቅጠን መበጥበጥ

**ማስታወሻ፡-**

የስቴንስል ህትመት በሶስት የተለያዩ ቀለማቶች ለማተም የተለያዩ አማራጮች አሉ።

1. ስቴንስሉ ሲዘጋጅ ሶስት የተለያዩ የስቴንስል ቅርፆችን ማዘጋጀት እና እንደቀለሙ አይነት በተራ መጠቀም
2. አንዱን የተዘጋጀችውን የስቴንሰል ቅርፅ በመጠቀም እየሸፈንን፣ እያፀዳን መስራት

- አንዱን የስቴንስል የተዘጋጀ ቅርፅ በመውሰድ ህትመቱ እንዲታተም በተፈለገበት ቦታ ላይ አስተካክሎ ማስቀመጥ፣ እንዲታተም ከተፈለገው ውጭ ያለውን መሸፈን
- ለህትመቱ ከመረጥናቸው ሶስት ቀለማት መካከል መጀመሪያ እንዲታተምበት የመረጥነውን በተገቢው በማቅጠን በስፖንጅ መቀባት
- በምንቀባበት ጊዜ ቀለሙን በስሱ በመጀመር እያስተካከልን መሄድ
- ለተወሰነ ጊዜ ደረቅ እስከሚል መጠበቅ እና ማንሳት
- በመቀጠል የተመረጠውን ሁለተኛ ቀለም እስቴንስሉ ላይ ለመቀባት መጀመሪያ ያተመነውን እና ቀሪውን ሶስተኛ ክፍል የታተመበትን ቦታ በስስ ወረቀት፣ በጋዜጣ መሸፈን እና ሁለተኛውን ስቴንስል በስፖንጅ በመቀባት ማተም፣ ትንሽ መጠበቅ እና ማንሳት
- በመጨረሻም ቀሪውን ሶስተኛ የተመረጠውን ቀለም እና ቀሪውን የስቴንስል ክፍል ለማተም አንደኛውን እና ሁለተኛውን በስስ ወረቀት፣ በጋዜጣ መሸፈን እና ቀለሙን በስፖንጅ መቀባት፣ ትንሽ መጠበቅ እና ማንሳት
- የሰራነውን ባለ ሶስት ቀለም የስቴንስል ህትመት በጥሩ ቦታ በማስቀመጥ ስራችንን መገምገም

**ማስታወሻ፡-**

ስቴንስል ስንል ሶስት እና ከዛ በላይ ቀለም ለማተም ከላይ ከተገለፀው ቴክኒክ በተጨማሪ

- በስፕሬይ፣ በጥርስ ብሩሽ በመጠቀም በወንፊት በመፈግፈግ (በማሸት) መተግበር
- በመዳመጫ (በሮለር) ወ.ዘ.ተ. ማተም ይቻላል።

### 2.1.2.2 አስሮ የማቅለም ብልሃት

አስሮ የማቅለም ብልሃት ህትመትን ከምናከናውንባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ እና ቀለል ባለ መንገድ የሚተገበር ነው። እንዲሁም በሰም እና በሻማ ማቅለም ዘዴን በመጠቀም በቀላሉ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

### የአሰራረር ቅደም ተከተል

- ጨርቅ ለመንከር እና ውሀ ለማሞቅ የሚያስችል ሰፋ ያለ ብረት ድስት ማዘጋጀት
- ውሀው ሲፈላ መጠነኛ የሆነ ቀለም፣ ጨው፣ ሎሚ ጨምቆ መጨመር
- ንፁህ ነጭ ጨርቅ ከጥጥ የተሰራ ማዘጋጀት በመቀጠልም ጨርቁን በሚፈለገው መጠን እና ይዘት በማጠፍ፣ በመጠምዘዝ በሲባጎ አለፍ አለፍ በማድረግ በጥንቃቄ አጥብቆ ማሰር
- ታስሮ የተዘጋጀውን ጨርቅ በሚፈላው ብረት ድስት ውስጥ መጨመር
- ከ40-50 ደቂቃ እየፈላ ባለው ቀለም ውስጥ በመጨመር እንዲፈላ ማድረግ፣ በእንጨት በተደጋጋሚ ቀስ ቀስ በማድረግ ማገላበጥ
- ከላይ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ሰፋ ባለ እቃ ውስጥ ቀዝቃዛ ውሀ ውስጥ በመጨመር እና እዛው ውስጥ ደጋግመን መንከር እና ማውጣት፣ የተቋጠረውን ገመድ መፍታት
- ገመዱ ከተፈታ በኋላ ጨርቁን በጥንቃቄ በመዘርጋት ፀሀይ ላይ እንዲደርቅ በማድረግ እና ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላ ውጤቱን መመልከት

**ማስታወሻ፡-**

አስሮ በማቅለም ሂደት ላይ የምናገኛቸው ዲዛይኖች እንደ ጨርቁ አስተጣጠፍ፣ አጠማዘዝ፣ አስተሳሰር ልዩነት ያመጣሉ።

የተለያዩ በርካታ ዲዛይኖች ከጨርቁ ላይ እንዲወጡ ለማድረግ በጨርቁ ላይ በጠጠር፣ በድንጋይ፣ እንጨት፣ የብረት ቁራጭ በማስገባት እና አብሮ በማሰር ወ.ዘ.ተ. ዲዛይኑን የበለጠ ሳቢና ማራኪ ማድረግ ይቻላል።

### ተግባር -2

ተማሪዎች በህትመት ዙሪያ የተማራችሁትን መነሻ በማድረግ የስቴንስል ህትመትን እና አስሮ የማቅለም ቴክኒክን መምህሩ(ሯ) በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በግል፣ በአናስተኛ ቡድን ሁለቱን የህትመት ቴክኖኮች በተደጋጋሚ በመስራት መለማመድ(ማወቅ) ይጠበቅባችኋል።

## 2.1.3 ኪነ ቅርፅ

ኪነ ቅርፅ ከስነ ጥበባት ዘርፎች መካከል አንዱ እና ቀደምቱ ነው። ጥንታዊው የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተለያየ ይዘት እና መጠን ልዩ ልዩ ሀሳቦችን እና መልዕክቶችን በተለያዩ ብልሃቶች ተደራሽ እየተደረገበት ይገኛል። ቅርፅ የሰው ልጅ ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ልዩ ልዩ ፈጠራዊ ተግባራቱን ለማከናወንና ለማሳየት የሚጠቀምበት የእይታዊ ጥበብ ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ የሰው ልጅ ጥበባዊ ተግባራቶችን ማሣያ ከማድረግ በተጨማሪ የሰው ልጅ አካባቢውን፣ ቤቱን፣ የእምነት ተቋማትን ለማስጌጥ፣ ለኑሮ ምቹ እና አስደሳች እንዲሆን ለማድረግ በስፋት እየተጠቀመበት ይገኛል። ኪነ ቅርፅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በርካታ የሆኑ የተለያዩ ግብአቶችን በመጠቀም ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

## ለኪነ ቅርፅ ተግባር በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውሉት ግብአቶች

ድንጋይ፣ እንጨት፣ እምነበረድ፣ መዳብ፣ ሸቦ የኪነ ቅርፅ ጭቃ፣ ሰም፣ ስሚንቶ፣ ጀሶ፣ ወረቀት ወዘተ በመጠቀም የሚዘጋጅ ሲሆን ቅርፅ ካለው ባህሪ እና ይዘት በመነሳት በዋናነት ሁለት ክፍሎች አሉት። እነሱም ባለ ሶስት አውታረ መጠን ይዘት ቅርፅ እና ሪሊፍ (ባለ ሁለት አውታር መጠን) ቅርፅ ናቸው።

### ባለ ሶስት አውታረ መጠን ይዘት ኪነ ቅርፅ

ይህ የኪነ ቅርፅ አይነት በባህሪው ቁመት፣ ርዝመት፣ ጥልቀት የሚያካትት ሲሆን የተሰራው ኪነ ቅርፅ በሁሉም የእይታ አውታሮች እተዟዟርን መመልከት እና መገንዘብ የሚያስችለን ነው። ለምሳሌ፡- ኪነ ቅርፅ ከፊት ለፊት፣ ከኋላ፣ ከጎን፣ ከላይ፣ ከታች ምን እንደሚመስል እና አጠቃላይ የኪነ ቅርፅ ይዘት በደንብ ለመረዳት ያስችላል።





ሥዕል 11 ባለሶስት አውታረ መጠን ይዘት ያላቸው የቅርፅ ስራዎችን የሚያሳይ

### ባለ ሁለት አውታር መጠን ኪነ ቅርፅ (ሪሊፍ)

ይህ የኪነ ቅርፅ አይነት በባህሪው ከፊት ብቻ የሚታይ (የኪነ ቅርፁን ከፊል ይዘት) ብቻ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ቁመት እና ርዝመትን ብቻ የሚያሳይ (የሚይዝ) ነው። ሪሊፍ ኪነ ቅርፅ ካላው ባህሪ በመነሳት ከአራቱ የኪነ ቅርፅ

መስሪያ ስልቶች መካከል ሞዴሊንግን እና ካርቪንግን በመጠቀም ተግባራዊ የሚደረግ ነው።





ሥዕል12 ባለ ሁለት አውታር መጠን ይዘት ያላቸው የኪነ ቅርፅ ስራዎች

**ተግባር**

ተማሪዎች ሪሊፍን በተመለከተ የተማራችሁትን ትምህርት እና ያገኛችሁትን እውቀት መነሻ በማድረግ እና የሪሊፍ ግብዓቶቹን፣ የአሰራር ስልቱን፣ የአተገባበር ሂደቱን በመጠበቅ እንደ እንጨት፣ ኖራ ድንጋይ፣ ሳሙና የመሳሰሉትን ግብዓቶች በመጠቀም በየግላችሁ ሪሊፍ ኪነ ቅርፅን ስሩ (ተለማመዱ)።

### 2.1.3.1 አራቱ መሰረታዊ የኪነ ቅርፅ መስሪያ ቴክኒኮች

ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው ኪነ ቅርፆችን ለመስራት ተግባራዊ የምናደርጋቸው አራቱ ስልቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ሞዴሊንግ
- ካርቪንግ
- ካስቲንግ
- አሰምብሊንግ

### ማስታወሻ፦

ተማሪዎች ከአራቱ የኪነ ቅርፅ መስሪያ ስልቶች ውስጥ ሌሎቹን በ5ኛ በ6ኛ ክፍል የተማራችሁ በመሆኑ የካርቪንግን ምንነት፣ የሚጠቀማቸው ግብዓቶች፣ የአሰራር ስልት በዚህ የክፍል ደረጃ ትማራላችሁ።

## ካርቪንግ

ከስያሜው ስንነሳ መቁረጥ፣ መጥረብ፣ መፈልፈል፣ መቦርቦር በጥቅሉ መቀነስ የሚለውን ሀሳብ እና ተግባር ያስረዳናል። ካርቪንግ ማለት ከኪነ ቅርፅ መስሪያ ብልሃቶች መካከል አንዱ ሲሆን ጠንካራ የሆነ ይዘት ያላቸው እና በቀላሉ ሊቆረጡ (ሊጠረቡ) የሚችሉ ግብአቶችን በማዘጋጀት ስለት ያላቸው ማቴሪያሎችን በመጠቀም በመቀነስ ስልት ብቻ በትዕግስት እና በጥንቃቄ የመቅርፅ ተግባር ነው።

የካርቪንግ ግብዓቶች፦ ለካርቪንግ ተግባር ብዙ አይነት ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ይዘት ያላቸውን ግበዓቶች የሚጠቀም ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። ድንጋይ፣ እንጨት፣ ሰም፣ ጀሶ፣ ሳሙና፣ ኖራ ድንጋይ፣ እምነ በረድ ወ.ዘ.ተ. ይጠቀሳሉ።





ሥዕል 13 በካርቪንግ ኪነ ቅርፅን ከእንጨት ላይ የማውጣት ተግባር (ስራ)

## ተግባር -3

1. ተማሪዎች ከላይ የምትመለከቷቸው ምስሎች ምንን ይገልፃሉ?
2. ከአራቱ የኪነ ቅርፅ መስሪያ ስልቶች የትኛውን ይወክላል? ለምን?

### የካርቪንግ የአተገባበር ሂደት፡-

- ምን መስራት እንደምንፈልግ ማሰብ፣ መምረጥ፣ መወሰን
- ለመስሪያ የሚሆን አመች ቦታ ማዘጋጀት
- ለካርቪንግ ተግባር ለመረጥነው ሀሳብ ማስፈሪያ (ድንጋይ፣ እንጨት፣ ሰም፣ ሳሙና) አንዱን በመምረጥ ለምሳሌ፡- ሳሙናን ብንወስድ የሳሙናውን የላይኛውን ገፅ ማስተካል፣ ማለስለስ በመቀጠል በእርሳስ ወይም በሌላ ለመንደፍ በሚያስችል ግብአት ካዘጋጀነው ሳሙና ላይ መንደፍ በመቀጠል ስለታማ ማቴሪያል (ከተር፣ ቢላዋ) በመጠቀም የንደፍነውን ንድፍ ሳንነካ ከንድፉ ውጭ ያለውን የሳሙናውን ክፍል እየቆራረጥን፣ እየጠረብን፣ እየፈለፈልን መስራት እና የተወሰነ የክፍታ ልዩነት እስከሚኖረው ድረስ በትዕግስት እና በጥንቃቄ መስራት በተጨማሪም የከፍታ ልዩነቱ በምንፈልገው መጠን መድረሱን ካረጋገጥን በኋላ ከዋናው የሪሊፍ ዲዛይን ላይ የምናስተካክለው ነገር ካለ በመጠኑ በመነካካት ማስተካከል እና መስራት በመጨረሻ ውጤቱን በመገምገም፣ አድናቆት እና ሂስ መስጠት።

**ማስታወሻ፡-**

ለካርቪንግ ተግባር የሚሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ የፈጠራ ሀሳቦችን ከምናየው፣ ከምንሰማው፣ ከምናስበው፣ ከተሰሩ ስራዎች ጭምር በመነሳት የሰው ገፀ ምስልን፣ ዕሐፎችን፣ ፊደላትን፣ ቁጥሮችን፣ የእንስሳት ምስልን፣ አዕዋፋትን መስራት እና ማጥናት ይቻላል።

ካርቪንግ በባህሪው አንድ አይነት የአሰራር ዘዴን ማለትም በመቀነስ ብቻ የሚሰራ በመሆኑ ከፍተኛ ትዕግሰት እና ጥንቃቄ በማድረግ የሚተገበር ነው። በተጨማሪም ከስለታማ ግብዓቶች እንደ ከተር፣ ምላጭ እና ቢላዋ የመሳሰሉትን በመጠቀም የሚተገበር በመሆኑ መድማት፣ መቆረጥ ስለሚያጋጥመን በጥንቃቄ

እና በማስተዋል መስራት አለባችሁ። እንዲሁም ስለታማ ነገሮችን በመዋዋስ ወይም በመቀባበል መስራት ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል ስለታማ ቁሳቁሶችን ከመዋዋስ እና በጋራ ከመጠቀም መቆጠብ ያስፈልጋል።

### ተግባር -4

ተማሪዎች ከአራቱ የኪነ ቅርፅ መስሪያ ስልቶች መካከል ካርቪንግን በተመለከተ ምንነቱን፣ ግብአቶቹን፣ የአሰራር ስልቱን እና የአተገባበር ቅደም ተከተሉን እና ሌሎች መሰረታዊ እና አስፈላጊ ነገሮችን ተምራችኋሀል (አውቃችኋል) ስለሆነም መምህሯ(ሩ) በሚሰጧችሁ መመሪያ እና በሚያቀርቡላችሁ ግብአት በአነስተኛ ቡድን፣ ጥንድ ጥንድ በመሆን በተደጋጋሚ በተግባር ስሩ (ተለማመዱ)።

## 2.2 የሙዚቃ ንባብ

የሙዚቃ ንባብ ጽንሰ ሀሳብን በ5ተኛና 6ተኛ ክፍል ተምራችኋል። በዚህ ርዕስ ደግሞ በትዝታና በባቲ ቅኝት የተፃፉ ዜማዎችን፣ ምትን አይቶና አዳምጦ መጫወትን ትማራላችሁ። በተጨማሪም በተለያዩ ቀላል የጊዜ ቆይታ የሚመሰረቱ ዜማዎችን አይቶና አዳምጦ መጻፍን ትማራላችሁ።

የጊዜ አመልካች ምልክቶች በሁለት ቁጥሮች የሚመሰረቱ መሆናቸውን በአምስተኛ ክፍል ተምራችኋል። የጊዜ አመልካች ቁጥሮች በሁለት ይከፈላሉ እነሱም ቀላልና ውስብስብ የጊዜ አቆጣጠሮች ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ የሙዚቃ ንባብን እንድተማሩ የሚፈለገው በቀላል የጊዜ አቆጣጠሮች የተፃፉ ምቶችንና ዜማዎችን ነው። የጊዜ አቆጣጠሮች የላይኛውና የታችኛው ቁጥር ትርጉም አሏቸው። የላይኛው ቁጥር በምድቡ (በባሩ) ውስጥ ምን ያህል ምት እንዳለ ይጠቁማል። የታችኛው ቁጥር ደግሞ የኖታውን አይነት (በአንድ ምት የምንጫወተውን የኖታ አይነት ይጠቁማል።

ምሳሌ፡- 4 → በምድብ (በባር) ውስጥ ምን ያህል ምት እንዳለ

4 → የኖታውን አይነት ወይም ዝርያን ያመለክታል

ከላይ የተቀመጠው ምሳሌ የሚያሳየው የላይኛው ቁጥር በአንድ ምድብ ውስጥ አራት ምት መኖሩንና የታችኛው ቁጥር ደግሞ አራት ሩብ ኖታዎች ወይም ከአራቱ ሩብ ኖታዎች የምት ዋጋ ጋር ሊመጣጠኑ የሚችሉ ኖታዎችና የእረፍት


ምልክቶች ይኖራሉ ማለት ነው። የሶልፌጆ ትምህርትን ለማስተማር በዋናነት ሁለት ክፍሎች አሉት። እነሱም

1ኛ የዕይታ ንባብ (sight reading)


2ኛ አዳምጦ መፃፍ (dictation) በመባል ይታወቃሉ

በተለያዩ የጊዜ አመልካች ቁጥሮች በስታፍ፣ በቦርድ ላይ ተጻፉትን የተለያዩ ኖታዎችን ትክክለኛየጊዜ ቆይታን ጠብቀን የምንጫወትበት ዘዴ እያዩ መጫወት ዘዴ ይባላል ከዚህ በታች የተቀመጡትን ማሳሌዎች ተለማመዱ


ምሳሌ-1 4 ምት በባር



ምሳሌ-2 3 ምት በባር



ምሳሌ-3 2 ምት በባር



## የተግባር ልምምድ አንድ

1. በተቀመጠው የጊዜ ቆይታ መሰረት እያንዳንዱን ባር ወይም ምድብ በማየት የጎደለውን ባር ሙሉ የሚያደርግ ኖታ ወይም የእረፍት ምልክት አሰቀምጡ




2. በተቀመጠው የጊዜ መለኪያ መሰረት የተጻፉትን ኖታዎችን በመመልከት በሩን/ምድቡን/ ለመከፈል ባርላይን ተጠቀሙ



3. የሚከተሉትን የጊዜ አመልካች ምልክቶች መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዳቸው አምስት አምስት ምድብ ወይንም ባር ሰርታችሁ አሳዩ

1. $\frac{4}{4}$
2. $\frac{2}{4}$
3. $\frac{3}{4}$

በጆራችን የምንሰማቸውን ድምጾች በማዳመጥ ወደ ሙዚቃ ኖታ ቀይረን የጊዜ አመልካች ቁጥሮች መሰረት በማድረግ በልሙጥ ወረቀት፣ በስታፍ፣ በቦርድ ወዘተ ምታቸውን ብቻ የምንጽፍበት ዘዴ ምትን አዳምጦ መጻፍ /Rhytimical dictation/ ይባላል።

## ምትን አዳምጦ የመፃፍ ተግባር

$\frac{4}{4}$ የጊዜ አመልካች ምልክትን መሰረት በማድረግ መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን ድምፅ ምቱን ብቻ አዳምጣችሁ ፃፉ?

$\frac{3}{4}$ የጊዜ አመልካች ምልክትን መሰረት በማድረግ መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን ድምፅ ምቱን ብቻ አዳምጣችሁ ፃፉ?


$\frac{2}{4}$ የጊዜ አመልካች ምልክትን መሰረት በማድረግ መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን ድምፅ ምቱን ብቻ አዳምጣችሁ ፃፉ?

ዜማን እያዩ ማንበብ የምንለው በሙዚቃ ስታፍ ላይ የተጻፉ ዜማዎችን እያየን ትክክለኛውን የጊዜ ቆይታና ድምጽን በመጠበቅ የምንጫወትበት ዘዴ ነው


## የተግባር ስራ ልምምድ ሁለት

1. ዜማን እያዩ ማንበብ ዘዴን በመጠቀም የትዝታ እና ባቲን ድምጾችን ደጋግማችሁ በማንበብ ተለማመዱ

ሀ.




-




ሐ.




መ.



ሠ.



ረ.



ዜማን ወይም ቃናን አዳምጦ መጻፍ ማለት ከሙዚቃ መሳሪያ ወይም ማንኛውም ዜማን በማዳመጥ ትክክለኛውን የጊዜ አመልካች በመጠቀም የሰማነውን ወደ ኖታ በመቀየር በስታፍ ላይ የምንጽፍበት ዘዴ ነው።

2. የሚከተሉትን በስታፍ ላይ የተጻፉትን ኖታዎች መምህሩ/ሯ/ ሲጫወት በመስማት ወደኖታ በመቀየር ጽፋችሁ አስቀምጡ


ሀ.



ለ.



ሐ.



## የተግባር ስራ ልምምድ ሦስት

**የእይታ ንባብ መልመጃ**



## የተግባር ስራ ልምምድ ሦስት

**የእይታ ንባብ መልመጃ**




## በትዝታ ቅኝት የተገነቡ ዜማዎችን ንባብ


ተማሪዎች ከዚህ በታች በትዝታና በባቲ ቅኝቶች ዜማዎችን ማንበብ ከመለማመዳችሁ በፊት ስለቅኝቶች በተወሰነ መልኩ እናያለን። ቅኝት ማለት በሌላ አገላለፅ ስኬል ሲሆን የሙዚቃ ድምፅ ቃና አወቃቀር ነው። በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የዜማ ቅኝቶች የምንላቸው ትዝታ፣ ባቲ፣ አንች ሆየ ለኔ እና አምባሰል ናቸው። እነዚህ ቅኝቶች ባለ አምስት የድምፅ ብዛት (ፔንታቶኒክ) ስኬል ናቸው ይሁን እንጅ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሙሉ በሙሉ በእነዚህ ቅኝቶች

ውስጥ የሚጠቃለል ነው ብሎ መደምደም አይቻልም በተጨማሪም የሞድ ስኬል ተያያዥነት የሜጀር እና የማይነር ባህሪ አላቸው።


የትዝታ አብይ (ሜጀር) ቅኝትን ለመመስረት በመጀመሪያ ከባለ ሰባት ድምፅ (ዲያቶኒክ ሜጀር ስኬል) እንደ መነሻ በመውሰድ መገንባት ይቻላል።ይህንን ቅኝት ከዲያቶኒክ ሜጀር ስኬል ከመረጥነው የስኬል አይነት አንዱን በመውሰድ ከመነሻው ድምፅ (ቶኒክ) ድምፅ ስንቆጥር የምናገኘውን አራተኛ እና ሰባተኛ ድምፅ ባለመጠቀም የምናገኘው የቅኝት አይነት ነው።

ምሳሌ፦ 1 ሲ ትዝታ አብይ ቅኝትን ለመመስረት


ሲ ዲያቶኒክ አብይ ስኬል




ከ ሲ ዲያቶኒክ አብይ (ሜጀር) ስኬል 4ተኛ እና 7ተኛን ሳይጠቀም ሲቀር ትዝታ አብይ (ሜጀር) ቅኝትን እናገኛለን። ከዚህ በታች የትዝታን አብይ ቅኝትን አመሰራረት ተመልከቱ።



## ሲ አብይ (ሜጀር) ትዝታ ቅኝት




4ተኛ 7ተኛ

በፒያኖ ላይ የተመሰረተ የትዝታ አብይ ቅኝት

## አንች ልጅ



## እኛም አለን ሙዚቃ




## በባቲ ቅኝት የተገነቡ ዜማዎች ንባብ

ባቲ አብይ ቅኝትን ለመመስረት በመጀመሪያ ባለ ሳባት ድምፅ (ዲያቶኒክ አብይ) ቅኝትን እንደ መነሻ በመውሰድ መገንባት ይቻላል። በተጨማሪም ይህ ቅኝት ከዲያቶኒክ አብይ ቅኝት ከተመረጠው የቅኝት አይነት አንዱን በመውሰድ ከመነሻው ድምፅ (ቶኒክ) ስንቆጥር የምናገኘውን ሁለተኛ እና ስድስተኛ ድምፅ ባለመጠቀም የምናገኘው ድምፅ ነው።

ምሳሌ፦ 1 ሲ አብይ (ሜጀር) ባቲ ቅኝትን ለመመስረት


ሲ አብይ (ሜጀር) ዲያቶኒክ ስከል







ከ ሲ ዲያቶኒክ አብይ (ሜጀር) ስኬል 2ተኛ እና 6ተኛን ሳይጠቀም ሲቀር ባቲ አብይ (ሜጀር) ቅኝትን እናገኛለን። ከዚህ በታች የባቲ አብይ ቅኝትን አመሰራረት ተመልከቱ



ሲ. ባቲ አብይ (ሜጀር)ቅኝት

### ሸግየ ሸጊቱ




## 2.3 ባህላዊ ውዝዋዜን መተግበር

በኢትዮጵያና በክልላችን የተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ባህላዊ ውዝዋዜዎች መኖራቸውን በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል። ከዚህ ቀጥሎ በቀርበው ቅደም ተከተልና አስተማሪያችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት ከክፍል ደረጃችሁና ከእድሜያችህ አኳያ ልትከውኑት በምትችሉበት አቅም ውዝዋዜዎችን ተግባራዊ እንድታደርጉ ይጠበቃል።

- በአካባቢው የተለመዱ ባህላዊ ዘፈኖችን በመለየት ለተማሪዎች የሚመቻቸውን መምረጥ
- ተማሪዎች ከ3-4 በቡድን በመመደብ።
- የተመረጠውን ባህላዊ ውዝዋዜ ከሙዚቃው ጋር በማዛመድ የመግቢያ እና የማሰጨፈረያ ስልቶችን በመጠቀም ልምምድ ማድረግ።
- በቡድን አመዳደብ ወቅት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በየቡድኖቹ እኩል መክፈል በተጨማሪም የወንድ እና የሴት ቁጥር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።
- ስልተ ምቱን በመከተል ባህላዊ ውዝዋዜውን ደጋግመው እንዲሰሩ ማበረታታት።
- ተመልካች ተማሪዎች ስለቀረበው ዝግጅት አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ።

➢በመጨረሻም የየቡድኖቹ ዝግጅት ካለቀ በሓላ ጥሩ ያቀረበውን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ለወደፊቱ የበለጠ ስራ እንዲሰሩ ማበረታታት።

## 2.4 የቴያትር እና የፊልም ጥበባት ሀሳቦችን ማፍለቅ

***የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች፦***

1. በአካባቢያችሁ የምትመለከቷቸው ፊልሞችና ድራማዎች መነሻ ሀሳባቸው በምን ጉዳዮች ዙሪያ እንደሆነ ተናገሩ።
2. በማህበረሰቡ ውስጥ የሚደረጉ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያለውን መደማመጥ፣ መግባባት፣ የስራ ድርሻና ቅደም ተከተልን መጠበቅ በዝርዝር አስረዱ።

በቴያትር እና በፊልም ጥበባት ላይ የሚዘጋጁ መሪ ፅሁፎችን የሰው ልጅ ለመፃፍ እና ለመተግበር ያደርገው የነበረው ጥባበዊ ፍላጎት ከፍተኛ ነበር። የቴያትር እና ፊልም ጥበባት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የተፃፉ ልዩ ልዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ለመጀመሪያ ጊዜ ለቴያትር መነሻ የሚሆኑ መሪ ፁህፎችን ማዘጋጀት እና መተግበር የተጀመረው በጥንታዊ ግሪካዊያን በ5ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚሁ ዘመን ከጥንታዊ ግሪካዊያን ማህበረሰብ ውሰጥ የወጡት የዘርፉ ባለሞያዎች በመነጨ ሀሳብ የቴያትር ፅሁፎችን እንደፃፉ የአራቱ ግሪካዊያን ፀሀፊዎች እና ስራዎቻቸው ያረጋግጣሉ። እነዚህ የቴያትር ፀሀፊዎች የጥንቱ ዘመን እሳቤ ጥበባዊ እሴቶችን ጨምሮ በትወና በማቅረብ እና የማህበረሰቡን ሕይወት የሚያንፀባርቁ ቴያትሮችን ሲሰሩ መቆየታቸው የቴያትር ጥበብ አሁን ለደረሰበት የእድገት ደረጃ ሚናቸው የጎላ ነው።

**ኤይስኪይለስ:-** ጥንታዊ ግሪካዊ ፀሀፊ ሲሆን ትኩረት ከሚያደርግባቸው ጉዳዮች በአብዛኛው አሳዛኝ ድርሰቶች (ታሪኮች) በመሆናቸው የትራጄዲ አፃፃፍ ሰልት አባት በመባልም ይታወቃል።

**ሶፎኪለስ:-** ከሶስቱ ጥንታዊ ግሪካዊያን ፀሀፊ ተውኔት መካከል የሚካተት ሲሆን ስራዎቹ ደግሞ ከኤይሲኪይለስ በመቀጠል የጀመሩ ነበሩ። ርዕሰ ጉዳዮቹም በአሳዛኝ ታሪኮች ዙሪያ ትኩረት ያደርጉ ነበር።

**ኢዮሪፒደስ:-** ከሶስቱ ጥንታዊ ግሪካዊያን ፀሀፊ መካከል የሚመደብ ሲሆን ስራዎቹም ትኩረት የሚያደርጉት በትራጄዲ (አሳዛኝ) ታሪኮች ዙሪያ ሲሆን

በህይወት ዘመኑም እስከ 25 የሚደርሱ ፁህፈ ተውኔቶችን እንደረሰ የዘርፉ ሙህራን ይጠቁማሉ።

አሪስቶፋኒስ:- አሪስቶፋኒስ የፊሊፐስ ልጅ ሲሆን የተውኔት ፅሑፍ ዘውጉ ደግሞ ቀልድ አዘል እና አስቂኝ ይዘት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። በህይወት ዘመኑ እስከ አርባ ሊደርሱ የሚችሉ ስራዎችን የሰራ ቢሆንም ከነዚህ መካከል አስራ አንዱ ስራዎቹ ተጠናቀው ለመድረክ (ለእይታ) የበቁ ናቸው።

ቴያትር እና ፊልም በውስጣቸው ብዙ የተለያዩ የጥበብ ዘርፎችን ያቀፉ የክውን እና እይታዊ ጥበብ ዘርፍ ናቸው። ለፊልም እና ቴአትር የሚሆኑ ሀሳቦችን ለማፍለቅ በርካታ ነገሮች ተጠቃሽ ሊካተቱ ቢችሉም በዋናነት ግን የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

- የማህበረሰቡን ወቅታዊ ሁኔታ እና ትኩረት የሚስቡ ጉዳዮች
- የማህበረሰቡ ማህበራዊ ህይወት የሚመለከቱ ሁኔታዎች
- የማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ (እሴቶች)
- የማህበረሰቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች
- የማህበረሰቡ እምነት እና ስልጣኔ
- የማህበረሰቡ ቀደምት እና የአሁን ታሪክ
- የማህበረሰቡ የጋራ የሆኑ እሴቶች መላላት
- የውጭው አለም ማህበረሰብ የአስተሳሰብ፣ የባህል፣ የእምነት፣ ቴክኖሎጅ ያሳደረው ተፅዕኖ
- በምንኖርበት አካባቢ እና አለም ውስጥ ከምናያቸው እና ከምናገኛቸው ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች መነሻ በማድረግ በቴያትር ድርሰት ውስጥ የተገነቡ ሀሳቦችን ይበልጥ ለማሳደግ በመቼት እና በሴራ ውስጥ መካተት ያለባቸው የህብረተሰቡን እምነት፣ ተስፋን፣ እውነትን፣ ክህደትን፣ ፍቅርን፣ ጥላቻን፣ ጀግንነትን፣ ታማኝነትን፣ ሀገር ወዳድነትን እና የመሳሰሉትን በማካተት ድርሰቱን የበለጠ ውጤታማ እና ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል።

በቴያትር እና በፊልም ዝግጅት ወቀት ዋነኛው ባለድርሻ ፀሀፊ ተውኔቱ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ለስራው መሳካት እና ውጤታማ መሆን የቴያትር ባለድርሻ አካላት በትብብር እና በመናበብ መስራት አለባቸው። እነዚህም ተመልካች፣

ተዋናይ፣ አዘጋጅ፣ የውበት ተውኔት ባለሙያ፣ ሌሎች አጋዥ አካለት ወ.ዘ.ተ. ትኩረት ሰጥተው ሲሰሩ ድርሰቱ ውጤታማ ይሆናል።

**ተግባር-**

**ተማሪዎች፣ ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚተገበር አጭር የድርሰት አፃፃፍ እና የትወና ልምምድ**

## ተስፈኛዋ ተማሪ

ዓለሚቱ በሰሜን ወሎ ዞን በመርሳ ከተማ መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸው ቤተሰብ ውስጥ የምትገኝ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን በትምህርቷ በጣም ጎበዝ ባህሪዋ ትሁት እና ሰው አክባሪ እንዲሁም ታዛዥ የሆነች ለቤተሰቦቿ 2ኛ ልጅ ነች። በምትማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ በበጎ አድራጎት እና በተለያዩ ክበባት እንቅስቃሴ በንቃት በመሳተፍ የምትታወቅ በመሆኗ በመምህሮቿ እና በክፍል ጓደኞቿ ዘንድ የተከበረች ናት። በመሆኑም ዓለሚቱ ከክፍል ጓደኞቿ ሀና እና አህመድ ጋር ሲያደርጉት የነበረውን ውይይት በቃለ ተውኔት ተፅፎ ቀርቦላችኋል። ይህንን ውይይት ካነበባችሁ በኋላ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን በድራማ መልክ አጥንታችሁ እና ተለማምዳችሁ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ተውናችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ዓለሚቱ: ሀኒ፣ አህመድ እንዴት ናችሁ? ዛሬ ከእረፍት በፊት የነበረው ትምህርት እንዴት ነበር?

ሀና: ደህና ነን። አንቺ እንዴት ነሽ? እረ የሆነ ነገር ያልገባኝ አለ።

አህመድ: እኔም በተመሳሳይ የሀናን ሀሳብ እጋራለሁ። አልሚ አንችስ ገብቶሻል?

ዓለሚቱ: እኔ በእየለቱ የምንማራቸውን ቀድሜ ስለማጠና እና በክፍል ውስጥ በንቃት ስለምከታተል አረሳሁትም። ለመሆኑ ለምንድን ነው ያልገባችሁ? ምክንያቱን አውቃችሁቷል?

ሀና: እረ በናትሽ አልሚ ትምህርቴን በአግባቡ መከታተል ስለማልችል እና ስለማላጠና ነው።

አህመድ፡ አልሚ ይገርምሻል ክፍል ውስጥ አስተማሪው ሲያስተምሩ መከታተል ስለማልችል ነው።

ዓለሚቱ፡ ተሳስታችኋል ስንፍና ጥሩ አይደለም።

ሀና እና አህመድ፡ አልሚ በናትሽ እባክሽን ጎበዝ መሆን እንድንችል ልምድሽን ንገሪን።

ዓለሚቱ፡ ካላችሁ እሺ። በመጀመሪያ ተምራችሁ ልትደርሱበት የምትፈልጉት ግብ ሊኖራችሁ ይገባል። ይህንን ለማሳካት ደግሞ የክፍል ደረጃ መቁጠር ሳይሆን ለስኬት ለመብቃት አስተማሪያችን የሚያስተምሩትን ትምህርት መከታተል እና ማጥናት አለባችሁ።

አህመድ፡ እሺ አልሚ መልካም ነው። አንቺ ግን ምን መሆን ነው የምትፈልጊው?

ዓለሚቱ፡ የእኔ ራዕይ የህክምና ዶክተር መሆን ሲሆን ይህን ለማሳካት በተከታታይ በፕሮግራም በማጥናት የሚሳካ መሆኑን አውቃለሁ። በመሆኑም እናንተም ራዕይ ሊኖራችሁ እና ጠንክራችሁ በማጥናት ጎበዝ ተማሪ እንደምትሆኑ ልትረዱ ይገባል።

ሀና፡ እኛም የመከርሽንን ምክር በመቀበል ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ጥረት እናደርጋለን። አይደለም እንዴ አህመድ?

አህመድ፡ አወ ሀኒ ትክክል ብለሻል በሉ ወደ ክፍል እንግባ የእረፍት ጊዜያችን ስላለቀ ተደወለ።

| ተ.ቁ | የምዕራፉ ይዘቶች | አሳክቻለሁ /አውቂያለሁ/ | አላሳካሁም /አላወኩም/ |
|---|---|---|---|
| 1. | የቀለም ቅብ እና የህትመትን ምንነትን | | |
| 2. | የቀለም ቅብ እና የህትመት ግብአቶችን፣ የአተገባበር ሂደቶቹን፣ የአሰራር ስልታቸውን | | |
| 3. | የተፃፉ ኖታዎችን፣ እርፍት ምልክቶችን እና ምቶቻቸውን መተግበር መቻልን | | |
| 4. | በትዝታ እና ባቲ ቅኝቶች ሙዚቃን ማንበብ (ሶለፌጆ) መቻልን | | |

## ማጠቃለያ

በምዕራፉ የቀረቡት የእይታዊ ጥበብ ይዘቶች ትኩረት የሚከተሉት ናቸው።

- ✍ በቀለም ቅብ ምንነት የሚካተቱ /የቅብ ቴክኒኮች፣ የቀለም አይነቶች፣ አስሮ ማቅለም/ በቅርፃ ቅርፅ ሪሊፍ ርእሶችን ያካትታል
- ✍ በህትመት ዙሪያ የተቀመጡ የህትመት አይነቶች አስሮ ማቅለም፣ ስቴንስል፣ ቀጥታ ህትመት እንዴት መተግበር እንዳለበት የያዘ ሲሆን

የሚሰሙ ዜማዎች የሚፃፉ የሚነበቡ መሆናቸውን መመልከት ተችሏል። ስለሆነም የተለያዩ የሙዚቃ ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶችን እንዲሁም በትዝታና በባቲ ቅኝቶች ላይ የተገነቡ ቀላል ዜማዎችን በሙዚቃ ንባብ ሂደት ዋና የሆኑትን የንባብ (ዜማ እና ምትን) የመጫዎት ስልቶች የእይታ ንባብ እና አዳምጦ መፃፍን በመጠቀም የመዘመር ተግባራትን አከናውናችኋል። ባህላዊ ውዝዋዜዎች እንደየአካባቢው ባህልና እውቀት መሰረት የተለያዩ ናቸው። እነዚህ የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ተግባራዊ ለማድረግ መሰረታዊ የሆኑ ቅደም ተከተሎች ያሏቸው መሆኑን ተምራችኋል።

የቴአትርና የፊልም ጥበባት አጀማመር የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው እና በሰው ልጅ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህል፣ በየጊዜው የሚፈጠሩ ወቅታዊ ጉዳዮች ወ.ዘ.ተ ሃሳቦችን እያነሱ ጥበባዊ እሴት በመጨመር ለማህበረሰቡ የሚቀርቡ ክውን ጥበባት መሆናቸውን ተገንዝባችሁዋል።

## የማጠቃለያ መልመጃዎች

**ትዕዛዝ አንድ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በ ሀ ረድፍ ለተዘረዘሩት ከ ለ ረድፍ ካሉት ተስማሚውን በመምረጥ አዛምዱ**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. ካርቪንግ | ሀ. በመፈግፈግ ቅብ ቴክኒክ የሚቀባ ነው |
| 2. ቻርኮል፣ ፓስቴል፣ ክራዮን | ለ. ከንጣት ወደ ጥቁረት ቅብ ብቻ የሚቀባ |
| 3. የውሀ ቀለም | ሐ. ለመድረቅ ረዥም ጊዜ የሚወስደው |
| 4. የዘይት ቀለም | መ. በመቁረጥ፣ በመፈልፈል የሚሰራ |
| 5. ህትመት | ሠ. በማጋጨት፣ በማላተምቴክኒክ የሚሰራ |
| 6. ሪሊፍ | ረ. ከፊት ለፊት ብቻ የሚታይ |

**ትዕዛዝ ሁለት፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ**

1.--------------- ተውኔቱን ለማራመድ በፅሀፊው የተፈጠሩ እና በድርሰት ውስጥ የሚኖሩ የድርጊት ውክሎች ናቸው።

2. በጭብጥ ተውኔት ውስጥ ምን ተባለ የሚለውን ካገኘን በ------------- ደግሞ ምን ተፈጠረ የሚለውን እናውቃለን።

**ትዕዛዝ ሶስት፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን ምላሽ ስጡ።**

1. መቼት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ
2. በ ጂ አብይ ስኬል ትዝታ ቅኝትን በስታፍ ላይ በሙሉ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ
3. በ 3 / 4 የጊዜ አመልካች ቁጥር አምስት ባር የተለያዩ ኖታዎችን እና የእረፍት ምልክቶችን በመጠቀም ፃፉ
4. በጊዜ አመልካች ቁጥር የላይኛው ቁጥር የሚያመላክተው ምንን ነው
5. በ ዲ አብይ ባቲ ቅኝትን በግማሽ ኖታ በስታፍ ላይ ደርድራችሁ አሳዩ
6. የእይታ ንባብ ማለት ምን ማለት ነው።



# ምዕራፍ 3

# ታሪክ እና ባህል

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- የስነ ጥበባት ባህላዊ እና ታሪካዊ አውዳቸውን ትረዳላችሁ፤
- በክልሉ የሚገኙ የሙዚቃና የሙዚቃ ባለሙያዎችን ታሪክና ስራዎቻቸውን ታደንቃላችሁ፤
- ለኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከቱ የሙዚቃ ባለሙያዎችን ትረዳላችሁ፤
- ሀገር በቀል የሆኑ የእደ ጥበብ ውጤቶች፣ ቀለም ቅቦች፣ የጥንታዊ ፅሑፎችን ልዩነት ታውቃላችሁ፤
- ሀገር በቀል እውቀትን በቴያትር እና በፊልም መግለፅ ትችላላችሁ፤
- የስነ ጥበባት ትምህርት ባህል እና ታሪክን ማቆየት እና ማስተማር የሚችሉ መሆናቸውን ትገነዘባላችሁ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የተካተቱት ይዘቶች ትኩረታቸው በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የሆኑ የእደ ጥበብ ውጤቶች ላይ ያሉ የቀለም ቅብ፣ የሸክላ ስራዎች እና ጥንታዊ የብራና ላይ ፅሁፎች የህብረተሰቡን እይታ እና ፍልስፍና፣ ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎችን ታሪክ እና ስራዎቻቸው፣ የተወዛዋዥ ባለሙያዎች፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን በቴያትር እና በፊልም የሚቀርቡበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው።

በመጨረሻ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ያሉት ባህላዊ ክዋኔዎችን አጥንታችሁ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ባህላዊ የሚዚቃ አይነቶች አመጣጣቸውን፣ ታዋቂ የሆኑ ሙዚቀኞች፣ ጥንታዊ ይዘት ያላቸው የተፃፉ ፅሁፎች፣ የቀለም ቅብ ስራዎች እና የሸክላ ስራ ውጤቶችን በመመልከት ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ እና ታሪካዊ አመጣጣቸውን መመርመር እና ማወቅ ተገቢ ነው።

## 3.1 የአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ

### የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች፦

***ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ ሀሳባችሁን ለመምህራችሁ ግለፁ።***

- ✍ በአማራ ክልል የሚገኙ ጥንታዊ ሙዚቃዎችን ተናገሩ።
- ✍ በአማራ ክልል ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎችን ዘርዝሩ።

የአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ ከአገሪቱ አጠቃላይ የሙዚቃ እድገት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በቅድሚያ ሀገር በቀል ከኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ አንፃር መመልከት ተገቢ ነው። ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላትና የራሷ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ባህሎች ያበለፀገች ሀገር መሆኗ ይታወቃል።

ታሪካዊ ከሆነው የባህል ቅርሳችን አንዱ የግዕዝ ቋንቋ ስነ ፅሁፍ በመሆኑ የሙዚቃ ታሪክ ከዚህ አንፃር መመልከቱ ተገቢ ነው። የግዕዝ ቅኔ ከጥንት ጀምሮ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው በምዕተ አመታት የሚቆጠር እድሜ ያለው ልዩ ስነ ፅሁፋዊ ቅርስ ነው። ይህ ቋንቋ ምጥንነቱ፣ ደምብና ስርዓተ ዜማው፣ ሰምና ወርቁ ወ.ዘ.ተ. የስነ ጥበቡን ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ይመሰክራል። ለዚህም በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓፄ ገብረ መስቀል የንግስና ዘመን የተነሳው ያሬድ በግዕዝ መፃህፍቱ ሚስጥር የተራቀቀ ሊቅ በመሆኑ ከመፅሀፍት ጠቅሶ ከራሱም ጨምሮ መዝሙሮችን ከነዜማቸው መድረሱን ታሪክ ይመሰክራል። እነዚህም የዜማ መፅሀፍት ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት የተባሉ ሲሆኑ ከተውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ እስካሁን ደርሷል። ከዚህ አንፃር የአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክን ስንመረምር ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በክልሉ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ብዙ የዜማ ስራዎች እንደሰራ እና በጣና ደሴት በሚገኘው ቅዱስ ቂርቆርስ ገዳም ለ3 አመታት እንዳስተማረ ታሪኩ ያስረዳል።

በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በላስታ ተነስቶ የነበረው አጼ ላልይበላ በክልሉ የሙዚቃ ታሪክ ሳናሰታውሰው አናልፍም። ይህ ንጉስ ዛሬም በዓለም የሚደነቁና ከአንድ ቋጥኝ የተቀረፁ ብዙ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ከማሳነፁም በላይ ለስነ ፅህፍ፣ ለሙዚቃና ለባህል እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል። በስሙም የሚጠሩ የዘማሪዎች ቡድን አቋቁሞ እንደነበር ይነገራል። በተጫማሪም በክልሉ ከቅዱስ ያሬድ በኋላ አያሌ ሊቃውንት ጥበቡን እያስተላለፉ መምጣታቸው ይታወቃል። እነዚህ የዜማ መፅሀፍት ከጥንት ጀምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ በክልሉ በሚገኙ መምህራን አማካኝነት ሲተላለፍ ቆይቷል። ከእነዚህም መምህራን መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. አባ ጊዮርጊስ ዘ ጋስጫ
2. አዛዥ ጌራ
3. አዛዥ ራጉኤል
4. አለቃ ገበረ ሀና እና ልጃቸው አለቃ ተክሌ ይገኙበታል።

ከላይ ባጭሩ ለመግለፅ እንደተሞከረው የአማራ ክልል ሙዚቃ ታሪክ ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ጀምሮ እንደነበረ ያስረዳል። በአንፃሩም በዚሁ ክፍለ ዘመን የዓለማዊ ሙዚቃ ተስፋፍቶ ነበር። እነዚህም አዝማሪዎች የመሰንቆ ተጫዋቾች እንደነበሩ ታሪክ ያስረዳል። ሀገራችን ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የሙዚቃ ቅኝቶችን እንደምትገለገል ይታወቃል። እነዚህ ቅኝቶች ትዝታ፣ ባቲ፣ አምባሰል እና አንች ሆየ ለኔ በመባል ይጠራሉ። እነዚህ ዛሬ በመላ አገሪቱ ጥቅም ላይ በመዋል የሚገኙ ቅኝቶች መሰረቶቻቸው እና ምንጮቻቸው አማራ ክልል መሆኑን ታሪክ ይናገራል።

የክልሉ ማህበረሰብ በእነዚህ ቅኝቶች መሰረት በማድረግ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ፍላጎቱን፣ እና ባህሉን በማዜም ከመጠቀም ባሻገር ለኢትዮጵያ የሙዚቃ እድገት ምንጭ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በጥንት በአማራ የሙዚቃ ታሪክ ወስጥ የምናገኛቸው የሙዚቃ ባለሙያዎች ከፍተኛ ሚና እና ተግባር የሚጫወቱት አዝማሪዎች እና ላሊበሎች ሲሆኑ እነዚህ የሙዚቃ ባለሙያዎች በወቅቱ በማህበረሰቡ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች ተቀባይነት ባይኖራቸውም ሙያውን ለማሳዳግ ከፍታኛ እሰተዋፅኦ ነበራቸው።

አዝማሪ ማለት አመሰጋኝ ነው። አዝማሪዎች በመጀመሪያ አነሳሳቸው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ወደ ዓለማዊ አገልግሎት በዋሉ ጊዜ ግለሰቦችን በማማሰገን እና በማዝናናት በሚገኝ አነስተኛ ስጦታ እና ገንዘብ ራሳቸውን ለማስተዳደር አስችሎቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ አዝማሪ የሚለው ቃል አሉታዊ ትርጉም ያለው መሆኑ እና እነዚህ ባለሙያዎችም አለም አጫዋች በሚል መጠሪያ ይታወቁ ነበር። ባሁኑ ወቅትም አለም አጫዋች፣ አዝማሪ፣ እንታንዣ፣ ቅሬ ወ.ዘ.ተ. በሚል መጠሪያ ስያሜ ሊጠሩ ይችላሉ። ይሄንን ሙያ ብዙውን ጊዜ ከቤተስብ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ (የተገኘ) ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግለሰቦች በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲሁም ሙያው በትምህርት እየተስፋፋ ይገኛል።

አዝማሪዎች የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ መሰንቆ ሲባል በጥንት ጊዜ ወንድ እና ሴት በመሆን ለሰርግ እና ለተለያዩ ክብረ በዓላት እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ከተሞች ሲስፋፉ ከትናንሽ የባህል ምሽት ክለቦች እስከ ትላልቅ ሆቴሎች የሙዚቃ ቡድን በመስራት ህዝቡን በማዝናናት እና በማስደሰት ላይ ይሰራሉ። በተጨማሪም በተለያዩ የኪነ ጥበብ ቡድኖች (ባንዶች) እና ቴያትር ቤቶች ውስጥም በቋሚነት ተቀጥረው እያገለገሉ ይገኛሉ። ቀደም ባሉ ጊዜያት የአገራችን ባህል ለውጭው አለም በማስተዋወቅ ሙያው አሁን ለደረሰበት ደረጃ ካበቁት ጥቂት የሙያው ባለቤቶች ውስጥ በዋናነት የሚታወቁት አሰፋ አባተ፣ ባህሩ ቃኜ፣ ደርባባው አቡን፣ አለማየሁ ፋንታ የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው። በዘመናዊ ባንድ አደረጃጀት ውስጥ ከሚታወቁት የባህል የኪነት ቡድኖች መካከል የወሎ ላልይበላ የኪነት ቡድንና በዘመናዊ የሙዚቃ ትምህርት ማስተማር ወ/ሮ ሰሂን ትምህርት ቤት፣ በጎንደር የፋሲለደስ የባህል ቡድን እንዲሁም በጎጃም የግሽ አባይ የባህል ቡድኖች ተቋቁመው በስራቸው በርካታ የሙዚቃ ባለሞያዎችን የያዙ ነበሩ።

ላልይበላዎች በአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። አብዝሀኛውን ጊዜ ወንድና ሴት ጥንድ በመሆን የሚንቀሳቀሱ ሲሆን እነዚህም ሞያተኞች ይሄንን ስራቸውን ከእምነት ጋር እንደሚያያዝ ይነገራል። ላሊበሎች ሞያውን በዘር የሚያስተላልፉ ሲሆን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቃሽና ምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያ የማይጠቀሙ ዜማውና የሙዚቃ ቃናቸው እጅግ በጣም የሚስብ ስሜትን የመግዛት ከፍተኛ አቅም ያለው ነው።

## 3.1.1 በአማራ ክልል የሚገኙ የሙዚቃ ባለሞያዎች የህይወት ታሪክ እና ስራዎቻቸው

ኢትዮጵያ የባህላዊና የዘመናዊ ሙዚቃ ውስጥ የአማራ ክልል የሙዚቃ ባለሞያዎች ከፍተኛና ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱ ናቸው። አሁን ለተደረሰበት የሙዚቃ እድገትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። በተለይም ከ1940ዎቹ ዓ.ም ጀምሮ ብዙ ዘመናዊ እና ባህላዊ የሙዚቃ ባለሙያዎች እያበቡ መጥተዋል። እነዚህ የክልሉን ማህበራዊ፣ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችን፣ ስነ ምግባርንና ፖለቲካዊ ህይወቱን በማንፀባረቅ የማህበረሰቡ መገለጫ ሆነው ቆይተዋል። በተጨማሪም እነዚህ ባለሙያዎች በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የክልሉን ባህል እና እሴቶችን ሲያስተዋውቁ የኖሩ ሲሆን ከዚህ በታች ክልሉ ካፈራቸው ባለሙያዎች መካከል ጥቂቶቹን ትመለከታላችሁ።


### ለማ ገብረ ህይወት

ለማ ገብረ ህይውት ከአባታቸው ገብረ ህይወት ወልዴ እና ከእናታቸው ወ/ሮ አማከለች ተክለ ሀይማኖት በአማራ ክልል በሴሜን ሸዋ ኮረማሽ በተባለ ቦታ በ1918 ዓ.ም ተወለዱ። እድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በመስኖ ማሪያም የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። አርቲስት ለማ የኪነት ባለሞያነት ህይወት ከ7 አመት የእድሜ ዘመናቸው ጀምሮ እየተገነባ እና እያደገ የመጣ ነው። የከተማውን ሕይወት ከመላመዳቸው በፊት አርቲስት ለማ ከመሰንቆ እና ከዋሽንት ጋር ለመዛመድ የቻሉት በተወለዱበት አካባቢ ነው። ሽለላ እና ፉከራውንም በልጅነት እንደበታቸው በጣፋጭ ዜማ ማንጎራጎር የጀመሩት ገና የ7 አመት እድሜ ልጅ ሆነው ነበር። በጣሊያን ወረራ ከአርበኛ ልጆች ተቀላቅለው አርበኞችን በሽለላ እና በፉከራ ሲቀሰቅሱ እና ሲያበረታቱ እንደነበር ይነገራል። ከድል ማግስትም በብሪትሽ አርሚ ውስጥ አዲስ አበባ በልጅ ወታደርነት ሲያገለግሉ ቆይተው በኋላም የክብር ዘበኛ ፈረሰኛ ሰራዊት ውስጥ እያሉ በአምስት አመት አገልግሎት በቆዩበት ወቅት ከማንጎራጎር እና ከመሰንቆ አልተለዩም ነበር። ‹‹አካሌ ውቤ›› በተሰኘው ዜማቸው በ1944 ዓ.ም በቀድሞው አዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት መድረክ የበቁት አርቲስት ለማ የመዲና ዜማ እና ግጥሞችን በመጫወት የመንፈስ ተሃድሶ እና ለጋሽ ብርቅየ የመድረክ ሰው መሆናቸውን አስመስክረዋል።

ለማ ከአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ወደ ቤሄራዊ ቤት ተዛውረው እስከ 1957 ዓ.ም ድረስ ባደረጉት የቆይታ ዘመናቸው የምንጊዜም ታሪክ የማይረሳቸው አያሌ ባህላዊ ዜማዎችን በራሳቸው ግጥም እና ዜማ አዘጋጅተው ተጫውተዋል። በመድረክ ብቻ ሳይወሰኑ ተከታዮቻቸውን ለማፍራት የሚጥሩ በመሆናቸው አብረዋቸው ሲሰሩ የነበሩ አርቲስቶች ይናገራሉ። መሰንቆ መጫወት የሚወዱ ሲሆን በተጨማሪም መለከት እና እምቢልታም መጫወት ይችሉ ነበር።

ቀረርቶ እና ሽለላ ሲነሳ በዚህ ሙያ ለረጅም ዘመን የታወቀውን ለማ ገብረ ሕይወትን በዘመኑ የነበሩ ሁሉ ያስታውሱታል። ለማ የተፈጥሮ ድምፁ ከፍተኛ ጉልበት ያለው በመሆኑ በሚያቅራራበት እና በሚሸልልበት ጊዜ ድምፅ ማጉያ አይጠቀምም ነበር። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴያትር ቤት ባልደረባ የነበረው ለማ ለተወሰኑ ዓመታት ያህል በቴያትር ቤቱ ከሠራ በኋላ “ለማና ጓደኞቹ” የተሰኘ የራሱን ድርጅት አቋቁሟል። በዚሁ ድርጅት አማካኝነት ለማና የሙያ ባልደረቦቹ አዝናኝ ዝግጅቶችን ለሃገር ጎብኚዎች እና ለሌሎች ታዳሚዎች አቅርበዋል። በአማራ ባህላዊ የሠርግ ጨዋታዎቹ የሚታወቀው ለማ በርካታ ሠርገኞችን በሙያው በማገልገልም ታላቅ አስተዋፅዎ አበርክቷል። “ኢዮሃ አበባዬ”፣ “እንቁጣጣሽ”፣ መዲና እና ዘለሰኛ ዜማዎች በአድማጭ ከተወደዱ ሥራዎቹ ውስጥ ይገኙበታል።

አርቲስቱ ባላቸው ችሎታ በሀገር ውስጥ ብቻ ተወስነው አልቀሩም በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በእስያ እና በአፍሪካ በተዘጋጁ ዓለም አቀፍ የሙዚቃ በዓላት (ፌስቲቫል) ላይ በመካፈል ሀገራችን ኢትዮጵያን ጥንታዊ ባህል እና ሙዚቃ ያላት ድንቅ እና ብርቅ ሀገር መሆኗን ለማሳየት ጥረት አድርገዋል። አንጋፋው የክልሉ የባህል ሙዚቀኛ አርቲስት ለማ በአጠቃላይ ለ59 አመታት በመድረክ ላይ ህይወታቸው በእንቅስቃሴ ካሰለፉ በኋላ ሚያዝያ 14 1987 ዓ.ም ስራቸውን ትተውልን አልፈዋል።



ሥዕል 1 ለማ ገብረ ሕይወት

## አሰፋ አባተ

ሁለ ገብ ከያኔ የመልካም ፍቅር ገጣሚ ኮከብ ድምፃዊ እና የመሰንቆ ሊቅ የሆነው አሰፋ አባተ ከአባቱ ከአቶ አባተ ዘለቀ እና ከእናቱ ከወ/ሮ ተወልደ ጉበና በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን ጉባላፍቶ ወረዳ ሳንቃ ቀበሌ ልዩ ስሙ በለስ በተባለ ቦታ በ 1927 ዓ.ም ተወለደ። እውቁ ድምፃዊ እና የመሰንቆ ሊቁ በ3 እና በ4 አመት እድሜው መዝፈን እና ማንጎራረጎር የጀመረ ልጅ እንደነበር ይነገራል። የሙያው ፍቅር ያደረበት በአካባቢው በሚኖርበት መንደር በሚዘጋጁ በዓላት ላይ በመገኘት በአጨዋወት ስልቱ እና በሚያሰማው ጣዕመ ዜማ ነበር። በህዝብ ዘንድም ተወዳጅነትን አትርፏል። በጊዜው የነበሩት የወሎ ገዥ አልጋ ወራሽ አሰፋው ወሰን ኃይለ ስላሴ ዝናውን በመስማት የግል የሙዚቃ ተጫዎች አድርገውት ይጫወት ነበር።

አሰፋ አባተ በ 14 አመት እድሜው በ1941 ዓ.ም በአቶ ባሻ ተክለ ማርያም አማካኝነት ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በሀገር ፍቅር ቴያትር ውስጥ ሰራ ጀመረ። ለብቻው ሲጫወት የሰውን ስሜት በቁጥጥር ስር የሚያደርግ ልዩ ተሰጥኦ ያለው ባለሙያ ሲሆን የመጫወት ችሎታው ከሌሎቹ የሙዚቃ ባለሙያዎች በጣም የተለየ እንደ ነበር ይነገራል። ይህንን የመሰንቆ አጨዋወት ዘዴን ያሻሻለው እና ያደባረው ከአንቱ ከቀኝ አዝማች ተሾመ ክብረት ነበር። አሰፋ አባተ መሰንቆን እንደ ቫይሎን ድምፅ አቅጥኖ የሚጫወት የመሰንቆ ጨዋታው ከሰውነቱ ጋር የተዋሀደ ብዙ ድንቅ ዜማዎችን እና ግጥሞችን የደረሰ እና የተጫወተ ዝነኛ ሰው ነበር። ከሚታወቅባቸው የሙዚቃ ስራዎቹ እና ዘፈኖቹ

መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ሸጊቱ
- የማትበላ ወፍ
- ፍቅሬ ትዝታየ
- ሸሞንሟናየ
- መኖር ተራርቆ ወ.ዘ.ተ የሚባሉት በሕይወት ዘመኑ የተጫዎታቸው ነበሩ። በተጨማሪም ልዩ ችሎታ ለዜማ እና ግጥም ፈጠራ የማይጨነቅ፣ ባየው ነገር ወዲያው ግጥም እና ዜማ የሚደርስ ሰው ነበር። ከስራዎቹ አብዛሀኞዎቹ የራሱ ፈጠራ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል።



ሥዕል 2 አሰፋ አባተ

## አስቴር አወቀ

አርቲስት አስቴር አወቀ በአማራ ክልል ውስጥ በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ሀሙሲት በምትባል አነስተኛ ከተማ በ1959 ዓ.ም ተወለደች። አስቴር በአንደኛ በትምህርቷ ጎበዝ እና ብዙ ሽልማቶችን ማግኘት የቻለች መሆኗን የልጅነት ታሪኳ ያስረዳል። አስቴር ወደ ሙዚቃው አለም የገባቸው ልጅ ሆና ገና በማንጎራጎር ላይ እያለች ነበር። እንዲሁም በህፃንነት እድሜዋ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ የሙዚቃ ችሎታዋን ማሳደግ ችላለች። የሙዚቃ ችሎታዋን ከፍ በማድረግ በሀገር ፍቅር ቴያትር ቤት በመጀመሪያ ከተቀጠረች በኋላ ብዙም ሳትቆይ በተለያዩ የግል የሙዚቃ ቡድኖች ስትጫዎት ቆይታለች። አስቴር ሙዚቃን እየሰራች ትምህርቷን አላቋረጠችም ነበር። ከሀገር ውጭ በ1981 ዓ.ም ወደ አሜሪካ በመጓዝ በሰሜን ቨርጅንያ በህብረተሰብ ኮሌጅ ኮምፒዩተር ሳይንስ ተምራለች። ከሀገር ውጭ እስከሄደችበት ድረስ እስካሁን የሰራቻቸው


የሙዚቃ ስራዎቿ የማይሰለቹ እና ጣዕም ያላቸው ጥልቅ ዜማዎችን ለህዝቡ በማቅረብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዝናን ከአተረፉ አርቲስቶች ተርታ ለመሰለፍ በቅታለች። አርቲስት አስቴር አውቀን ከሌሎቹ የሙዚቃ ባለሙያዎች ለየት የሚያደርጋት ነገር ቢኖር የሙዚቃውን ጥበብ ትምህርት በመማር የሀገራችንን የሙዚቃ ዘይቤ ከምዕራቡ አለም የሙዚቃ ስልት ጋር በማዋሀድ አዲስ የሙዚቃ ስልት በመፍጠር አገራችንን እና ባህሏን በአለም መድረክ ላይ በማስተዋወቅ የምትገኝ እና ዓለም አቀፍ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ በመሳተፍ ሽልማትን ያገኘች እውቅ እንስት ሙዚቀኛ ነች። ከስራቿ መካከል ካቡ፣ ጨጨሆ፣ የኔ ማርወለላ፣ እምየ እናቴ ወዘተ ይጠቀሳሉ።



ሥዕል 3 አስቴር አወቀ

## ባህሩ ቃኜ

ባህሩ ቃኜ ከቀደምት ባለሙያዎች አንዱ ሲሆን በመሰንቆ አጨዋወቱ በግጥም ድርደራው እጅግ የተደነቀ ነበር። ባህሩ የተወለደው በወሎ ክፍለ ሃገር ሲሆን በመሰንቆ አጨዋወቱ እና በግጥም አደራደር ችሎታው የተመሰገነ ከመሆኑ የተነሳ የልዑል አልጋወራሽ ልዩ አጫዋች በመባልም ይታወቅ ነበር። ባህሩ ቃኜ በዘመነ ደርግ በርከት ባሉ የምሽት መዝናኛ ቤት ውስጥ ይጫወት ነበር። ባህሩ ብዙ የቀድሞ ታሪኮችን የሚያውቅ፣ ቁጭ ብለው የሚደመጡ ለስላሳ ዜማዎችን በማቅረብ ልዩ ተሰጥኦ ያለው ታላቅ የሙዚቃ ሰው ናቸው። ከባህሩ ተወዳጅ ዜማዎች መካከል “አምባሰል”፣ “ተይ ማነሽ” እና “ትዝታ” ከራሄል ዮሃንስ ጋር የተጫወቱት ይገኙበታል።



ሥዕል 4 ባህሩ ቃኜ

## የክብር ዶክተር ማሪቱ ለገሰ

ማሪቱ በባቲ፣ በአምባሰል እና በአንችሆዬ ለኔ ቅኝቶች አጨዋወት ወደር ያልተገኘላት፣ የድምጿን ለዛ እና ውበት ጊዜ ያለወጠው ወሎ ያፈራት ምርጥ የባህል ድምፃዊት ነች። ማሪቱ የወሎ ላልይበላ ኪነት ቡድን ሲቋቋም ቡድኑን ተቀላቅላ ለወጣት ባለሙያዎች አርኣያ ልትሆን ችላለች። ከማሪቱ ስራዎች ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ዘፈኖች መካከል "አካሌ ውቤ"፣ "ዘራፌዋ" እና "ወለባ" በተባሉት ዜማዎቿም ትታወቃለች። በአሁኑ ጊዜ ኑሮዋን በአሜሪካ አድርጋ በተለያዩ ክፍለ ግዛቶች በመዘዋወር ልዩ የሙዚቃ ሥራዋን በማሳየት ላይ ትገኛለች። ፈገግታ የማይለያት ማሪቱ ትንሽ ትልቁን አክባሪ ባለሙያም ናት።



ሥዕል 5 ማሪቱ ለገሰ

## አሰፋ ደባልቄ

አሰፉ በወጣትነቷ የጎንደሩ የፋሲለደስ ኪነት አባል ነበረች። የጎንደርን ባህል የሚያንፀባርቁት ዜማዎቿ እጅግ ለዛ ያላቸው ናቸው። ወደ አዲስ አበባ መጥታ የመጀመሪያ ካሴቷን ባሳተመችበት ወቅት በአጭር ጊዜ ውስጥ በአድማጮች ዘንድ ለመታወቅ የቻለችውም በዚሁ የተነሳ ነው። “የሆዴን”፣ “የኔ አከላት” እና “ዙማዬ” የተሰኙት ዜማዎቿ ተወዳጅነትን ካስገኙላት ሥራዎቿ ጥቂቶቹ ናቸው። አሰፉ በአሁኑ ጊዜ ነዋሪነቷ በአሜሪካ ሲሆን በተለያዩ ክፍለ ግዛቶች እየተዘዋወረች የሙዚቃ ሥራዋን ታቀርባለች።




ሥዕል 6 አሰፉ ደባልቄ

## 3.2 የአማራ ክልል ውዝዋዜ ባለሙያዎች ታሪክ

የአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ ሲነሳ የማይታለፈው ጉዳይ የሙዚቃ ኪነቶች ታሪክ ነው። ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ በየአውራጃው እና በየቀበሌው እንዲሁም በየትምህርት ቤቱ የሙዚቃ ቡድኖች ተቋቁማው የተለያዩ የሙዚቃ እና ውዝዋዜ ስራዎች ይሰሩ ነበር። በመሆኑም በአማራ ክልል ውስጥ የሙዚቃን እድገት ከፍ ያደረጉ የተለያዩ የሙዚቃ ቡድኖች ቢኖሩም በክልሉ የውዝዋዜ ባለሙያዎችን በማፍራት የሚታወቁት ሦስቱ በክልሉ ተቋቁመው የነበሩት የኪነት ቡድኖች በግምባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። እነሱም የጎጃሙ ጊሽ አባይ፣ የወሎው ወሎ ላልይበላ እና የጎንደሩ ፋሲለደስ ናቸው።

የጎጃም ግሽ አባይ ኪነት ቡድን በ1970ዎች መጀመሪያ የተመሰረተ እና በጎጃም የሚገኙ የኪነ ጥበብ ፍቅር ያላቸውን ወጣቶች አቅፎ ይዞ የነበረ የኪነት ቡድን ነው። የኪነት ቡድኑ የጎጃምን ባህል የሚያንፀባርቁ እና የሚወክሉ በርካታ የሙዚቃ ስራዎችን የሰራ ሲሆን በዘፋኝነት ይሁኔ በላይ፣ ሰማኸኝ በለው የሚጠቀሱ ሲሆን በመሳሪያ ተጫዋችነት ሃብቱ ንጋቱ (አንሙት ክንዴ) የነበሩ ሲሆን በውዝዋዜው ሙያ ደግሞ የተለያዩ የጎጃም ባህላዊ ጭፈራዎችን እና ጨዋታዎችን ያስተዋውቁ ነበሩ።





ሥዕል 7 የግሽ አባይ ኪነት ቡድን ዘፋኝ ከነበሩት በከፊል





ሥዕል 8 የግሽ አባይ ኪነት ቡድን ተወዛዋዥ ከነበሩት በከፊል

የወሎ ላልይበላ ኪነት ቡድን በ1970 ዓ.ም የተመሰረተ በሃገራችን ከሚጠቀሱ ስኬታማ የባህል ቡድኖች አንዱ ነው። ‹‹የወሎ ላልይበላ ኪነት›› ቡድን ጥንስሱ የተጀመረው ከገጠር ወጥተው ከተማ ይኖሩ በነበሩ አዝማሪዎች ነው። እነዚህ አዝማሪዎች ኑሮን ከማቅለል አንፃር ህብረት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን

በማመን ‹‹የወሎ ተጫዋቾች ማህበር በሚል ስም ማህበር መሰረቱ። ከዚያ በኋላ ግን በወቅቱ በነበረው ‹‹ኪነት ለልማት›› በሚለው የመንግስት ሃሳብ መሰረት አንጋፋው የኪነ ጥበብ ሰው አቶ ቀለመወርቅ ደበበ ከአዲስ አበባ ተልከው ከማህበሩ አባላት እና ከማህበሩ ውጪም የተሻለ ችሎታ ያላቸውን የወሎ አካባቢ ሰዎች በመያዝ ኪነት ቡድኑን እንደገና አደራጅተውታል። ቡድኑ በስፋት የተንቀሳቀሰ እና በመላ ሃገሪቱ ስሙ ናኝቶ የነበረ ነው። ዛሬ ላይ ለኢትዮጵያ ምልክት የሆነችውን ማሪቱ ለገሰ፣ ዚነት ሙሃባው እና ዙሪያሽ አብዩ የወሎ ላልይበላ ኪነት ቡድኑ ፍሬዎች ናቸው። በተጨማሪም የወሎን ቱባ ባህል እና ባህላዊ ውዝዋዜን በመጫወት የአካባቢውን ማህበረሰብ ወጉን፣ ልማዱን እና ስነ-ቃሉን ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጉ ነበሩ። ይህ ቡድን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ፈርሶ የቆዩ ሲሆን አሁን ደግሞ ሙያተኞችን አሰባስቦ በማደራጀት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ እንደገና ስራውን ጀምሯል።



ሥዕል 9 ከወሎ ላልይበላ ኪነት ቡድን መካከል በከፊል






ሥዕል 10 ከወሎ ላልይበላ ኪነት ቡድን በተዋዛዋዥነት ሲሰሩ ከነበሩት በከፊል

የጎንደር ፋሲለደስ ቡድን ጎንደር እና አካባቢዋ ውስጥ በሚኖሩ የሙዚቃ ተሰጥኦ ባላቸው ወጣቶች የተመሰረተ የኪነት ቡድን ነው። የዚህ ቡድን መስራች አንጋፋው የኪነጥበብ ሰው አቶ ቀለመወርቅ ደበበ እንደሁኑ ይነገራል። የኪነት ቡድኑ በ1976 አካባቢ የተመሰረተ ሲሆን የኪነት ቡድኑ ዋሴ ካሳን፣ አሰፋ ደባልቄን፣ ታዋቂዋን የእስክስታ ንግስት እንዬ ታከለን እና ሌሎችንም ያፈራ የኪነት ቡድን ነው። አንጋፋው የባህል ሙዚቃ ተጫዋች ይርጋ ዱባለ የማህበሩ መስራች አባል ናቸው።



ሥዕል11 የጎንደር ፋሲለደስ ድምፃዊ ነበረ



ሥዕል 12 ከጎንደር ፋሲለደስ ተወዛዋገዮች መካከል በከፊል

## 3.3 የኢትዮጵያ ታላላቅ የሙዚቃ ባለሙያዎች እና ስራዎቻቸው

### 3.3.1 የቅዱስ ያሬድ የሕይወት ታሪክ

ሙዚቃ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ሲሆን ህይማኖት ደግሞ ለሙዚቃ እድገት ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ለኢትዮጵያ የሙዚቃ ጥበብ እድገት በየደረጃው አስተዋፅኦ ካበረከቱት ውስጥ የቅዱስ ያሬድ የዝማሬ ስራዎች ቀዳሚዎቹ ናቸው። በኢትዮጵያ የዜማ ታሪክ ውስጥ ከቅዱስ ያሬድ በፊት በለሆሳስ ከመፀለይ በስተቀር ስርዓት ኖሮት የተደራጀ ዜማ አልነበረም።

ያሬድ የሚለው ቃል ትርጉም እንዚራ፣ በገናና መሰንቆ የሚል ሲሆን እነዚህ የዜማ መሳሪያዎች ደስ የሚያሰኙ ናቸው። የያሬድ ዜማዎች ደስ የሚያሰኙና እንደ መሳሪያዎቹ ለዛና ጣዕም ያላቸው ናቸው። ሌላው ትርጉም ደግሞ ሚሰጥር ተመልካች ወይም ሚሰጥር ገላጭ የሚል ሲሆን በተጨማሪም ንብ

የሚል ትርጉም ያለው ነው። ንብ የተባለበት ምክንያት ንብ የማትቀስመው አበባ እንደ ሌለ ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ከቅዱሳት መፅሀፍት የማይጠቅሰው ነገርም የለም።

ታላቁ የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ ከአባቱ ይስሀቅ (አብዮድ) እና ከእናቱ ክርስቲና (ታውክሊያ) ሚያዚያ 5 ቀን 505 ዓ.ም በአክሱም ተወለደ። አባቱም የአክሱም ፅዮን ቄስ ገበዝ ሲሆን በዚያን ጊዜ የብሉይ እና የሀዲስ መምህራን ተማሪዎች የሚገኙት አክሱም ፅዮን ነበር። የአክሱም ቤተ ጉባኤ መምህር የነበረው የእናቱ ወንድም አጎቱ መምህር ጌዲዮን ይባል ነበር። ያሬድ የ7 አመት ህፃን በነበረበት ጊዜ አባቱ ስለሞተ ከአጎቱ ዘንድ መፅሀፍት ለመማር ሄደ። ትምህርቱንም በመቁጠር ጀመረ። ነገር ግን በትምህርቱ ደካማ ስለነበር ተስፋ ቆርጦ ከአክሱም ከተማ ወጥቶ ወደ እናቱ መንደር ተጓዘ። በጉዞውም ወቅት ስለ ደከመው ለጥሙ ከምንጭ ውሀ ጠጥቶ ለድካሙ ከዛፍ ጥላ ስር አረፈ። በምን ምክንያት ከጓደኞቹ በታች እንደሆነ እና ሲያስብ እና ሲያሰላሰል እንዲሁም ሲተክዝ ከቆየ በኋላ አንድ ነገር ከዛፍ አየ። ይኸውም አንድ ትል የዛፉን ፍሬ ለመመገብ ፊልጎ ወደ ላይ እወጣ እና እየወደቀ ተዳጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ በ7ኛው ጊዜ ወደ ዛፍ ወጥቶ ፍሬዋን ሲመገብ ተመለከተ። ተማሪ ያሬድም ከዚህ ትል መታገስን፣ መፅናት፣ ጥረትንና ስኬትን እንደ ትምህርት ወስዶ እኔም ተስፋ ሳልቆርጥ የተሻለ እሆናለሁ በማለት እንደ ገና ወደ መንበሩ በመመለስ ትምህርቱን ለመቀጠል ወሰነ። ከዚያም ትምህርቱን እንደገና በመጀመር ከሁሉም ተማሪዎች የተሻለ ሆነ። ብዙም አወቀ። መፅሀፍትን በቃሉ መያዝ በመቻሉ ለማወቅ ያደርግ የነበረውን ጥረት፣ ደግነቱን፣ ትዕግስቱንና ትህትናውን ተመልክተው መምህሩ ጎበዝና ጠንካራ መሆኑን መስክረውለታል። ትምህርቱን በስፋት አጠናክሮ በመቀጠሉ የብሉያት፣ የሀዲሳት እና የሊቃውንት ትርጓሜ ሊቅ ለመሆን በቅቷል።

ቅዱስ ያሬድ ሙራደ ቃል በተባለ ቦታ ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያዜም ንጉሱ ዓፄ ገብረ መስቀል ከነሰራዊቶቻቸው ንግስቲቱ ከነደንገጡሮቿ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ሊቃዉንቱና ካህናቱ እየመጡ ያዳምጡ ነበር ይላሉ ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሣ በመጽሐፋቸዉ።

ቅዱስ ያሬድ በግእዝ፣ በዕዝል በዓራራይ ዜማ ዝማሜ እየደረሰ እያለ ንጉሱ ዓፄ ገብረ መስቀል ተገኝተው ነበር። በዜማው ተመስጠው አይን አይኑን እያዩ እንደ እርሱ እዘማለሁ ብለው በያዙት የብረት ዘንግ ሳያውቁት ቅዱስ ያሬድ እግር

ላይ ቸከሉት። ሁለቱም በተመስጦ ስለነበሩ የሆነውን ነገር አላስተዋሉትም ነበር። ዜማው አብቅቶ ሁለቱም ከተመስጧቸው ሲነቁ የቅዱስ ያሬድ እግር ላይ ዘንጋቸው ተሰክቶ ብዙ ደም ፈሶት ነበር። ንጉሡም ደንግጠዉ እጅግም አዝነው ‹‹ደምህን አፍስሻለሁና የምትፈልገውን ማንኛዉንም ነገር ጠይቀኝ እሰጠሃለሁ›› ሲሉ ቃል ገቡለት። ቅዱስ ያሬድም ‹‹የምለምነዎት አንድ ነገር አለ እርሱን ይፈፅሙልኝ›› አላቸው። ‹‹የፈለከዉን ጠይቅ ፈቅጄልሃለሁ›› አሉት። እርሱም ‹‹እስካሁን እግዚአብሔር በፈቀደልኝ መሰረት በዚህ ከተማ ከእርሰዎ ጋር ቆይቻለሁ። ብዙ ደቀ መዛሙርትም ተክቼያለሁ። ከእንግዲህ በኋላ የቀረኝን ዘመን በጸሎትና በብሕትውና መኖር እንድችል ከከተማው ራቅ ወዳለ ቦታ ሔጄ ፈጣሪዬን ማገልገል እፈልጋለሁ›› ብሎ የንጉሱን ፈቃድ ጠየቀ።



## 3.3.2 የቅዱስ ያሬድ የዜማ አይነቶች

የያሬድ የዜማ አይነቶች ግዕዝ እዝል እና አራራይ በመባል በሶስት ይመደባሉ። እነዚህ የዜማ አይነቶች አንድ ድምፅ ከሌላኛው ድምፅ ያልተደባለቀ፣ ወጥ የሆነ ድምፅ አላቸው ሶስቱም የዜማ አይነቶች የተለያየ ትርጉም አላቸው። ምሳሌያቸውም የአካል የግብርና የስም ሶስትነትንና አንድነትን የሚገልፁ ናቸው።

1. **ግዕዝ፦** ማለት አንደኛ ወይም በመጀመሪያ የተገኘ ዜማ ማለት ነው:: በዜማነቱ ሲተረጎም ስልቱ የቀና ርቱዕ ቀጥ ያለ በጣም ጠንካራ እና ሀይለኛ ማለት ነው:: በዚህም የተነሳ ሊቃውንቱ ደረቅ ዜማ (ለዛው በቀላሉ የማይያዝ ብለው ይገልፁታል

2. **ዕዝል፦** ዕዝል የሚለው ቃል ታዛይ (ተደራቢ) ማለት ነው:: ይኸውም ከግዕዝ ጋር ተደርቦ የሚዜም ለስላሳ ዜማ ማለት ነው:: በባህሪው አሳዛኝ የሆነ ዜማ ነው::

3. **አራራይ፦** አራራይ ማለት የሚራራ ልዩ ጣዕም ያለውና ልብን የሚመስጥ ማለት ነው:: ከግዕዝ ቀጥሎ እንደሚጠራና ርህራሄ ያለው ሲሆን ግዕዝ ከእዝልና አራራይ ተጣምረው የሚዜም ሲሆን እዝልና አራራይ ግን በየትኛውም ቦታ ተጣምረው ሊዜሙ አይችሉም::



ሥዕል 13 ቅዱስ ያሬድ

## 3.3.2 የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶችና ትርጉማቸው

ቅዱስ ያሬድ ለዜማው መማሪያ የሚሆን የፊደል ቅርፅነት የሌላቸው ስምንት የዜማ ምልክቶችን አዘጋጅቷል። አምበርና አድርስ የተባሉት ሁለቱ የዜማ ምልክቶች ሲጨመሩ የምልክቶቹ ብዛት አስር ይሆናሉ። እነዚህ ሁለት ምልክቶች ከቅዱስ ያሬድ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደተጨመሩ ይነገራል። የዜማ ምልክት ማለት ዜማውን እንዴት ማዜም እንዳለብን ሊመራን፣ ሊያስረዳንና ሊያሳውቀን የሚችል ጠቋሚ ምልክት ነው።

**ድፋት፦** ማለት ድምፅንና አንገትን ወደ ታች እርግጥ አድርጎ ወይም ደፍቶ ትንፋሽን ወደ ሆድ ውስጥ በመመለስ ማዜም ማለት ሲሆን ከላይ ወደ ታች መውረድን ያመለክታል::

**ሂደት፦** ሳትቆም ሳታቋርጥ ምንም ነገር ሳትይዝ ሰተት ብለህ ሂድ ወይም አዚም ሲሆን

**ቅናት፦** በዜማው ቃል መጨረሻ ያለውን አንዱን ፊደል ይዘህ አንገትን ወደላይ በማቅናት ድምፅን እንቅ በማድረግ አዚም ማለት ነው።

**ይዘት፦** በፍጥነት ከዜማው ዘር አንዱን የፊደል ሆሄ ያዝ በማድረግ ማዜም ማለት ነው።

**ቁርጥ፦** ዜማው በሚዜምበት ጊዜ በመጠኑ በመቀነስ ትንፋሽን ወደ ታች በማመቅ እንደገና ድምፅን በማጋነን እና አገጭን ወደ ፊት በማድረግ አዚም ማለት ነው።


**ጭረት፦** ማለት በዜማው መካከል ያለውን ንባብ አንዱን ፊደል ጎተት ወይም ሳብ አድርገህ አንገትህን ወደ ላይ አቅንተህ አዚም ማለት ነው።

**ርክርክ፦** ማለት ረጅም የሆነውን ዜማ በላዩ ላይ ርክርኩን በመጨመር በረጅሙ አዚም ማለት ነው።

**ደረት፦** ማለት ደረትን ከፍ በማድረግ ፊት ለፊት ቀጥ ብሎ በጉልህ ድምፅ በጉሮሮህ አዚም ማለት ነው።

**ድርስ፦** ማለት የቃሉን መጨረሻ የሆነውን አንዱን ፊደል ሆሄ ያዝ በማድረግ ድምፅን ወደ ኋላ በመሳብ ዜማውን እስከ መጨረሻው ማዜም ማለት ነው።

**አንብር፦** ማለት አስምጥ አሳርፍ ማለት ሲሆን ያንዱን ዘር የመጨረሻ ሆሄ ያለምንም ተጨማሪ ድምፅ እና ርክርክ በማስቀመጥ (በማቆም) አዚም ማለት ነው።




ሥዕል 15 የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች

## 3.4 በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ አጀማመር

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ የተጀመረው ቀድሞ የክብር ዘበኛ ሰራዊት ይባል በነበረው ወታደራዊ ክፍል ውስጥ ነበር። ይህ የሙዚቃ ክፍል የተመሰረተው በ40ዎቹ የአርመን ወጣት ሙዚቀኞች ነው። የእነዚህ የአርመን ወጣቶች አመጣጥ በጊዜው የነበሩት ንጉስ ለጉብኝት ወደ እየሩሳሌም ተጉዘው በነበረበት ጊዜ የሙዚቃ እውቀት ያላቸውን የአርመን ወጣቶች ያገኛሉ። ንጉሱም ወጣት ሙዚቀኞቹ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የዘመናዊ ሙዚቃ ስራ እንዲጀምሩ አደረጉ። የአርመን ሙዚቀኞች በቀድሞው የክብር ዘበኛ ሰራዊት ውስጥ ገብተው በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ ጀመሩ:: ይህ የመጀመሪያውና በአርመኖች የተጀመረው የዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ ዋና ዓላማው ወታደራዊ የሰልፍ ሙዚቃ /ማርሾችን/ በመስራት ሠራዊቱን በሰልፍ እንቅስቃሴ ውበትና ድምቀት እንዲኖረው ማድረግ ብቻ ነበር። የንጉሱም ፍላጎትና ዓላማ ይሄው ነበር። ምንም እንኳን የንጉሱ ዓላማ አርመኖቹን የሰልፍ ሙዚቃን ብቻ ማሰራት ቢሆንም የአርመኖቹ ቦታ በኢትዮጵያውያን ወጣቶች መያዝና መተካት ነበረበት። ለዚህም ሲባል ኢትዮጵያውያንን በሙዚቃ ትምህርት ማሰልጠን ነበረባቸው።

ይህ የዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ እስከ ጠላት ወረራ ጊዜ ቀጥሎ በጠላት ወረራ ምክንያት ሲቋረጥ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ ለአሁኑ የዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ መሰረት ጥሏል። በአደረጃጀቱ ለየት ያለ በዚያው በታሪካዊው የክብር ዘበኛ ሰራዊት ስር እንደገና እንዲቋቋም ተደረገ። በዚህ ወቅት በሙያው እንዲሰማሩ የተደረጉት እንደ መጀመሪያው አርመኖች ሳይሆኑ ከጠላት ወረራ በፊት በዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ሙዚቃን ይማሩ የነበሩ የአገራችን ልጆች ናቸው።

ከ1935 ዓ.ም ጀምሮ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በሙዚቃ ሙያ ለመሰልጠን ፈቃደኛ እየሆኑ ይቀጠሩ ጀመር ይህ በዚህ እንዳለ በ1938 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው የዘመናዊ ኦርኬስትራ በዚሁ በክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ተቋቋመ።

ኦርኬስትራው ሲቋቋም በችሎታቸው ላቅ ያሉ በስነ ምግባራቸው የተሻሉ ወጣቶችን ከሰልፈኛው የሙዚቃ አባላት መካከል ተመርጠው ብዙም ጊዜ ሳይወስድ የተለያዩ የዘመናዊ የሙዚቃ ቡድን በማቋቋም የውጭ አገር ሙዚቃ ስራዎችን ጭምር መጫወት ቻሉ። በቤተ መንግስትና በታላላቅ ሆቴሎችም

እየተጋበዙ ዘመናዊ ሙዚቃን ይሰሩ ጀመር።በአብዛኛው የሚሰሩት ስራዎች የውጭ አገር ሙዚቃዎች ይሁኑ እንጂ አልፎ አልፎ የአገር ውስጥ ዜማዎችን በሙዚቃ መሳሪያ ብቻ ለህዝብ ያሰሙ ነበር። በኖታ ተፅፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ ጆሮ የቀረበው ‹‹ አንቺ ልጅ ›› በመባል የሚታወቀው ሙዚቃ ሲሆን በኖታ የፃፈውና ያቀነባበረው በዳግምዊ ምኒሊክ ት/ቤት የሙዚቃ ዕውቀት ቀስሞ ወደ ክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል እንዲመደብ የተደረገው የመቶ አለቃ እሸቴ መኮንን ነበር።

በዚህ ኦርኬስትራ ውስጥ ሲያገለግሉ ከነበሩት እውቅ ድምፃውያን መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል። እነሱም፦ አስካለ ብርሀኔ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ ተፈራ ካሳ፣ እሳቱ ተሰማ፣ ተዘራ ኃይለ ሚካኤል፣ ኑሩ ወንዳፍራሽ እንዲሁም ዘግየት ብሎ የተቀላቀለው ጥላሁን ገሰሰ ይገኙበታል።

በኢትዮጵያችን የዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ የተጀመረው በቀድሞው የክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ይሁን እንጂ በተለይም ከጠላት ወረራ በኋላ የቀድሞው የምድር ጦር፣ የባህር ኃይል፣ የፖሊስ ሠራዊትና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴያትር ቤት /የአሁኑ ብሄራዊ ቴያትር/ ሙዚቃ ክፍሎች ተመስርተው ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል።

እንዲሁም በአገራችን በ1938 ዓ.ም የተመሰረተው የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት የሙዚቃ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች በማሰባሰብ በዘመናዊ የሙዚቃ አሰለጣጠን ዘመናዊ የሙዚቃ ዕውቀት ይዘው እንዲወጡ በማድረግ ለአገራችን የዘመናዊ ሙዚቃ እድገት ያደረገው አስተዋፅዖ ከፍተኛ። እንዲሁም በአሁኑ ሰዓት በዘመናዊ መልክ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ቴያትር ቤቶች እና ወታደራዊ ክፍሎች ሲኖሩ አንዳንድ ጀማሪ የሙዚቃ ቡድኖችም በዘመናዊ የሙዚቃ እንቅስቃሴ ስራ ውሰጥ ይገኛሉ።



## ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በአዲስ አበባ 1930 ዓ.ም ተወለዱ። አባታቸው ግራዝማች ከበደ አድነው ሲሆኑ ከልጅነታቸው ጀምሮ የሙዚቃ ስሜት እና ፍቅር ያሳደሩባቸው እናታቸው ወይዘሮ ፋንታዬ ነከሬ ነበሩ። አያታቸው ሊቀመኳስ አድነው ጎሹ ደግሞ የአድዋ አርበኛ እና የንግስት ዘውዲቱም ታማኝ አማካሪ እንደነበሩ ይነገራል። እናታቸው የሙዚቃ ፍቅርን በልጅነታቸው ያሳደሩባቸው ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳሉ ነበር። መሰረታዊ ትምህርታቸውን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እና በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮከበ ፅባህ) ካጠናቀቁ በኋላ በሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተመርቀዋል። ከፍተኛ ትምህርታቸውን ደግሞ በኒዮርክ ክፍለ ሀገር ከሚገኘው የሮቼስተር ዩኒቨርሲቲ ኢስት ማን የሙዚቃ ትምህርት ቤት በ1954 ዓ.ም በመጀመሪያ ዲግሪ ከተመረቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን መስርተዋል።

በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ እውቀት ላይ የተመሰረተ የሙዚቃ ትምህርትን እስከ ሦስተኛ ዲግሪ (ዶክትሬት) ድረስ በመማር የሙዚቃ እውቀት ጥግ የደረሱ ሰው ነበሩ። በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የሙዚቃ ሳይንስ ትምህርት የሚሰጥበትን የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት እንዲመሰረት በማድረግ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከቱ እና የመጀመሪያው የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የነበሩ ናቸው። ፕሮፌሰር አሸናፊ የባህል ሙዚቃ ተመራማሪ (Ethnomusicologist)፣ የሙዚቃ አቀናባሪ፣ መራሔ ሙዚቃ (conductor) እና የመፅሃፍት ደራሲም ነበሩ። በዚህ ታላቅ ሙያው በተለያዩ የአሜሪካ ሙዚቃን የሚያስተምሩ የኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች ባአስተማሪነት እና በተመራማሪነት

አገልግለዋል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ ትምህርት እንዲጀመር፣ የሙዚቃ ባህል እንዲጠና እና በአጠቃላይ የሙዚቃው እድገት ላይ ከፍተኛውን አሻራ ካሳረፉ የሙዚቃ ሙህራን መካከል ቀዳሚው ነበሩ።

ካበረከቷቸው ጉልህ ስራዎች መካከል የጥቁር ህዝቦችን ሙዚቃ ታሪክ እና ባህልን የሚያወሳው ‹‹Roots of black music›› የተሰኘው መጽሐፍ እና ከፍተኛ እውቅናን ያስገኘለት ስራቸው በ1953 ዓ.ም በሀንጋሪ የቀረበው ‹‹ባለዋሽንቱ እረኛ›› (The Shepherd flutist) እና በርካታ የሆኑ ጥናትና ምርምሮችን በኢትዮጵያ ሙዚቃዎች ላይ አድርጓል። ፕሮፌሰር አሸናፊ ግምቦት 1 ቀን 1990 ዓ.ም በ60 ዓመቱ ሲኖርበት በነበረው በአሜሪካ ፍሎሪዳ ውስጥ አልፈዋል።



ሥዕል 15 ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ


## በሻህ ተክለማርያም

ለኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት መሰረት ከጣሉት ሰዎች መካከል በሻህ ተክለማርያም አንዱ ተጠቃሽ ናቸው። በሻህ ተክለማርም ትውልዳቸው ቡልጋ ከሆነው ከአባታቸው ከግራዝማች ተክለማርያም አጥናፉ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ የሺ.ወርቅ ተክለፃዲቅ በ1904 ዓ.ም በመጋቢት ወር ቀድሞ ባሌ ክ/ሀገር ተብሎ በሚጠራው ጎባ ከተማ ተወለዱ።

እድሜያቸው ስምንት አመት ሲሞላ በመጀመሪያ ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ቀጥሎም የቀድሞው ተፈሪ መኮንን ት/ት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን

የተከታተሉ ሲሆን በዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት እያሉ በአርመናዊው የሙዚቃ መምህር ነርሲስ ናልቫንዲያን ዘመናዊ የሙዚቃ ት/ት ሲጀምሩ ቫዮሊንና ፒያኖ የተባሉትን አለም ዓቀፍ የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጫወት ችለዋል። እኚህ ታላቅ የሙዚቃ ባለሙያ የሶስቱን አመት የሙዚቃ ትምህርት በአንድ አመት በማጠናቀቅ በተማሩበት ት/ት ቤት የሙዚቃ መምህር መሆን ችለዋል።ኢትዮጵያ ሃገራችን በጠላት በተወረረች ጊዜ ይህንን የውጭ ጠላት ለመዋጋት ወደ ቡልጋ ገብተው ጠላት ሀገራችንን ለቆ እስኪወጣ ድረስ በዚሁ ቦታ በመዋጋት የቆዩ ሲሆን ጠላት ከወጣ በኋላ በትምህርት ሚንስቴር ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ያሬዳዊውን የሙዚቃ ምልክት ከአውሮፓውያን የሙዚቃ ምልክት ጋር አቀናጅተው አለማቀፋዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እያሉ የሀገር ፍቅር ማህበር ቲያትር ቤት ተቋቁሞ ስለነበር ከየካቲት 2 ቀን 1934 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ቲያትር ቤት መስራት ጀመሩ።

በሻህ ተክለማርያም የመጀመርያው የህገረሰብ የሙዚቃ ቡድን በማቋቋም ክራርን ቀደምት ባለሙያዎች የሚጫወቱት በግርፍ ብቻ ስለነበር ‹‹ድርድር›› የተባለውን የክራር አጨዋወት ዘዴ በመፍጠር በተጨማሪም መሰንቆ የተባለውን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በተለየ ፈጠራ በሁለት ዓይነት አሰራር በመጠቀም እናት መሰንቆ በመቆም የሚጫወቱት በጣም ትልቅ ሆኖ /ቤዝ/ ወፍራም ድምፅ የሚያወጣ አድረገው በመስራት ለባህል የሙዚቃ ቡድን እንዲያገለግል አድርገዋል።



ሥዕል 16 በሻህ ተክለማሪያም ቫዮሊን ሲጫወቱ

እኚህ የሙዚቃ ባለሙያ ማራካሽ የተባለውን የምት የሙዚቃ መሳሪያ በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ያዘጋጁ እና በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን በኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎች የተቀናበረውን ኢትዮጵያዊ የህገረሰብ የሙዚቃ ቡድን /ኦርኬስትራ/ አቋቁመዋል።

በሻህ ተክለማርያም በ1953 ዓ.ም የአገራችንን ባህል ለማስተዋወቅ የሙዚቃ ቡድኑን በመምራት በቀድሞ ሶቪየት ህብረት /ሞስኮ/ እንዲሁም ወደ ቻይና በመሄድ ባህላችንን በጊዜው አስተዋውቀዋል። በአሁኑ ጊዜ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነውን ‹‹ሙሽራዬ›› የተባለውን የሰርግ ዘፈን ግጥም እና ዜማ በማውጣት ለህዝብ ያበረከቱ ሰው ናቸው።

በሻህ ተክለማረያም በ1967 ዓ.ም በጡረታ ተገልለው ህይወታቸውን ሲመሩ ቆይተው ሐምሌ 6 ቀን 1987 ዓ.ም አርፈዋል። ዛሬ በአገራችን በሚገኙ ቴያትር ቤቶች እና የኪነ ጥበብ ተቋማት ለሚጎርፈው የተቀናበረ የህገረሰብ ሙዚቃ የመጀመሪያውን ዘር የዘሩት እኚህ የኪነ ጥበብ ሰው ታላቅ ባለውለታ ናቸው።



ሥዕል 17 በሻህ ተክለማሪያም ያሻሻሉት እናት መሰንቆና የባህል መሳሪያ ቡድን

### ተግባር-1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልስ ስጡ።

1. የቅዱስ ያሬድ ስራዎችን በመዘርዘር የስኬቱን ምክንያቶች ተናገሩ።
2. በሻህ ተክለማሪያም ለሀገር ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ለይታችሁ ከተወያያችሁ በኋላ ከታሪኩ የተማራችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
3. የፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ታሪክን አጭር ፅሁፍ በማዘጋጀት አቅርቡ።
4. ለኢትዮጵያ የሙዚቃ እድገት አስተዋፅዖ ያበረከቱ ሌሎች የሙዚቃ ባለሙያዎችን ታሪክ አጭር ሪፖርት አቅርቡ።

## 3.5 የኢትዮጵያ ታላላቅ የእይታዊ ጥበብ ባለሙያዎች

ዘመናዊ የአሳሳል ዘይቤ በሃገራችን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለውጥ ማምጣት የቻሉና የተለያዩ የአሳሳል ዘይቤዎችን ያስተዋወቁ፣ ያስተማሩ በርካታ የእይታዊ ጥበብ ሰዎች ተፈጥረዋል። ከእነዚህም ውስጥ ስዓሊ አገኘሁ እንግዳ፣ አፈወርቅተክሌ፣ ገብረክርስቶስ ደስታ፣ ሻንበል ለማ ጉያ፣ እስክንድር ቦጎሲያን፣ ዘሪሁን የትምጌታ፣ ጌታቸው ዮሴፍ፣ አለ ፈለገሰላም፣ እሸቱ ጥሩነህ፣ ታደሰ መስፍን፣ ታደሰ በላይነህ፣ በቀለ መኮነን፣ መዝገቡ ተሰማ፣ ደስታ ሀጎስ፣ እመቤትአወቀ፣ ወ.ዘ.ተ.ይገኙበታል።

በዚህ ርዕስ ላይ የስዓሊ አገኘሁ እንግዳን፣ የሻምበል ለማ ጉያን፣ የአፈወርቅ ተክሌን ና የገብረክርስቶስ ደስታን ታሪክና ስራዎቻቸውን እንመለከታለን።



### ሰዓሊ አገኘሁ እንግዳ

ሰዓሊ አገኘሁ እንግዳ በ1905 ዓም በጎንደር በማጎደረ ማርያም ተወለዱ። በቀደሞው ዘመን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለትምህርት ወደ ውጭ

ከላኳቸው ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ነበሩ። ፈረንሳይ ሀገር በመሄድ የስዕልን ጥበብ ተምረው ከመጡ በኋላ የኢትዮጵያ የብር ኖቶች ላይ የሚገኙትን የስዕል ዲዛይኖች፣ በቀድሞው ፓርላማ ውስጥ የሚገኙ ስዕሎች እና የተለያዩ የአብያተ ክርስቲያናት የግድግዳ ሥዕሎች በመሳላቸው ይታወቃሉ። ቀዳማዊ ሀይለስላሴ በ 1924 ዓም በአዲስ አበባ ከተማ ቅድስት ስላሴ ለሀገር በጎ ያደረጉ ሰዎች መካነ መቃብር ይሆን ዘንድ ሲያሰሩ፣ የካቴድራሉን ስዕል የሳሉት ሰዓሊ አገኘሁ እንግዳ ናቸው። የተለያዩ የስዕል ኤግዚብሽኖች በማቅረብ በወቅቱ ዝናን አትርፈዋል። ሰዓሊ አገኘሁ እንግዳ በ1941 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ዘርፍ ውስጥ የስነ ጥበባት ማዕከል አስተባባሪ ሆነው ሰርተዋል። የመጀመሪያዉ የኢትዮጵያ የዘመናዊ ሰዓሊ አቶ አገኘሁ እንግዳ፣ ከስዕል ተሰጥኦቸው በተጓዳኝ በገና ደርዳሪና ገጣሚ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። ከቀዳሚዎቹ አውሮጳ ቀመስ ሥነ ሥዕልን ከያዙ፣ የኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ሠዓልያን መካከል ተደናቂ የሚኾኑት ሠዓሊ አገኘሁ እንግዳ ናቸው። ብቸኛው የብር ኖት ላይ ሥራቸውን ያሳረፉ ኢትዮጵያዊ ሠዓሊ ነበሩ። በሥራዎቻቸው ረቂቃዊነትንና ዘመናዊነትን አዳብለው ቢሠሩም "ፍፁም ኢትዮጵያዊነትን " የተላበሱ ሥዕሎችን በስፋት ሰርተዋል።




ሥዕል18 ከሰዓሊ አገኘሁ እንግዳ ስራዎች በከፊል

አገኘሁ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የነበሩበት በመኾናቸው፣ በመንግሥት ነፃ የትምህርት ዕድል በማግኘት፣ ለሥዕል ትምህርት ወደ ፈረንሳይ ተላኩ። በፓሪስ በሚገኘው ኤኮል ናሲዮናል ሱፔርየ ዴ ቢው ገብተው፣ ለስምንት ዓመት ያኸል ሥነ ጥበባትን ትምህርታቸውን እስከ 1925 ዓ.ም ድረስ ተማሩ። ወደሀገራቸው በመመለስ ብዙ የሥዕል ትርኢቶችን አሳይተዋል። የወታደር መለያ አልባሳትን፣ የወረቀት ብሮች ንድፎችን፣ የቤተ ክርስትያን ሙራሎችን እና የብዙ እውቅ ባለታሪኮችን ምሥሎች፣ የራስ ምሥል፣ አስቴር መንገሻ ስራዎችን ሰርተዋል። ከነፃነት መልስ በ1934 ዓ.ም የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በ አዲስና ልዩ መልክ ተዋቅሮ ሲቋቋም፣

ሠዓሊ አገኘሁ እንግዳም የሥነ ጥበባቱ ዘርፍ መምርያ ረዳት ዳይሬክተር ኾነው ተሠየሙ።

አስገራሚው ሠዓሊ አገኘሁ እንግዳ በከበደ ሚካኤል ታላላቅ ሰዎች መካከል ከቀረቡት ኹለት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነበሩ። የህልፈተ ህይወታቸውም ጉዳይ በጣም አወዛጋቢ ነው። ባልታወቀ ሁኔታ በ 1950 ዓም በ 45 ዓመታቸው አርፈዋል።

## ሻምበል ለማ ጉያ ከ1921-2013 ዓ.ም



ሥዕል 19 ሰዓሊ ሻምበል ለማ ጉያ

በኢይታዊ ጥበብ ታሪክ ውስጥ በሥራዎቻቸው ደማቅ አሻራ ካስቀመጡና ልዩ የሆነ ጥበባዊ እይታን በምጥን የቀለማት ውህደት ውስጥ የማሳየት ፀጋን ከታደሉ እውቅ ሠዓሊያን መካከል አንዱ የክብር ዶክተር ሎሬት አርቲስት ሻንበል ለማ ጉያ ናቸው።

የክብር ዶክተር ሎሬት ሻምበል ለማ ጉያ ከአባታቸው ጉያ ገመዳና ከእናታቸው ማሬ ኀበና በቀድሞው ምስራቅ ሸዋ አድአ ሊበን ወረዳ ደሎ በሚባል ቀበሌ ውስጥ ነሐሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም ተወለዱ።

በልጅነታቸው እናታቸው የእጅ ስራ አዋቂና ባለሙያ ነበሩና ለማ እንደማንኛውም የአካባቢው ሕፃናት ሁሉ የህፃንነት እድሜያቸውን ተጫውተውና ተሯሩጠው ከማሳለፍ ይልቅ የእናታቸውን ፈለግ በመከተል የቅርፃ ቅርፅ ሥራን አጥብቀው ይወዱና አዘውትረውም ይሰሩ እንደነበር ይነገራል።



ሥዕል 20 ሰዓሊ ሻምበል ለማ ጉያ በቀለም ቅብ ስራ ላይ

በዚህም ለሞያው በነበራቸው ከፍተኛ ፍቅርና በሸክላ ስራዎች ላይ በሚሰሯቸው የሰው፣ የእንስሳትና የቁሳቁስ ቅርፆች ቤተሰባቸውንም ሆነ የአካባቢውን ሰዎች በማስደነቃቸውና ትኩረትን በመሳባቸው በአካባቢው ማህበረሰብ አወንታዊ ምክረ ሀሳብ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት እንዲገቡ እድሉ ተመቻቸላቸው። በአስራ አምስት አመታቸውም ከሚኖሩበት ቀበሌ በአስር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው በቀድሞው አጠራር አፄ ልብነ ድንግል ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን ጀመሩ።




ሥዕል 21 ሰዓሊ ሻምበል ለማ ጉያ በእስቱዲዮ ስራ ላይ

በጊዜውም እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ ይሰጥ የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት በ1943 ዓ.ም አጠናቀው ቶሎ ሥራ በመያዝ ቤተሰባቸውን ለመርዳት በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ናዝሬት (በድሮ ስሙ) ዓፄ ገላውዴዮስ ተብሎ በሚጠራው የመምህራን ተቋም በመግባት በመምህርነት ሠልጥነው ሥራ ጀመሩ። ነገር ግን መልሰው ሥራቸውን በማቋረጥ ወደ ትውልድ ቀያቸው ተመለሱ።

የዛን ጊዜው ብርቱ ወጣት ለማ ጉያ ከህጻንነት እድሜያቸው ጀምሮ በልባቸው የሰረፀውን የዕደ-ጥበብ እና የሥነ-ሥዕል ሞያ ለማሳደግ ብሎም ስለሙያው ጠለቅ ያለና በቴክኖሎጂ የታገዘን እውቀት ለመገብየት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲያሰላስሉ ቆይተው እንደ ድንገት አንድ መላ በህሊናቸው ብልጭ ይልላቸዋል። ይኸውም ከእንጨት በመስራት በቀለማት ያስዋቡትን የአውሮፕላን ሞዴል በየሳምንቱ መጨረሻ ወደ ቢሾፍቱ ለሚመጡት ንጉስ ኃይለሥላሴ ማሳየትና ትኩረታቸውን መሳብ ነበር። ሃሳባቸውም ተሳክቶላቸው በአንድ ወቅት ኃይለ ስላሴ ለጉብኝት ወደ ቢሾፍቱ በሄዱበት ጊዜ ከንጉሱ ፊት ቀረቡ።

ንጉሱም የለማን ሥራ አይተው እጅግ በመደነቃቸው ምን እንዲደረግላቸው እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸዋል። ለማም ‹‹ግርማዊ ሆይ አየር ኃይል ያስገቡኝ›› ብለው መመለሳቸውን እና ጃንሆይም በለማ ጉያ ሀሳብ በመስማማት እና በማድነቅ ወደ አየር ሀይል እንዲገቡ መመሪያ መስጠታቸው ይነገራል።

በአየር ሃይል ማሰልጠኛ ተቋሙ የሚሰጠውን ስልጠና ካጠናቀቁና ሁለት አመታት በማሰልጠኛው ካገለገሉ በኋላ በ1945 ዓ.ም በወጣት ዕጩ የፖሊስ ኃይል ሰልጣኝነት የሚሰጠውን ስልጠና በማጠናቀቅ በ1950 ዓ.ም በከፍተኛ ውጤት ተመረቁ።



ሥዕል 22 ከሰዓሊ ሻምበል ለማ ጉያ የጥበብ ስራዎች መካከል አንዱ

ሠዓሊ ለማ ጉያ ከሰለጠኑበት የአየር ሃይል ሙያ በተጓዳኝ ወደዚህ ሙያና ስራ ለመግባት በር የከፈተላቸውን የሥነ-ጥበብ ሙያ ሳይዘነጉ በአስመራ የጣሊያኖች የስዕል ትምህርት ቤት ከደሞዛቸው እየቆረጡ ከፍለው በመማር የሙያ ማዳበር ሥራቸውን የቀጠሉ ሲሆን በተለይም በገፀ ምስል፣ በመልክአ ምድር እና በቁሳቁስ (Still-Life) ሥራዎች በመማር በተፈጥሮ የታደሉትን እውቀት ሊያዳብሩ ችለዋል።

በተለይም በአየር ሃይል በነበራቸው ቆይታ ለአየር ሃይሉ አባላት የሥዕል ኤግዚቢሽን በማቅረብ በአንድ በኩል በወታደራዊ ትምህርቱ የተሰጣቸውን ግዳጅ እየተወጡ በሌላ በኩል ለአባላቱ የሥዕል ሥራዎችን በማሳየት ለሥነ-ሥዕል ጥበብ የነበራቸውን ልዩ ፍቅር አሳይተዋል።

የሠዓሊ ለማ የሥነ-ሥዕል ጉዞ እናታቸው ማሬ ጎበና ከሚሰሩት የሸክላ ሥራ በተጨማሪ፣ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን የአፈር አይነቶች በመደባለቅ የተለያዩ የሰውን፡ የእንስሳትን ሥዕሎች በቤታቸው ግድግዳ ላይ ይስሉና ለቤቱም ልዩ የሆነ ውበትና ድምቀትን ይፈጥሩ እንደነበር ይነገራል።

ተፈጥሮአዊ የአሳሳል ዘይቤን የሚያዘወትሩት ሠዓሊ ለማ ጉያ በአገራችን ዘመናዊ የምስል ቴክኖሎጂ ባልተስፋፋበት ወቅት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦችን የአለባበስና የአኗኗር ዘይቤን የሚገልፁ ትውፊት እና ባህልን የሚያጎሉ የጥበብ ስራዎችን በመስራት እና በማሳተም በመላው አገሪቱ እንዲዳረሱ በማድረጋቸው እና በስፋት የቆዳ ላይ የቀለም ቅብ ስራዎችን በመስራት ይታወቃሉ።

ለማ ጉያ ብሩሽ እና ቀለማቸውን በማዋሃድ የሠሯቸው የሥዕል ሥራዎች እጅግ በርካታ ቢሆኑም በተለይ ግን ‹‹የሸክላ ገበያ››፣ ‹‹የደንከል ልጃገረድ››፣ ‹‹ቋንጣ››፣ ‹‹አቦል ቡና››፣ ‹‹እሬቻ››፣ ‹‹ዋርካ››… የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው እና ሌሎችም ሥራዎቻቸው የማህበረሰባችንን ባህል እና ወግ መሰረት ያደረጉ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎች በመሆናቸው በብዙዎች ዘንድ አድናቆት እና ሙገሳን ያተረፉባቸው ሥራዎች ናቸው።

በኑሯቸውም ሆነ የሥዕል ሥራዎቻቸውን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እስከ እድሜ ማምሻቸው በትጋት የሠሩት የክብር ዶክተር ሎሬት አርቲስት ሻንበል ለማ ጉያ ለአገር እና ለሕዝብ ብዙ ሠርተዋል። «ይህቺ ናት አገሬ፣ ይህቺ ናት ኢትዮጵያ» እያሉም ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን ለዓለም ህዝብ አስተዋውቀዋል። ከሥዕል ሥራዎቻቸው ባሻገርም ለህዝባቸው እና ለአገራቸው ነፃነትም የታገሉ የነበሩ እና ትውልድ ሁል ጊዜ ሥራዎቻቸውን እና መልካም ምግባራቸውን ሲዘክር ይኖራል።ሻምብል ለማ ጉያ በአደረባቸው ፅኑ ህመም ጥቅምት 21 2013 ዓ.ም በተወለዱ በ92 አመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል።

## የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ



ሥዕል 23 የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ምስል

በዓለም የታወቁ እና የተከበሩት የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በሰሜን ሸዋ የቀድሞ ነገሥታት ከተማ በነበረችው አንኮበር ላይ ጥቅምት 13 ቀን 1925 ዓ.ም ከአባታቸው አቶ ተክሌ ማሞ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ፈለቀች የማታወርቅ ተወለዱ።

የመጀመሪያና መካከለኛ ትምህርታቸውን የት እና መቼ እንዳጠናቀቁ የተጻፈ መረጃ ባይገኝም፤ ገና በአሥራ አምስት ዓመታቸው በ 1940 ዓ/ም ለከፍተኛ ትምህርት ተመርጠው የምሕንድስና ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ሎንዶን አገር እንዲሄዱ ተደረገ።

በሽኝታቸው ወቅት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሲሰናበቱ፣ አፈወርቅ ተክሌ ጃንሆይ የሰጧቸውን ምክር ሁሌም እንደሚያስታውሱት ይናገራሉ። “ንጉሠ ነገሥቱ ተግታችሁ አጥኑ፣ ተማሩ ብለው ከመከሩን በኋላ ጠንክራችሁ በመሥራት ኢትዮጵያን የምትገነቡበት ዕውቀት ይዛችሁ ተመለሱ።

ስትመለሱ አዕምሯችሁ ዝግጁ የሆነ እውቀታችሁም ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚችል ጥበብን ሸምቶ እንዲመለስ ነው እንጂ አውሮፓ ውስጥ እንዴት ያሉ ረዣዥም ፎቅ ቤቶች እንዳሉ ወይም መንገዶቻቸው የቱን ያህል ስፋት እንዳላቸው እንድትነግሩን አይደለም።” ነበር ያሏቸው

አፈወርቅ ተክሌ በእንግሊዝ ትምህርታቸውን በትጋት ሲከታተሉ የቆዩ ሲሆን በተለይም በሒሣብ፣ በኬሚስትሪ እና በታሪክ ትምህርቶች ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብም ችለዋል።

ነገር ግን አስተማሪዎቻቸው የተፈጥሮ ስጦታቸው እይታዊ ጥበብ እንደሆነ ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። በእነርሱ አበረታችነት በዚህ ተሰጥዋቸው ላይ የበለጠ ለማተኮር ወስነው በሎንዶን የስነ-ጥበብ ትምህርት ቤት ተመዝግበው ገቡ። ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች እየተዘዋወሩ፣ በየቦታው እስከ ሦስት ወራት በመቀመጥ የብሔር ብሔረሰቦችን ታሪክ፣ ባህልና ወግ ሲያጠኑ ቆዩ።

“ምኞቴ በዓለም የታወቀ ኢትዮጵያዊ የእይታዊ ጥበብ ምሁር መሆን ስለነበር፣ የአገሬን ወግ እና ባሕል ጠንቅቄ ማወቅና ማጥናት እንዳለብኝ አውቄያለሁ። ሥራዬ የዓለም ንብረት ይሆናል ነገር ግን በአፍሪካዊነት ቅመም የጣፈጠ ሥራ ነው የሚሆነው።” ይሉም ነበር። ወደ ውጭ ሊሄዱ ሲነሱ የሰሙትን የንጉሠ ነገሥቱን ቃላት ‘....ኢትዮጵያን ለመገንባት አዕምሯችሁ ዝግጁ ይሁን፣ ለዚህም የሚጠቅም ጥበብን ሸምቱ...” ያሏቸውን ቃላት ሁል ጊዜ በውስጠ ጆሯቸው እያስተጋቡ፤ ከውጭ ሲመለሱ ሚኒስቴር እንዲሆኑ ቢደረግም እሳቸው ግን ይህንን ሃላፊነት በመተው የእይታዊ ጥበብ ሥራቸው ላይ በማተኮር ስዕሎቻቸውን በአገር ውስጥም በውጭ አገርም እያሳዩ ለማገልገል ቀረጡ።



ሥዕል 24 ከአለም ሎሬት ሜትር አፈወርቅ ተክሌ የጥበብ ስራዎች መካከል አንዱ

በሃያ ሁለት ዓመታቸውም በ1946 ዓ/ም ሥራቸውን የሚያሳይ የመጀመሪያውን የእይታዊ ጥበብ ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አቀረቡ። ወዲያውም ከዚህ ኤግዚቢሽን ባገኙት ገቢ ተመልሰው ወደአውሮፓ በመሄድ ለሁለት ዓመት በኢጣልያ፣ ፈረንሳይ፣ ስፔን፣ ፖርቱጋል፣ ብሪታንያ እና ግሪክ አገሮች የጠለቀ የእይታዊ ጥበብ ጥናት አከናወኑ። በተለይም በነዚህ አገሮች ውስጥ በስደት የሚገኙትን የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሃይማኖታዊ የብራና መጻሕፍት በጥልቀት አጠኑ። እንዲሁም የመስታወት ስዕል (stained glass art) እና የ'ሞዛይክ' አሠራርን ጥበብ ተምረው ወደአገራቸው ተመለሱ። እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ከመደበኛ የስቱዲዮ ስራዎቻቸው በተጨማሪ የሀይማኖታዊ ስዕሎች፣ የመስታውት ስዕል እና ቅርፃቅርፆችን ሰርተዋል። ለምሳሌ፡- የመናገሻ ቅዱስ ጊወርጊስ ቤተክርስቲያን የግድግዳን እና የጣራ ስዕሎች በተጨማሪም የሞዛይክ ስራዎችን ሰርተዋል። እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን የዘውድ ስርዓት የሚያሳይ ስዕል እና በሐረር ከተማ የሚገኘውን የልዑል ራስ መኮነን ሀውልት እና ሌሎች በርካታ የሆኑ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚያሳዩ የእታዊ ጥበብ ስራዎች ሰርተዋል።የአዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ/ም በተወለዱ በ79 ዓመታቸው ባደረባቸው ፅኑ ህመም ምክንያት ዓርፈዋል።

እናት ኢትዮጲያ ደመራ የመስቀል አበባ





ሥዕል 25 የዓለም ሎሬት ሜትር አርትሲት አፈወርቅ ተክሌ የስዕል ስራዎች ውስጥ በከፊል

ሠዓሊና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ ደስታ



ሥዕል 26 ሰዓሊ እና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ ደስታ የስዕል ስራ በመስራት ላይ እያሉ

‹‹ሞት እንደሁ ልሙት፣ በሴኮንድ መቶኛ
እንቅልፍ እንደሬሣ፣ ዘለዓለም ልተኛ፡፡
መንገድ ስጡኝ ሰፊ ስሄድ እኖራለሁ
ሰማየ ሰማያት እመዘብራለሁ
የተዘጋውን በር እበረግዳለሁ፡፡
የሌለ እስኪፈጠር የሞተ እስኪነቃ
በትልቅ እርምጃ ከመሬት ጨረቃ

ከጨረቃ ኮከብ

ካንዱ ዓለም ወዳንዱ

ስንዝ እፈጥናለሁ

በፀሐይ ላይ ቤቴን ጎጆ እቀልሳለሁ።

. . . መንገድ ስጡኝ ሰፊ

ፀሐይ ልሁን ፀሐይ

እንደ ጽርሐ አርያም ሁሉንም የሚያሳይ

እሳተ ገሞራ አመድ እረመጡን

ጎርፍ የእሳት ጎርፍ ልሁን።

… መንገድ ስጡኝ ሰፊ››

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሥነ ስዕል ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ የነበረው ሠዓሊና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ ደስታ የ‹‹ጠፈር ባይተዋር›› ሲል በ1961 ዓ.ም ከፃፈው እና ጥልቅ ጥበባዊ ስሜቱን ከገለፀበት ቅኔው የተወሰደ ነው።

ገብረክርስቶስ ደስታ የቤተክህነት ሊቅ ከሆኑት ከአባታቸው አለቃ ደስታ ነገዎ እና ከእናታቸው ወ/ሮ አፀደ ማርያም ወንድማገኘሁ ጥቅምት 5 ቀን 1924 ዓ.ም በሐረር ከተማ ተወለደ። ሠዓሊ እና ባለቅኔው ገብረክርስቶስ ደስታ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ታሪክ ላይ በተለይ ረቂቅ (አብስትራክት) የተሰኘውን ዘመናዊ የሥዕል አሠራር ስልት በስፋት ከማስተዋወቅ በላይ የሀገሪቱን እና የሕዝቧን ሕይወት ባመዛኙ ጅኦሜቲሪክ ይዘት ባላቸው ስነ ጥበባዊ ስራዎች በመግለጽ፣ የጠቢብ እና የዜግነት ገዴታውን ለሀገሩ አበርክቷል።

ድንቅ ሥዕሎቹንም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በግልና በቡድን በተደጋጋሚ ኤግዚቢሽን ያሳየ ሲሆን፣ በሕዝቦች የባሕል ልውውጥ በየጊዜው የኢትዮጵያ የሥነ ጥበባት ቡድን መሪ ልዑክ በመሆን በልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ አደባባዮች ላይ ሀገሩን የወከለ የጥበብ ሰው ነበር።

በቡድን እና በግል የሥዕል ኤግዚቢሽን ላይ በጀርመን፣ በዩጎዝላቪያ፣ በግሪክ፣ በሕንድ፣ በሩሲያ፣ በቼኮዝላቫኪያ፣ በሴኔጋል፣ በጋና፣ በብራዚል፣ በስፔን፣ በኢጣሊያ፣ በፈረንሳይ፣ በቤልጅየም፣ በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በናይጄሪያ፣ በኬንያ ወዘተ… በስፋት የተሳተፈ ሲሆን በዘመናዊ አሣሣል የጥበብ ስልቱ በሀገሩ እውቅና ከማግኘት አልፎ ለዓለም የሥነ ጥበብ እድገት እና መሻሻል የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የሥነ-ስዕል ዕድገት ተጠቃሽ በመሆኑ በ1958 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሽልማት ድርጅት የሀገሪቱን ከፍተኛና ዓለም አቀፋዊ የሥነ ጥበብ ሽልማት በልዩ ሽልማት የተቀበለው ሠዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ እንደ መምህርነቱም ከ1955 ዓ.ም እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ ባሉት 12 ዓመታት ውስጥ ዛሬ ለሀገሪቱ አንቱ የተሰኙ እና ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸውን ሠዓሊያንን አፍርቷል።

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ ግጥም ባህል ውስጥ ገብረክርስቶስ ደስታ ጥልቅ እና ስሜትን የሚነኩ ግጥሞችን አበርክቷል። ገብረክርስቶስ በሕይወቱ ሳለ አንዳንድ ግጥሞቹ እና ቅኔዎቹ በየጋዜጣው እና በየመጽሔቱ ታትመው የወጡለት ሲሆን፣ አንዳንዶቹንም በልዩ ልዩ መድረኮች በሀገር እና በውጭ ሀገር ጭምር ራሱ አቅርቧቸዋል። እንደዘመናዊ ሥዕሎቹ ሁሉ፣ በኢትዮጵያ የሥነ ግጥም ባህል ውስጥ የራሱን ትልቅ ድርሻ አበርክቷል።

በሕይወት ያለፈው ገብረክርስቶስ ደስታ ከነበሩን ብርቅዬ የጥበብ ሰዎች አንዱ ነበር። ይሁንና በዘመነ ደርግ በሕይወቱ ላይ ባንዣበበ አደጋ በመስከረም ወር 1971 ዓ.ም ሀገሩን በስደት ጥሎ እንደወጣ ቀረ። ከተሰደደ ከሁለት ዓመታት እንግልት በኋላ መጋቢት 21 ቀን 1973 ዓ.ም. በተወለደ በ49 ዓመቱ አሜሪካ ኦክላሆማ ግዛት ሕይወቱ አለፈች።ለሀገሩ መሬት ሳይታደል ግብዓተ መሬቱም እዚያው ተፈፀመ። ከገብረክርስቶስ ደስታ ስዕሎች በከፊል የተወሰኑትን ከዚህ በታች እንመልከት።



ጎሎጎታ



አረንጓዴ ድርሰት

ሥዕል 27 ከሰዓሊ እና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ ደስታ ስራዎች በከፊል

## ተግባር -2

ተማሪዎች፣ ከላይ በቀረበው እና በተማራችሁት የታላላቅ ኢትዮጵያዊያን ስዓሊያን የህይወት ተሞክሮ እና ስራዎቻቸውን መነሻ በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ሀሳባችሁን በተናጠል፣ በጥንድ በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ እየወጣችሁ አቅርቡ።

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ታላላቅ ስዓሊያን እነዚህ ብቻ ናቸው ወይስ ሌሎችንም ታውቃላችሁ?
2. ታላላቅ የኢትዮጵያ ስዓሊያን ለስራዎቻቸው መነሻ የሚያደርጓቸውን ሀሳቦች፣ እይታዎች ከምን ከምን ነገሮች ያፈልቃሉ (ያመነጫሉ)?
3. ታላላቅ የኢትዮጵያ ስዓሊያንን የህይወት ተሞክሮ እና ስራዎችን መነሻ በማድረግ ለወደፊቱ እናንተስ በምን በምን የሙያ መስኮች የመሰማራት ራዕይ አላችሁ? ለማህበረሰቡ እና ለሀገራችሁ ምን አስተዋፅኦ ለማበርከት አስባችኋል (አቅደችኋል)?

## 3.6 በኢትዮጵያ የሚገኙ ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶች

ኢትዮጵያ በርካታ የሆነ የማህበረሰብ ስብጥር እና ብዝሀነት ያላት ሀገር ስትሆን ህዝቦቿም በፍቅር በአንድነት ተቻችለው፣ ተፋቅረው በጋራ የሚኖሩባት ቀደምት እና ጥንታዊ የሆነ ታሪክ ያላት ሀገር ነች። ስለሆነም በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ አለባበስ፣ አመጋገብ ወ.ዘ.ተ. ያላቸው በመሆኑ ሀገራችን የዚህ ሁሉ ተዋፅኦ ውጤት በመሆኗ እና ጥንታዊ ይዘትን፣ እሳቤን በተላበሱ ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶች በተሰሩ የእጅ ስራ ውጤቶች የተሞላች እንድትሆን አድርጓታል። እነዚህ ጥበባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የማህበረሰብ ብዝሀነት የአስተሳሰብ፣ የባህል፣ የእምነት፣ የፈጠራ፣ የታሪክ ማሳያ መስታወት በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብዝሀነት ያላቸው ማህበረሰቦች ጥበባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች የእለት ከዕለት ተግባራቸው ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል አሁንም ድረስ ተግባራዊነቱ ቀጥሏል።



በሀገራችን ኢትዮጵያ ሀገር በቀል የሆኑ ጥበባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች ሃሳብ እና ተግባር ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ እየተላለፉ የመጣ እና ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ተግባር ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጥበባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች ከሌላው አለም ለየት ከሚያደርጉት መሰረታዊ ምክንያቶች ተግባሩ የሚከናወነው ከህፃናት የእድሜ ክልል ጀምሮ በእድሜ የገፉ ሰዎችንም ጭምር እና በሁሉም ፆታ የሚተገበር መሆኑ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን በምንኖርበት ምድራዊ ልዑል በአፍሪካ አህጉር በአፍሪካ ቀንድ የምትገኝ በመሆኗ በተፈጥሮአዊ አቀማመጥም በብዙ ነገሮች የታደለች ናት። ማለትም በጣም ከፍተኛ ከሆነው እና እስከ 4800 ሜትር ከፍታ በላይ ያለው ራስ ደጀን (ዳሽን) እንዲሁም በጣም ዝቅተኛ የሆነው የደንከል ሰምጥ ሸለቆ የሚገኝባት ናት። ስለሆነም ሀገራችን ጥንታዊ የነበረው እና አሁን ያለው ጥበባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች የሀገሪቱን ተፈጥሮአዊ የመሬት አቀማመጥ ጥንታዊ እና ቀደምት የሆኑ ስልጣኔዎች መገኛ እና በመረጃ የተደገፉ የስልጣኔ መነሻ፣ ማሳያ የሆኑ በርካታ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣ ማህበራዊ ስልጣኔ ካላቸው ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት፣ ከእስያ፣ ከመካከለኛው ምስራቅ፣ ከአውሮፓ ወ.ዘ.ተ ጋር ስሟ እንዲጠራ አስችሏል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ ቦታዎች እና አካባቢዎች ከጥንት ጀምሮ እካሁን ድረስ ማህበረሰቡ ሲጠቀምባቸው የቆዩት እና አሁንም ድረስ በመተግበር ከሚገኙ ሁሉን አቀፍ ከሆኑ ሀገር በቀል እውቀቶች መካከል በዋናነት የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

1. በባሌ ክፍለ ሀገር አርሶ አደሮች በማሳቸው ውስጥ ድንችን ጃርት እንዳይበላባቸው የሚጠቀሙት ብልሀት
2. የኮንሶ ማህበረሰብ ባህላዊ የሆነው የአፈር አጠባበቅ እና የእርከን ጥበብ ስራ

3. አርሶ አደሮች የመሬት ለምነትን ለመጠበቅ እና ጥሩ ምርት ለማግኘት ተግባራዊ የሚያደርጉት ዘዴ
4. በዎልቂጤ፣ ወሊሶ፣ ቲሊሊ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ከቀንድ የሚሰሩ ልዩ ልዩ ጥበባዊ ስራዎች
5. በደብረብርሀን፣ በትግራይአካባቢ የሚገኙ ማህበረሶች መኖሪያ ቤታቸውን ከድንጋይ፣ ከጭቃ፣ ከአመድ ወ.ዘ.ተ የሚተገብሯቸው የቤት ስራ ዲዛይኖች
6. ቀደምት የሆኑት የአክሱም ሀውልት፣ የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርሲቲያናት፣ የዓፄ ፋሲለደስ ቤተ መንግስት ጎንደር ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ኪነ ህንፃ የሚያሳዩ ናቸው
7. ሰውነትን የማስዋብ፣ ጥንታዊ ይዘት ያላቸው የአልጋ ዲዛይንና የፀጉር ስታይል ከቆዳ፣ ከእንጨትና ከድንጋይ በመቁረጥ፣ በመጥረብና በመፈልፈል የሚሰሩ መገልገያ ቁሳቁሶች ይጠቀሳሉ።
8. ለእርሻ ተግባር እና ምርትን ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ የእርሻ መሳሪያዎችን ዲዛይን የማድረግ እና የመስራት እውቀት
9. በአዲስ አበባ እና በአዋሳ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ከሸንበቆ፣ ከቃጫ የሚሰሩ ለቤት ውስጥ እና ለጌጣጌጥ ተግባር የሚውሉ ልዩ ልዩ እቃዎችን የመስራት ጥበብ ወ.ዘ.ተ.

ሀገር በቀል የሆኑ ጥበባዊ ክዋኔዎች ታሪክ በኢትዮጵያ እንደሚታወቀው በዚሁ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ፤ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን የፃፉ ሙህራን፤ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚገልፁት የኢትዮጵያ ሀገር በቀል የሆኑት ጥበባዊ ክንዋኔዎች የጀመሩት ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ መሆኑን ያስረዳሉ። በሀገራችን ውስጥ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሲተገበሩ የቆዩ እና በመተግበር ላይ ያሉት ሀገር በቀል ጥበባዊ ክዋኔዎች በሁለት ይከፈላሉ።

1. ሀይማኖታዊ ጥበባት (ቀለም ቅብ፣ መስቀል፣ ጥንታዊ ፁህፎች፣ የዘውድ ዲዛይን፣ አለቶችን መጥረብ የእምነት ቦታዎችን መገንባት፣ ለእምነት ተግባር ማስኬጃ የሚውሉ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው ከብረት፣ ከእንጨት፣ ከመዳብ፣ ከነሀስ ዲዛይን የሚደረጉ እና የሚሰሩ ሀይማኖታዊ ቁሳቁሶች ወ.ዘ.ተ)
2. ማህበረሰብ አቀፍ ጥበባዊ እውቀት (የአልባሳት ዲዛይን፣ የቀርቅሀ፣

የሽንበቆ ስራዎች፣ የጌጣጌጥ ስራዎች ወ.ዙ.ተ.)

በሀገራችን የተለያዩ የታሪክ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በእውቀት እና ልማዳዊ በሆነ መንገድ የሚከወኑ ሀገር በቀል እውቀቶች፣ ልምዶች፣ ከዛሬ 3000 አመት በፊት ጀምሮ በተለይ ደግሞ ከዳማት ስርወ መንግስት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ ይታወቃል። በሀገራችን አለትን በመጥረብ እና በመፈልፈል የሚሰሩ የጥበብ ስራዎች ከመጀመራቸው በፊት ትናንሽ እና መካከለኛ ይዘት ባላቸው የተለያዩ ድንጋዮች ላይ የሚሰሩ ዲዛይኖች እና ፁህፎች፣ የተቀረፁ ምስሎች ወ.ዘ.ተ.የሚጠቀሱ ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ በእምነት ተቋማት፣ በተለያዩ አካባቢዎች እና ቦታዎች ውስጥ የነበረው ሀገር በቀል የሆነ ሃሳብ እና ተግባር በሂደት በተለያዩ ምክንያቶች ወረራ፣ ጥፋት፣ ተፅዕኖ ተፈፅሞበታል። ይሄም በመሆኑ በርካታ የሆኑ ሀገር በቀል እውቀቶች፣ ሃሳቦች፣ ተግባራቶች (ጥበቦች) አንዳንዶቹ ሙሉ ለሙሉ የተወሰኑት በከፊል እንዲጠፉ እና እንዲዳከሙ የማድረግ ተግባራቶች ተፈፅመዋል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሆኑ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ጥበባዊ ውጤቶች ይገኛሉ። ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ጥበባዊ ስራዎች ስንል አንድ ማህበረሰብ በአካባቢው በሚያገኛቸው ጥሬ እቃዎች ተጠቅሞ በራሱ ሀገር በቀል በሆኑ የአሰራር ዘዴዎች እና ቴክኖሎጅዎችን መሰረት በማድረግ በአብዛኛው በእጅ የሚያመርታቸው ቁሳዊ ባህሎች ናቸው። ማህበረሰቡም እነዚህን ሀገረ ሰባዊ እጅ ስራዎችን የሚያዘጋጀው በእለት ከዕለት ህይወቱ የሚፈልገውን ምርት ለማምረት፣ መሰረታዊ ፍላጎቱን ለመሟላት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማዘጋጀት በሚል ፍላጎት እና እሳቤ ነው። በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች እና አካባቢዎች የሚገኙት ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆኑ ልዩ ልዩ ባህላዊ እና ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ ያላቸው በርካታ ሀገረ ሰባዊ የእጅ ጥበብ ስራ ውጤቶች ይገኛሉ። እነዚህን ሀገረ ሰባዊ ጥበባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች የሚሰሩበትን ግብአቶች፣ የሚሰሩበትን አላማ፣ የአሰራር ስልታቸውን ወ.ዘ.ተ.መነሻ በማድረግ የእንጨት፣ የወረቀት፣ የፀጉር፣ የሳር፣ የክር፣ የቆዳ፣ የቀንድ፣ የብረት፣ የድንጋይ ወ.ዘ.ተ. በሚል ሊከፋፈሉ/ሊጠኑ/ ይችላሉ። በአጠቃላይ በሀገራቸን በተለያዩ አካባቢዎች እና ቦታዎች በሚኖሩ ማህበረሰቦች ሀገር በቀል በሆነው ጥበባዊ እውቀቶች የሚሰሩ በርካታ የሆኑ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው ስራዎች ያሉ ቢሆንም ሀሳቡን ለመረዳት እና ለአያያዝ አመች እንዲሆኑ በዘርፍ በዘርፋቸው ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

- በቤት እና በእርሻ ተግባር ለሚከናወኑ ቀላል እና ከበድ ያሉ ስራዎችን ለመስራት የሚውሉ
- በቤት ውስጥ ለመመገቢያ፣ ለመጠጫ፣ ለመቀመጫነት፣ ለመኝታ አገልግሎት የሚውሉ
- በቤትውስጥየምርትውጤቶችን ለማስቀመጥ፣ ምግብን ለማዘጋጀት፣ ለመፍጨት፣ ለማቡካት፣ ለመጋገር፣ ለማስቀመጥ ወ.ዘ.ተ. የሚሆኑ
- እንጨቶችን፣ ብረቶችን፣ የእንጨት እና የብረት ውጤቶችን ለመቆራረጥ/ ለማዘጋጀት/ የሚውሉ
- ለጦር መሳሪያ እና ተያያዥ ተግባራቶች የሚያገለግሉ ወ.ዘ.ተ.

### 3.6.1 ሀገር በቀል የሆነ ይዘት ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎች

ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶችን በመጠቀም የሚሰሩ ጥንታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች ማህበረሰቡ ያለውን ታሪክ፣ ገጠመኝ፣ ርዕዮተ አለም፣ ፍልስፍና፣ ሀይማኖት ወ.ዘ.ተ. የራሱን ሀገር በቀል እውቀት እና ቁሳቁሶችን በግብአትነት በመጠቀም የሚሰሩ ናቸው። በአገራችን በተለያዩ ቦታዎች እና አካባቢዎች በቤተ ክርስቲያን፣ በመስጊድ፣ በገዳማት ወ.ዘ.ተ. በመሳሰሉት የእምነት ስፍራዎች በግድግዳ ላይ፣ በድንጋይ ላይ፣ በእንጨት ላይ፣ በጨርቅ ላይ፣ በብራና ላይ ወ.ዘ.ተ ተስለው የሚገኙ በርካታ ሀገር በቀል የቀለም ቅብ ስራዎች ይገኛሉ።

ሀገረ ሰባዊ የቀለም ቅብ ስራዎች ከሚሰሩበት አላማ፣ ከሚጠቀሙት ግብአት፣ ከአሰራር ስልታቸው፣ ከሚያስተላልፉት መልዕክት ወ.ዘ.ተ. አንፃር ሀይማታዊ ቀለም ቅብ ስራዎች፣ ታሪካዊ ቀለም ቅብ ስራዎች፣ ተፈጥሮአዊ ይዘት ያላቸው ቀለም ቅብ ስራዎች በመባል የሚመደቡ ናቸው። አብዛኛዎቹ የአለም ሀገራት የእውቀት ብልጭታን ባላዩበት እና ባላሰቡበት ዘመን በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች እና አካባቢዎች ያሉ ማህበረሰቦች ጥንታዊ ይዘት ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎችን በመስራት በጊዜው የነበራቸውን ሀሳብ እና ስላጣኔ ለመጭው ትውልድ እንዲቆይ እና እንዲተላፍ አድርገዋል።

በሀገር በቀል እውቀት እና ጥበብ የተሰሩት ጥንታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች ለረዥም ዘመናት የሀገራችንን ጥንታዊ የስልጣኔ መሰረት እና ሚሰጥሮችን በመሸከም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ ቆይተዋል። በሀገራችን ታሪክ ጥንታዊ ይዘት ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎች የተሰሩበት ሁኔታ እና ጊዜ ቢኖርም በዋናነት ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ድርሻ ነበራት። በዋናነት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ከእንስሳት

ቆዳ፣ ከእንጨት ብራና አዘጋጅተው፣ ድንጋይ ጠርበው፣ እንጨት አለስልሰው ልዩ ልዩ ቀለማቶችን ከአፈር፣ ከተለያዩ እፅዋቶች እና ልዩ ልዩ አዝርዕቶችን በመጠቀም ቀምመው እና አዘጋጅተው ኢትዮጵያዊ የሆነ የቀለም ቅብ አሰራር ስልትን ተከትለው የሳሏቸው በርካታ ይዘት እና መጠን ያላቸው የቀለም ቅብ ውጤቶች በተለያዩ የሀገራችን ክፍል በተለያዩ ቦታዎች ይገኛሉ። እነዚህ ጥንታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች የሀይማኖቱን ታሪክ እና አስተምህሮ፣ የሀገሪቷን ታሪክ እንዲሁም የህዝቡን ማንነት ማሳያ ምልክቶች በመሆን ለብዙ ዘመናት ኖረዋል ወደፊትም ለቀጣዩ ትውልድ ታሪክን ተሸክመው የሚቀዩ ሀገር በቀል በሆነ ጥበብ እና እውቀት የተሰሩ የአገራችን ቅርሶች ናቸው።

ጥንታዊ ይዘት ያላቸው ቀለም ቅብ ስራዎች ከሚገኙባቸው የሀገራችን ክፍሎች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ። በጎርጎራ ደብረ ሲና ማርያም፣ በጎንደር ደብረ ብርሀን ስላሴ፣ በጣና ሀይቅ ክብራን ገብርኤል እና ናርጋ ስላሴ፣ በአዲስ አበባ እንጦጦ ማርያም እና ራጉኤል፣ በከፋ ዞን አንደርቻ መድህኒያለም፣ በትግራይ አባ የማታ ና አቡነ አሮን ገዳማት ይጠቀሳሉ።

**ማስታወሻ፡-**

በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች እና አካባቢዎች የሚሰሩት ጥንታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች ሀይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ትርጓሜ ና መልዕክቶችን የያዙ ናቸው።

እነዚህ ሀገር በቀል በሆነው ጥበብ እና እውቀት የተሰሩት ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎች ከሀይማታዊ ስፍራዎች እና አካባቢዎች በተጨማሪ በዋሻዎች፣ በአለቶች፣ በድንጋይ፣ በእንጨት፣ በመኖሪያ ቤቶች፤ አካባቢዎች ጭምር የሚገኙ ናቸው።

እንዲሁም በድሬደዋ የለገ ኦዳ ዋሻ፣ በጌዲዮ ዞን የገልማ ዋሻ ውስጥ የሚገኙት ጥንታዊ ይዘት ያላቸው የቀለም ቅብ ስራዎች ከሚገኙበት አካባቢ የሚጠቀሱ ናቸው።



ሥዕል 28 በሀገር በቀል ጥበብ እና እውቀት የተሰሩ ጥንታዊ ይዘት ያላቸው ቀለም ቅብ ስራዎች

### 3.6.2 ሀገር በቀል የሆነ ይዘት ያላቸው ጥንታዊ መዛግብት


ጥንታዊ መዛግብት የምንላቸው አሁን ያለው የሰው ልጅ የደረሰባቸው ለዕህፈት እና ለህትመት አገልግሎት የሚውሉ መስሪያና መሳሪያዎች ከመፈጠራቸው እና አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው ብዙ ሽህ አመታቶችን ቀድመው በወቅቱ ስለ ነበሩ ሀይማኖታዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ሀገር በቀል እውቀትን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ቁሳቁሶች ላይ ተፅፈው የምናገኛቸው የፁህፍ ውጤቶችን ነው። እነዚህ ጥንታዊ ይዘት ያላቸው መዛግብት የብራና መፃህፍት፣ የድንጋይ ላይ ፁህፎች፣ የእንጨት ላይ ፁፎች፣ የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው። እነዚህ ጥንታዊ መዛግብቶች ከላይ ከተጠቀሰው ምንነታቸው እና ዘርፋቸው በተጨማሪ ሀገር በቀል በሆነ ጥበብ እና እውቀት ተሰሩ ሊያስብሏቸው ከሚችሉት በርካታ ምክንያቶች መካከል ለመዛግብቱ ማዘጋጃ የሚሆን እራሱን የቻለ ተጨማሪ ጥበብ እና እውቀት የሚጠይቁ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ፦ የብራና፣ የድንጋይ፣ ቀለም፣ የቀለም መያዥያ እቃዎች(ቀንድ)፣ የመቃ (ብዕር) አዘገጃጀት፣ የአዘገጃጀት ሂደት፣ መፃህፍቱን የመደጎስ ዘዴ እና ሂደት፣ መዛግብቱ ሳይበላሹ ለረዥም ጊዜ የማቆየት ስልት ወ.ዘ.ተ ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚህ ሀገር በቀል በሆነው ጥንታዊ ጥበብ እና እውቀት የተዘጋጁት ጥንታዊ መዛግብት ወደ ፁህፍ ስራ ባለሙያዎች ሲገቡ የሚከተሉትን የፁህፍ ዘዴ እና ህግጋትንም መሰረት አድርገው የሚዘጋጁናቸው። መስመር፣ ህዳግ፣ አርእስት፣ ኀላፍ፣ ግሌት፣ ሐውልት፣ ሲራክ፣ ምስማክ፣ ማህፀን፣ ሕድን፣ ዓምድ አዘጋጅተው የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች እና ሀሳቦችን ለመጭው ትውልድ በማስረጃ አስተላልፈዋል። በጥንታዊ መዛግብቶች ላይ ሰፍረው (በመረጃ መልክ) ተቀምጠው ከምናገኛቸው መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

- የነገስታቶች ታሪክ
- የግዛት ሁኔታ
- ያስተዳድሩት የነበረው ህዝብ ና ማንነት
- የተለያዩ ሀይማኖታዊ መፅሀፍት
- የቅዱሳን እና የሰማእታት ገድላት፣ ድርሳናት
- ስለ ጠፈር እና ከዋክብት ጥልቅ የሆነ እይታ እና ትንታኔን የያዙ
- ስለ ፍጥረታት ምንነት እና ባህሪያት ጥልቅ እይታና ትንታኔን የያዙ
- የስነ ምግባር እና የፍልስፍና ማስተማሪ መፅሀፍት
- የነበራቸው ሀብት፣ ስለ ጀግንነታቸው ሁኔታ ወ.ዘ.ተ. ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጥንታዊ ይዘት ያላቸው መዛግብቶች በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ የአለም አካባቢዎች በስፋት እና በብዛት ይገኛሉ። ለምሳሌ፦ በሀገር ውስጥ በደብረ ሊባኖስ፣ በደብረ ዳሞ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ጣና ገዳማት ወ.ዘ.ተ. ይገኛሉ። በተጨማሪም እነዚህ ጥንታዊ መዛግብት በአለም የተለያዩ ሀገራት እና ቦታዎች እንዲገኙ ካደረጓቸው ምክንያቶች መካከል ወደ ሀገራችን በመጡ የአውሮፓ ጎብኝዎች፣ ቅኝ ገዥዎች፣ ተመራማሪዎች፣ አሳሾች፣ የፖለቲካ እና ሀይማኖት አማካሪዎች እንዲሁም ለሀገር ቅርስ በማይቆረቆሩ ኢትዮጵያዊያን አማካኝነት በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው ጥንታዊ መዛግብት፣ ዕሑፎች፣ ደብዳቤዎች ወ.ዘ.ተ. ተዘርፈው ተሸጠው ይገኛሉ።

እነዚህ ጥንታዊ መዛግብቶች በውጭው አለም ከሚገኙባቸው ቦታዎች፣ ሀገሮች፣ ተቋማት መካከልየሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ። በብሪቲሽ ሙዚየም፣ በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ፣ በኬምብሪጅ ዩንቨርስቲ፣ በበርሊን ቤተ መፃህፍት ወ.ዘ.ተ.ተጠቃሽ ሲሆኑ እነዚህንም ለማስመለስ እና ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ ሰራ መሰራት አለበት።

ሥዕል 29 ሀገር በቀል በሆነው ጥበብ እና እውቀት የተፃፉ ጥንታዊ ይዘት ያላቸው መዛግብት

## 3.6.3 ሀገር በቀል በሆነው ጥንታዊ ጥበብ እና እውቀት የተሰሩ የሸክላ ስራዎች

### የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ሀሳባችሁን በተናጠል፣ በጥንድ በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ እየወጣችሁ አቅርቡ

1. በሀገራችን የሸክላ ጥበብ ስራ መቼ እና እንዴት እንደተጀመረ ታውቃላችሁ?
2. በምትኖሩበት ቤት ውስጥ የተለያዩ ተግባር እና አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ መገልገያ ቁሳቁሶች ከምን ከምን እና እንዴት እንደተሰሩ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ?
3. በሸክላ ጥበብ የተሰሩት መገልገያ ቁሳቁሶች ሀገር በቀል በሆነው ጥንታዊው ጥበብ እና በሀገሬው ሰው የሚሰሩ መሆኑንስ አስባችሁ ታውቃላችሁ?

የሸክላ ጥበብ ስራ ማለት ምግብ ለማብሰል፣ ለመመገቢያ፣ ለመጠጫ እና ለልዩ ልዩ ተግባር እና አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ነገሮችን በዋናነት የሸክላ አፈርን ለዚሁ ተግባር በማዘጋጀት እና ከፍተኛ ሙቀት ባለው እሳት በማቃጠል ጠንካራ የሆነ ይዘት እንዲኖረው እና ለረዥም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጎ የመስራት ሂደት እና ውጤት ነው።

የሸክላ ጥበብ ስራ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ተግባራዊ ከሚደረግበት አካባቢ የሚኖረውን ማህበረሰብ ባህል፣ እምነት እለታዊ ክንውን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ወ.ዘ.ተ. መነሻ በማድረግ በተለያያ ይዘት እና መጠን ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል።

የሸክላ ጥበብ ስራ የሚጠቀመውን ግብአት፣ የአሰራር ሂደቱን እና ተሰርቶ ካለቃ በኋላ የሚሰጠውን አገልግሎት መነሻ በማድረግ በሚከተሉት ሶስት ክፍሎች ይመደባሉ።

## የአፈርነት ባህሪይ ያላቸው የሸክላ ስራዎች

የሸክላ አፈሩ ለዚሁ ተግባር ከተዘጋጀ በኋላ ስስ ይዘት ባለው መልኩ እየተገነባ፣ እየታሸ፣ እየተስተካከለ ይሰራ እና ሲጠናቀቅ አነስተኛ ሙቀት ባለው እሳት (ከ 600 — 1200 ) ዲግሪ ፈራናይት እንዲቃጠል ይደረጋል ይሄም መጠነኛ የሆነ ጥንካሬ እንዲይዝ ያደርገዋል።

ይህ የሸክላ ዘርፍ ከዋናው የሸክላ ይዘት ውጭ ሌሎች ለማሰዋቢያ የሚሆኑ ዲዛይኖች፣ ጌጣጌጦች አይሰሩበትም። ወጥ እና ልሙጥ የሆነ ይዘት ያለው ሲሆን በእይታም ቀይ፣ ቡናማ፣ ጥቁር፣ ቡናማ አይነት ቀለማትን ይይዛል። ተሰርቶ ካለቀ በኋላም የፈሳሽነት ባህሪይ ያላቸውን ነገሮች ለመያዝ ያገለግላል። ብዙም ጠንካራ የሆነ ይዘት የላቸውም። ይህም በጥንካሬ ደረጃ የድንጋይና የሴራሚክ ባህሪ ካላቸው ያነሱ ናቸው።




ሥዕል 30 የአፈርነት ባህሪ ያላቸው የሸክላ ስራዎችን የሚያሳይ

## የድንጋይ ባህሪ ያላቸው የሸክላ ስራዎች

የሸክላ አፈሩ በጥሩ ሁኔታ ከተመረጠና ከተዘጋጀ በኋላ በሚፈለገው ይዘት እና መጠን በመገንባት፣ በማሸት፣ በማስተካከል እየተሰራ ከተጠናቀቀ በኋላ በጣም ከፍተኛ የሙቀት ሀይል ባለው እሳት (ከ1100-1200) ዲግሪ ፈራናይት እንዲቃጠል የሚደረግ ሲሆን ይሄም ሁኔታ የሸክላ ውጤቱን ጠንካራ የሆነ ይዘት እንዲኖረው ያስችለዋል።

በቋሚነት የፈሳሽነት ባህሪ ያላቸውን ነገሮች ለማስቀመጥ ተግባር አይውልም በብዛት ለመመገቢያ፣ ለመጠጫ የሚውሉ እቃዎችን ለማምረት ይውላል በላዩ ላይ መጠነኛ የሆኑ ጌጣጌጦች ሊሰሩበትም ላይሰሩበትም ይችላል። ድንጋይ ለበስ(እንደ ድንጋይ ጠንካራ) የሆኑ የሚለው መጠሪያ የተሰጣቸው በጣም

ጠንካራ በመሆናቸው የተነሳ ነው። እንዲሁም በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ ሙቀትን የመቻልና ሙቀትን የማቆየት አቅም አላቸው። ከዚህም የተነሳ ለምድጃ፣ ለምግብ ማብሰያ፣ ትኩስ ምግቦችን ለማቅረብ አገልግሎት በስፋት ይውላሉ።




ሥዕል 31 የሸክላ ስራ ጠንካራ ይዘት ያላቸው

## ከሴራሚክ የሚዘጋጁ የሸክላ ስራዎች

ለሸክላ ስራው የተመረጠው እና የተዘጋጀው የተፈጨ ሴራሚክ በጥሩ ሁኔታ ከተመረጠና ከተዘጋጀ በኋላ በሚፈለገው ይዘት እና መጠን በመገንባት፣ በማሸት፣ በማስተካከል እየተሰራ ከተጠናቀቀ በኋላ በጣም ከፍተኛ የሙቀት ሀይል ባለው እሳት (ከ2200 -2600) ዲግሪ ፈራናይት እንዲቃጠል የሚደረግ ሲሆን ይሄም ሁኔታ የሸክላ ውጤቱን በጣም ጠንካራ የሆነ ይዘት እንዲኖረው ያስችለዋል። በተጨማሪም በጣም ሳቢ እና ማራኪ ይዘት ያላቸው ዲዛይኖች ይኖሩታል። ይህ የሸክላ አይነት በተለያዩ ቀለማት እጅግ ውስብስብና ጥልቅ በሆኑ ዲዛይኖች የተዋበ እና የተጌጠ በመሆኑ እጅግ ሳቢና ማራኪ በጣም አንፀባረቂ የሆነ ይዘት እንዲላበስ አስችሎታል።




ሥዕል 32 የሸክላ ስራዎች በዲዛይን ኢፌክት

**ማስታወሻ፦**

የሸክላ ጥበብ ስራ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሀገራችንን ጨምሮ በሌሎችም የአለም ሀገራት ተግባራዊ እየተደረገ የቆየ እና አሁንም በመተግበር ላይ ይገኛል።

የሸክላ ጥበብ ስራው ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ በጥሩ ሁኔታ በሚፈለገው መጠን እና ይዘት ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ባህላዊ እና ዘመናዊ ይዘት ያላቸው የማቃጠያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

## የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

ተማሪዎች፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን በተመለከተ በዝርዝር ሰፋ ያሉ ሀሳቦችን እና ትንታኔዎችን ተምራችኋል። በመሆኑም ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ሀሳባችሁን በተናጠል፣ በጥንድ በመሆን ያዘጋጃቹሀትን ዘገባ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ እየወጣችሁ አቅርቡ።

1. ሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎች (ውጤቶች) ስንል እንዴት ይገለፃሉ?
2. ሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎች ለማህበረሰቡ እና ለሀገር የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ እና በውስጣቸው የያዙትን እምቅ እውቀት እና ሀብት እንዴት ይገለፃል?
3. ሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎችን እና እውቀቶችን ማህበረሰቡ በአግባቡ እየተጠቀመባቸው ይመስላችሁዋል? ለምን?
4. የውጭው አለም ማህበረሰብ በተደጋጋሚ ሀገራዊ በሆኑት የጥበብ ስራዎች እና እውቀቶች ወረራ፣ ዘረፋ፣ ማጥላላት፣ መደበቅ እና ሌሎች አላስፈላጊ ተግባራቶችን ሲፈፅሙ እንመለከታለን። ለምን ይመስላችሁዋል?

## 3.7 ሀገር በቀል እውቀትን በቴያትር እና በፊልም መግለፅ

### የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ሀገር በቀል እውቀት ማለት ምን ማለት ይመስላችሁዋል?
2. በአካባቢያችሁ እና በክልላችሁ የሚገኙ ሀገር በቀል እውቀቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።
3. በቴያትርና በፊልም የተላለፉ ሀገር በቀል እውቀቶች ላይ ያተኮሩ ክውን ጥበባትን ተመልክታችሁዋል? ምን ምን ሀሳቦች ተንፀባርቀውባቸዋል?

**ማስታወሻ፡-**

ሀገር በቀል እውቀት ማለት በአንድ ሀገር እና አካባቢ ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦች ከእለት እለት የሚያከናውኗቸውን የኑሮ ዘይቤን ውጣ ውረድን ለማቃለል የሚጠቀሙበት ባህላዊ እውቀታቸው ሲሆን በተጨማሪም ለአንድ ሀገር ህልውና መሰረት ነው።

ሀገር በቀል እውቀቶችን ለህዝብ የምናስተምረው ሳይሆን ከህዝብ የምንማረው እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላላፍ የቆየ ነው።

ማህበረሰቡ በተለያየ የኑሮ ዘይቤ ቢገኝም አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታውን ለማቃለል፣ ለችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚጠቀምባቸውን የመገልገያ እቃዎች የአሰራር ዘዴዎች፣ የግብርና እቃዎች አሰራር እና አጠቃቀም፣ ባህላዊ ህክምናዎች፣ የእደ ጥበብ ውጤቶች፣ ጥንታዊው የከዋክብት እና የጠፈር ምርምር፣ ወቅትን፣ ጊዜያቶችን መለየት(መረዳት)፣ ጥንታዊ ፍልስፍና(እሳቤ)፣ የእርቅ ስርዓት የመሳሰሉት ናቸው።

እነዚህን ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶች ማህበረሰቡ ከጥንት ጀምሮ ባከማቸው ልምድ (እውቀት) በመጠቀም እና ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በማዛመድ በኑሯቸው ሂደት ውስጥ በማስተሳሰር ተጠቅመውበት አልፈዋል ትውልዱም በቅብብሎሽ አሁን ድረስ እየተጠቀመበት ይገኛል። በአጠቃላይ እነዚህ እውቀቶች ከባህል፣ ከታሪክ ከአፈ ታሪክ፣ ከዘፈን፣ ከባህላዊ ትውፊቶች እና ወጎች ወ.ዘ.ተ. እናገኛቸዋለን።

የፊልም እና የመፅሀፍት ደራሲዎች፣ የታሪክ አጥኝዎች፣ የቲያትር አዘጋጆች ወ.ዘ.ተ.እንደየ ሙያ ዘርፋቸው ልዩ ልዩ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ለመስራት ሲያስቡ (ሲፈልጉ) ለሀሳባቸው እንደመነሻ፣ ለሚፈልጉት መረጃ እንደ ማጣቀሻ ለማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሲተገበሩ የቆዩ እና ተግባራዊ እየሆኑ ያሉትን ጥንታዊ የሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶችን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር፣ ለማስተዋወቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ አስፈላጊ ከሆኑት አይታዊ ጥበባት መካከል ፊልምና ቲያትር ተጠቃሽ ናቸው።

ስለሆነም የዘርፉ ባለሞያዎች ጥበባዊ ክዋኔዎችን በሚፈልጉት መንገድ እና ሁኔታ ለመስራት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሀገር በቀል ጥበባዊ አውቀቶችን እና ሌሎችንም እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደሁኔታው በማጣጣም ይጠቀሙባቸዋል። ለምሳሌ፡-

- በኮንሶ ማህረበረስብ ባህላዊ የሆነው የእርከን ስራ እና የአፈር ጥበቃ ዘዴ
- ቀደምት የሆኑት የአክሱም ሀውልት እና የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን የምህንድስና ጥበብ
- ባህላዊ የሆነው ብረትን የማቅለጥ እና የብረታ ብረት ጥበብ ስራ
- ሰውነትን የማስዋብ፣ የሸክላ ስራዎች ወ.ዘ.ተ.

| ተ.ቁ | የምዕራፉ ይዘቶች | ተረድቻለሁ | አልተረዳሁም |
|---|---|---|---|
| 1. | የአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ እና ስራዎችን | | |
| 2. | በአማራ ክልል የሚገኙ አርቲስቶች እና ተወዛዋገሮች ታሪክ እና ስራዎቻቸውን | | |
| 3. | ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶችን ምንነት | | |
| 4. | የሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶች ግብአቶችን፣ የአተገባበር ሂደት | | |
| 5. | በኢትዮጵያ የስዕል እና የሙዚቃ ጥበባት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ታላላቅ ሰዓሊያንን እና የሙዚቃ ባለሙያዎችን | | |
| 6. | ሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶችን በመጠቀም የቲያትር እና ፊልም ጥበባትን እንዴት መግለፅ እንደሚቻል | | |

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሦስት ተካተው የቀረቡት ይዘቶች የስነ ጥበባት ባህላዊ እና ታሪካዊ ዳራዎች እና ማህበራዊ ትስስሮችን የሚገልፁ እና የተማሪዎችን ምልከታዎች ማስፋት የሚያስችሉ ነበሩ። ከእነዚህ መካከል በአማራ ክልል የሙዚቃ ታሪክ እና የሙዚቃ ተወዛዋዦች ታሪክ እንዲሁም የሙዚቃ ባለሙያዎች ስላበረከቱት ማህበራዊ እና ሙዚቃዊ አስተዋተፅዖዎችን ተመልክታችኋል። ከነዚህም መካከል ለማ ገብረ ሕይወት፣ አሰፋ አባተ፣ አስቴር አወቀ፣ ማሪቱ ለገሰ እና አሰፋ ደባልቄ ይጠቀሳሉ። እንዲሁም በውዝዋዜው ዘርፍ በርካታ እንደነበሩ ይታወቃል። በክልሉ የሙዚቃ እድገት ውስጥ ሚናቸው የማይረሳው የጊሽ አባይ ኪነት ቡድን፣ ወሎ ላልይበላ ኪነት ቡድን እና የጎንደሩ ፋሲለደስ ኪነት ቡድን አበርክቷቸው ከፍተኛ ነው። በሀገር ደረጃ ከፍተኛ አስተዋፅዖ የነበራቸው የሙዚቃ ባለሙያዎች ደግሞ ቅዱስ ያሬድ፣ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ እና በሻህ ተክለማሪያም የሚጠቀሱ ናቸው። የወሎ የላልይበላ፣ የጎንደር ፋሲለደስ፣ የጎጃም ጊሽ አባይ የኪነት ቡድን ተወዛዋዦች ተጠቃሽ ናቸው።

- ✍ በሀገር በቀል ጥበባዊ ክዋኔዎችን እና የእደ ጥበብ ስራዎችን በተመለከተ
- ✍ ጥንታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች፣ ሳቢና ማራኪ የሆኑ ጥንታዊ መዛግበቶች፣ የሸክላ ስራዎች
- ✍ የሀገር በቀል ጥበባዊ እወቀቶችን በቲያትር እና በፊልም የመግለፅ ጥበብን በተመለከተ ቀርበዋል። በመጨረሻም በምዕራፉ ላይ የተቀመጡ ይዘቶችን ተማሪዎችን በሚያሳትፍ መልኩ የተቀመጡ ልዩ ልዩ ተግባራት እና ጠቃሚ ማስታወሻችን፣ መልመጃዎችን ያካተተ ነው።

# የማጠቃለያ መልመጃዎች

**ትዕዛዝ አንድ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛ ሀሳብ የያዘውን እውነት ያልያዘውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ።**

1. እዝል ማለት ታዛይ ማለት ሲሆን ከግዕዝ ጋር ተደርቦ የሚዜም ለስላሳ ዜማ ነው።
2. አሰፋ አባተ በ1927 ዓ.ም በሀገር ፍቅር ቴያትር ቤት ስራ የጀመረበት ጊዜ ነበር።
3. ቅዱስ ያሬድ በ505 ዓ.ም በአክሱም ተወለደ።
4. ማሪቱ ለገሰ የክልሉን ባህል በማስተዋወቅ የምትታወቅ የአምበሳል ንግስት ነች።
5. የማህበረሰቡ ባህል፣ እምነት እና ታሪክ ለሀገር በቀል ጥበባት እንደ መነሻ በመሆን አያገለግሉም።
6. ሀገር በቀል ጥበብ እና እውቀት ለእይታ ከሚቀርቡባቸው የስነ ጥበባት ዘርፎች መካል ፎቶ ግራፍ አንዱ ነው።
7. የክብር ዶክተር ሎሬት አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ በ1946 ዓ.ም ተወለዱ

**ትዕዛዝ ሁለት፦ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር እና ግልፅ መልስ ስጡ።**

1. በሻህ ተክለ ማርያም የሀገራቸውን ባህል ለማስተዋወቅ የሙዚቃ ቡድን በመምራት በቀድሞው ሶብየት ህብረት እና ቻይና የሄዱት መቼ ነበር?
2. አሰፋ ኣባተ ከሚታወቅባቸው ዘፈኖች መካከል ሶስቱን ጥቀሱ""
3. የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች ውስጥ ሶስቱን ፃፉ።
4. በሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶች ከሚሰሩት ሶስቱን ጥቀሱ።
5. ከአለም ሎሬት ሜትር አርቲሰት አፈወርቅ ተክሌ ስራዎች መካከል አራት ጥቀሱ።
6. ስዓሊ ና ገጣሚ ገብረ ክርስቶስ ደስታ በቡድን እና በተናጠል ጥበባዊ እግዚቢሽን ካሳየባቸው ሀገሮች (ቦታዎች) መካከል አምስት ጥቀሱ?
7. ለቴአትር እና ፊልም ጥበባት ሀሳብ ለማመንጨት እንደመነሻ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች መካከል ሶስት ዘርዝሩ?

# ምዕራፍ 4



# ሥነ ውበታዊ ጠቀሜታ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በአካባቢያችሁ ለሚገኙ ስነ ውበታዊ እሴቶች ዋጋ ትሰጣላችሁ፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ስነ ውበታዊ እሴቶችን ታደንቃላችሁ፤
- ክውን እና እይታዊ ጥበባትን ተዛምዶ እና ልዩነት ታውቃላችሁ፤
- በኢትዮጵያ የሚገኙ የስነ ጥበባት ውጤቶችን እና ስራዎችን አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በዋናነት ለስነ ጥበባት ትምህርት ዋጋ መስጠትን ለተማሪዎች ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ይዘቶችንና ጥቅማቸውን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ሀሳቦችን አካቷል። በመሆኑም የስነ ጥበባት ጥቅሞችን በተለያዩ ዋና ዋና ዘርፎች ለማህበራዊ ህይወት፣ ለፖለቲካ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለሀይማኖታዊ ዘርፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ ቢኖረውም በዚህ ርዕስ ስር የተካተተው ለማህበረሰቡ ህይወትና እድገት ያለውን ጠቀሜታ ይዳስሳል። በተጨማሪም ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያለውን የክውንና እይታዊ ጥበባት አሰራራቸውን እንድታደንቁና እውቅና እንድትሰጡ በሚያስችል መልኩ ቀርቧል።

## 4.1 የእይታዊ ጥበባት ጠቀሜታ

### የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች፣ በአካባቢያችሁ ለሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች የምትሰጡት ስነ ውበታዊ ዋጋ ምን ያህል ነው?
2. ተማሪዎች፣ በአካባቢያችሁ ከምትመለከቷቸው በርካታ ነገሮች መካከል የትኛው ነው የእናንተን የእይታ ስሜት የበለጠ የሳበው? ለምን?
3. አንድን ነገር ውብ (ጥሩ) ነው ወይም ውብ አይደለም ለማለትና ለመለካት የሚያስችሉን ነገሮች ምን ምን ናቸው?

የዘርፉ ባለሙያዎችና ለሙያው ቅርበት ያላቸው ሰዎች ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ውበትንና ተያያዥ ሁኔታዎችን እንዲሁም ከሰው ልጆች ጋር ያለውን መስተጋብራዊ ሂደት ለመፈተሽ፣ ለማወቅ፣ ለማሳወቅ ሲያደረጉ የቆዩትና በመደረግ ላይ ያሉት ሁነቶች ቀጣይነት ያላቸው መሆኑ ይታወቃል።

ስለሆነም የሰው ልጅ ውበት የሚለውን ቃል የሚረዳበት ሁኔታና መጠን የሚያግባባ እና የጋራ መሆኑ ግልፅ ነው።

ነገር ግን ሰዎች ለውበት የሚሰጡት እሳቤ፣ የሚገለፅበት መንገድ፣ የአከናወን ሂደቱ በሰዎች የመረዳት እና የማገናዘብ አቅምና ሁኔታ የማህበረሰቡን ባህል፣ እምነት፣ ስልጣኔ፣ አይታ፣ አከናወን፣ ግብአት ወ.ዘ.ተ. መነሻ በማድረግ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ነው።

ስነ ውበታዊ ዋጋ በነገሮች፣ በድርጊቶች (በሁኔታ)፣ በጉዳዮች፣ በስነ ጥበባዊ ስራዎች፣ ተፈጥሯዊ አካባቢዎች ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ነገሮች ስናስብ እና ተግባራዊ ስናደርግ ውበትን በመፍጠር ጥሩ የትኛው እንደሆነ ጥሩ ያልሆነው ደግሞ የትኛው እንደሆነ ለማሳየት ለመገንዘብ የምንመዝንበት ጥበባዊ ምልከታ ነው።

ስለዚህ የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ስነ ውበታዊ ሀሳቡን እና ስሜቱን ለመግለፅ፣ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ስነ ውበታዊ እሴቶችን የተላበሱ እንዲሆኑ በማድረግ እና ስነ ውበታዊ ዋጋ በመስጠት ኑሮውን ምቹ፣ አስዳሳች፣ ሳቢ እና ማራኪ ለማድረግ በማያቋርጥ ሂደት ላይ

ይገኛል።

## ማስታወሻ፦

ውበት (ውብ) ስንል አንድን ነገር አስደሳች መሆን (ጥሩ ሆኖ መገኘት) ና አለመሆንን ለመገንዘብ፣ ለመወሰን እና ለመለየት የሚረዳን ነገሮችን የመመልከት እና የመረዳት ቅንጅታዊና ሂደታዊ ውጤት ነው።

## ተግባር

ተማሪዎች፣ በምትኖሩበት አካባቢ እና በተለያዩ ቦታዎች በሀይቅ (በውሀ ዳርቻ) እና በአካባቢው ያሉትን ሌሎች ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት በጥሩ ሁኔታ የተገነባ ህንፃ እና እንዲሁ የሆነ ቦታ ላይ ስነ ውበታዊ ተግባርን ባላገናዘበ መልኩ የተገነባ ህንፃ ስታዩ (ስታወዳድሩ) የትኛው ውብ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ሀሳባችሁን በምክንያት በማስደገፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ ግለፁ። ከዚህ በታች የቀረቡትን ምስሎች ተመልክታችሁ በማነፃፀር ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።




ሥዕል 33 ስነ ውበታዊ ቅንጅትን የሚያሳይ



ሥዕል 34 ስነ ውበታዊ ቅንጅትን የማያሳይ

የውበትን ዋጋ ለመጨመር እና ለማሳደግ፣ ሰዎች እንዲመለከቱት እና እንዲገነዘቡት የምናድርግበት መንገድ እና ሁኔታ አስደሳች የሆነ ስነ ውበታዊ ስሜትን ለመፍጠር በመጀመሪያ እኛ በውስጣችን ያሰብነውን ረቂቅ ሀሳብ ማሳደግ እና ማበልፀግ ይገባል። በመቀጠልም ሀሳቡን ሊታይ፣ ሊዳሰስ እና ሊደመጥ በሚችል መንገድ መቃኘት እና ማምጣት ተገቢ ነው።

ለምሳሌ፡- የፀሀይን ወደ ማታ መጥለቅ በፎቶ ግራፍ ለማንሳት (ለማስቀረት) ብንፈልግ ፎቶ ግራፉችን የሚኖረውን ስነ ውበታዊ ዋጋ ከፍ ለማድረግ ወይም ውብ እንዲሆን ለማድረግ ከማንሳታችን በፊት የምናነሳውን ቦታ መምረጥ(መወሰን)፣ ከፀሀይዋ መጥለቅ ጋር አብረው ያሉ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን መቃኘት እና ማቀናጀት በመጨረሻም ደስ የሚል ስሜት የፈጠረብንን በመለየት ማንሳት ይኖርብናል።

ከላይ በተገለፁት ሂደቶች እና ሌሎች መሰረታዊ የውበት ማሳያ የሆኑ ነገሮችን በመተግበር የሚሰራ ማንኛውም ነገር በየትኛውም ሰው ዘንድ ደስ የሚል ውበትን ከመፍጠር እና ከማሳየት የሚያግደው ነገር አይኖርም።





ሥዕል 35 ተፈጥሯዊ ውበትን የሚገልፁ

**ማስታወሻ፡-**

ስነ ውበታዊ ስሜትን ለማምጣት (ለመፍጠር) የምናረቃቸው ሀሳቦች፣ የምናከናውናቸው ድርጊቶች፣ የምንጨምራቸው፣ የምናስተካክላቸው ስነ ውበታዊ እሴቶች ውበቱ እንዲገለፅ የፈለግነውን ነገር የሚኖረውን ከፍተኛ ስነ ውበታዊ ይዘት ያሳድጋሉ።

## ተግባር፦ የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. እይታዊ ጥበባት ስንል እንዴት ይገለፃል?
2. በእይታዊ ጥበባት የሚካተቱት ዘርፎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገሩ።
3. እይታዊ ጥበባት ካላቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች መካከል የተወሰኑትን ዘርዝሩ።

እይታዊ ጥበባት ስንል በዋናነት የጥበብን ምንነት እና ጥልቀት ሊያስገነዝቡ እና ሊያሳዩን ከሚችሉ በርካታ የስነ ጥበባት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በውስጡም ልዩ ልዩ ክፍሎችን የያዘ ነው። ከነዚህም መካከል ቀለም ቅብ፣ ኪነ ቅርፅ፣ ግራፊክስ አርት፣ ዲዛይን፣ ንድፍ፣ ኮላዥና ሞዛይክ፣ ፎቶግራፍ፣ ኪነ ፅህፈት፣ ኪነ ህንፃ፣ ፊልም፣ ፋሽን ዲዛይን ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው።

እይታዊ ጥበባት ከላይ የተገለፁትን ዘርፎች ወደ ተግባራዊ ክንውን በመቀየር ለመስራት ልዩ ልዩ ይዘትና መጠን ያላቸው ግብዓቶችን ይጠቀማል።

እነዚህ ግብዓቶችም ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታዩ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ይዘት ያላቸው በማለት ይጠቀሳሉ።

እይታዊ ጥበባት ካላቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች መካከል የሚከተሉትን እንመለከታለን።

- የህፃናት አካላዊና አዕምሮአዊ እድገትን ያበለፅጋል፣ ያጠነክራል።
- ሰዎች ነገሮችን የሚመለከቱበትን፣ የሚረዱበትን፣ እሳቤና እይታ ያሻሽላል
- ውስጣዊ እና ረቂቅ የሆኑ ስሜቶችን፣ ሀሳቦችን ሊታዩና ሊዳሰሱ ወደ የሚችሉ ነገሮች የመቀየር አቅምን እና ክህሎትን ከፍ ያደርጋል
- በአካባቢያችን የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ቀርቦ የመረዳት፣ የመለየት፣ የማድነቅ ፍላጎትን ይጨምራል
- በራስ የመተማመን ስሜትን ያጎለብታል፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ ከሰዎች ጋር የመግባባት፣ አብሮ በጋራ የመስራት አቅምን ያሳድጋል።
- የምንኖርበትን አካባቢ ለኑሮ ምቹ፣ ሳቢ እና ማራኪ እንዲሁም አስደሳች ለማድረግ በሚደረገው ሙያዊ አበርክቶ ትልቅ ድርሻ አለው።
- የችግር ፈችነት አቅምን ያጎለብታል

- በመማር ማስተማር ክዋኔ የሌሎች ትምህርቶች የመማር ማስተማር ሂደት ተግባር ተኮር፣ አይረሴነት እንዲኖረው፣ አሳታፊ እና አስደሳች እንዲሆን ያደርጋል።

## 4.2 የክውን ጥበባት ጥቅሞች

በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች የራሳቸው የማንነት መገለጫ እና ማሳያ የሆኑ በርካታ ጥበባዊ እሴቶች ለዘመናት አብሯቸው የኖረ ነው። ይህም ሲባል ጥበባዊ ዘርፎች እንዲሁ የተገኙ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ በሽግግር እና በረዥም ጊዜ የተከማቸ እውቀት የመጣ መሆኑ ይታወቃል።

ማህበረሰቡ ጥበብ በሚባል የቤት መሰረት የተገነባ ሲሆን በውስጡ በርካታ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን የማስተሳሰር ብቃት ያለው እና ህዝብንም ለረዥም ዘመናት የመቻቻል አብሮ የመኖር ትስስርን የሚያመጣ ከፍተኛ ሀይል ያለው የጥበብ ዘርፍ ነው።

### ተግባር

1. ክውን ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ።
2. የክውን ጥበባት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ አብራሩ።

የክውን ጥበባት ማለትም ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ እና ቴያትር ለማህበረሰቡ የተለያዩ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ። በተጨማሪም በመማር ማስተማር ሂደት ጉልህ ሚና አላቸው። ከዚህ በታች በተለያዩ ምድቦች የክውን ጥበባት ጠቀሜታን እንመለከታለን።

### 4.2.1 ክውን ጥበባት ለማህበራዊ ህይወት ያላቸው ጠቀሜታ

- ሰፊ ጉልበትን እና ረዥም ጊዜን የሚጠይቁ ተግባሮች የሚያመጡትን የስራ ጫናን ለመቀነስ ለምሳሌ፦ የደቦ ስራ፣ የእርሻ ስራ ወቅት ድካምን ለመቀነስ ባህላዊ ሙዚቃን ይጠቀማሉ።




ሥዕል 36 የእርሻ ወቅት ዘፈኖችን የሚያሳይ

- ለማህበረሰቡ በተለያዩ ሁነቶች ማለትም ለሰርግ፣ ለበዓላት፣ ለልደት ወ.ዘ.ተ ወቅት ባህላዊ ሙዚቃን በመጠቀም የእርስ በእርስ ግንኙነታቸው እና ባህላቸውን ያዳብራል።



ሥዕል 37 ባህላዊ የሰርግ ሂደት የሚያሳይ

- የጋራ ስሜትን በቡድን ለመግለፅ ይህም ሲባል ህዝቦች አንድ የሚያደርጋቸውን የሀገር ስሜት እና ፍቅርን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል።
- መረጃን ለመለዋወጥ ይጠቀሙበት ነበር። ይህም ሲባል ጥንት ባልተማሩ ማህበረስብ ውስጥ ሀሳብን ለመግለጽና እና ከትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር ይጠቀሙበት ነበር።
- ሀገረ ሰባዊ እውቀቶችን ከትውልድ ውደ ትውልድ ለማሸጋገር
- ለሌሎች የጥበብ ዘርፎች ለማጀቢያነት ይጠቀሙበታል ለምሳሌ፦ ለፊልም፣ ለቴያትር
- ለመንፈሳዊ ሕይወት ፍልስፍናቸውን እና ሀሳበቸውን ለማህበረሰቡ ለማስረፅ



ሥዕል 38 የመስቀል በዓል አከባበር

### 4.2.2 በህፃናት ማህበራዊ እድገት ላይ ያለው ጠቀሜታ

በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የክውን ጥበባት የሚሰጡት ጠቀሜታን በተመለከተ

- አካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና ስነ ባህሪያዊ ለውጦችን ለማምጣት ያስችላል።




ሥዕል 39 ህፃናት ሙዚቃ መሳሪያ ሲጫወቱ

- የፈጠራ ስራዎችን ለማሳየት እና ለመግለፅ ሀይልን ይሰጣል።



- የቋንቋ እና የንግግር ክህሎታቸውን እንዲዳብር እንዲሁም በቀላሉ ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታቸውን ያሳድጋል።
- በቀላሉ እየተዝናኑ እንዲማሩ እና የማስታወስ ችሎታቸው እንዲዳብር ያደርጋል።




- ታሪካቸውን፣ ባህላቸውን፣ አካባቢያቸውን እና የቤተሰብ ፍቅርን እንዲያዳብሩ ያደርጋል



➤ የክውን ጥበባትን በመተግበር የተስተካከለ የስውነት ቅርፅ እንዲኖራቸው ያደርጋል

## 4.3 ሀገር በቀል የስነ ጥበባት ስራዎች

### ተግባር


ተማሪዎች፣ ከዚህ በታች የቀረበውን በሀገር በቀል ጥበብ እና እውቀት የተሰራውን የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ጥበባዊ ታሪክ እና ፋይዳውን በመገንዘብ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ሀሳባችሁን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

1. ታሪኩን እንዴት ተረዳችሁት? እንዴትስ ታደንቁታላችሁ?
2. ቀደምት ሀገረሰባዊ ጥበባትን ሲያከናውኑ የነበራቸውን አስተሳሰብ፤ የስልጣኔ ታሪክ እንዴት ትገልፁታላችሁ?
3. የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን የታነፁበት መንገድ፣ ሂደቱ፣ ግብአቶቹን፣ ቴክኒኩን እንዴት ነው እውቅና የምትሰጡት?
4. በሌላው አለም ሀገራት በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰሩ ጥበባዊ ስራዎች ሊኖሩ ይችላሉ? ካሉስ ለምን እና እንዴት እንደተሰሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።



ሥዕል 4 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል ቤተ ጊዮርጊስ


ላልይበላ በአማራ ክልል በሰሜን ውሎ ዞን የምትገኝ ከተማ ነች። ላልይበላን ሄደው ሲጎበኙ የተለያዩ ስሜቶች ይፈራረቃሉ። የመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ “እንዴት እስከዛሬ ሳላየው ቀረሁ? ”የሚል የቁጭት ስሜት፣ ከዚህ በፊት አይተውት ከሆነ ደግሞ “እንዴትስ ድጋሚ እያየሁት እንደ አዲስ ያስደንቀኛል” የሚል የመደመም ስሜት ይፈጥራል።



ሥዕል 5 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል

ላልይበላ በዓለማችን ካሉት አስደናቂና አስደማሚ ክስተቶች መካከል ይሰለፋል በዓይን ካላዩት ግን የማስደነቁን ጥልቀት መረዳት የሚቻል አይደለም።

ላልይበላን ስንጎበኝ በአዕምሮዋችን የሚመላለሱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። የላልይበላ ቤተ ክርስቲያናት እንዴት ተሠሩ? መቼ ተሠሩ? በማን ተሠሩ? ለምንስ ተሠሩ? በዚህም ይህንን ጥንታዊ ሀገር በቀል ጥበባዊ ታሪክ በመመልከት እና በመረዳት ለጥያቄዎቹ መልስ ማግኘት ይቻላል።



ሥዕል 6 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የውስጥ ገፅታ

ስለ ላልይበላ ብዙ ተብሏል፣ ተጽፏልም። በሀገራችን ደራሲዎች ቢያንስ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የንጉሥ ላልይበላን ገድል፣ እንዲሁም ባለፉት ምዕተ ዓመታት ስለ ንጉሡ አዳዲስ አፈ ታሪኮች እና ጥናቶች እንደገና ተከልሰው ቀርበዋል። በውጭ ጸሐፊዎችም በተለይ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካሁን የአጥኝዎችንና የደራሲዎችን ቀልብ እንደሳበ ነው። በዛ ያሉ የውጭ ሃገር መጻሕፍትም በላልይበላ ዙርያ ለኅትመት በቅተዋል።

ስለ ሕንጻዎቹ ታሪክ የሚያወጋው የመጀመሪያው ፅሁሑፍ መረጃ በ15ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በተጻፈው “ገድለ ላልይበላ” ነው።

የላልይበላ ገድል እንደሚገልጸው ንጉሡ ሁለተኛዋን እየሩሳሌም በላስታ ለማስገንባት እንዳሰበና ቤተክርስቲያኖቹንም ማሰራት እንደጀመረ ነው። ከአንድ መቶ አመታት ያህል በኋላም በ1520ዎቹ ፍራሲስኮ አልቫሬዝ የተሰኘ ካህን ከፖርቱጋል መልእክት ለማድረስ መጥቶ ለስድስት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀምጦ ነበር። በዚህም ወቅት የላልይበላን ውቅር ቤተክርስቲያናት ለመጎብኘት እድል አግኝቶ እያንዳንዱን ሕንጻ ከገለጸ በኋላ በመደነቅ እንዲህ ብሏል፣ “ስለነዚህ ሕንጻዎች ከዚህ በላይ መጻፍ አልችልም። ምክንያቱም ከዚህ በላይ ብጽፍ የሚያምኑኝ አይመስለኝም። እስካሁን የጻፍኩትንም እውነት አይደለም ይሉኛል ብዬ እፈራለሁ።

በሀገራችንም ሆነ በሌላው ዓለም ክፍል ከተሰሩት ውቅር ሕንጻዎች አንዳንዶቹ ከዚህ በፊት በተፈጥሮ ከተሰሩ ዋሻዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከዋሻውም በመነሳት የተለመደውን የሕንጻ አሰራር አስመስሎ ድንጋዩን በመፈልፈል የሚሰሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ግን አንድ ሙሉ ትልቅ ቋጥኝ ድንጋይን በመፈልፈል ከመሬት በታች ወይም ከተራራ በጎን በኩል ተፈልፍለው ይሰራሉ።



ሥዕል 7 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል

የላልይበላ ቤተክርስቲያናት ከመሬት በታች ወይም ከተራራው ጎን ተፈልፍለው ከሚሰሩት አይነቶች መካከል የሚመደቡ ናቸው። ይህም የሚሰራው እንደተለመደው የሕንጻ አሰራር ከመሰረቱ ተጀምሮ ወደላይ የሚቆለል ሳይሆን ከጣራው ተነስቶ ወደ ታች የሚፈለፈል ነው። ይህም አይነት አሰራር ከሕንጻ ስራ ይልቅ ከኪነ ቅርጽ ከመቅረጽ ጋር ይነጻጸራል። የኪነ ቅርጽ አሰራርን ዝነኛው የመካከለኛው ዘመን ቀራጭ ሚካኤል አንጀሎ ሲገልጸው “እያንዳንዱ ድፍን ድንጋይ ውስጥ ቅርጽ አለ … የቀራጩም ስራ ይህንን ቅርጽ ከታፈነበት ድንጋይ ነጻ ማውጣት ነው” በማለት ነበር። ላልይበላ ልዩ ልዩ የሆኑ የብረት መሣሪያዎችን አሠራ። ለመጥረብም የተሠራ አለ። ለመፈንቀልም የተበጀ ብረት አለ። ለመፈልፈልም የተሠራ አለ።


የላልይበላ ውቅር ቤተክርስቲያናት ከሌሎቹ የሚለዩት በአንድ አካባቢና በተቀራራቢ ጊዜ ከአስር የሚበልጡ ፍልፍል ሕንጻዎች በመሠራታቸው ነው። እንዲሁም ደግሞ ከሌሎቹ በተለየ ጥበብ የፈሰሰባቸው ስለሆነ፣ የአሰራሩ ጥራት፣ የሕንጻዎቹ ግዝፈትና የጌጥ አቀራረፅ ብልሀታቸው ነው። ከቀራጮቹ ችሎታም በተጨማሪ ይህንን ማድረግ የቻሉት የአካባቢው ድንጋይ ለሥራው አመች ስለነበረ ነው።



ሥዕል 8 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል


በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተለያዩ ቦታዎችና አካባቢዎች ከአንድ ወጥ አለት (ቋጥኝ) ተፈልፍለው የተሰሩ በርካታ ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ስራዎች ይገኛሉ። የተፈለፈሉባቸው አለቶች (ቋጥኞች) የሚፈለገውንና የሚታሰበውን የዲዛይን መልክ፣ የጌጣጌጥ ቅርፅ፣ የመስኮቶችና የበሮች ገፅታ በላያቸው ላይ ለመስራት (ለማሳየት) የሚያስችሉና የመለስለስና የመጠንከር ባህርይ ያላቸው መሆናቸውን በተለያዩ ጊዜያት የዘርፉ ባለሙያዎች ያደረጓቸው ጥናቶች ይጠቁማሉ።

አንድ ሕንጻን ከድንጋይ ፈልፍሎ ማውጣት እጅግ ከባድ ስራ እንደሆነ ግልጽ ነው። እንኳንስ አስራ አንድ ትላልቅ ቤተክርስቲያናት ይቅርና አንድን ሙቀጫ ከድንጋይ ፈልፍሎ ማውጣት ምን ያህል እንደሚከብድ የሞከረው ያውቀዋል። ታዲያ አባቶቻችን ይህንን እልህ አስጨራሽ ሥራ ለመስራት ምን አነሳሳቸው ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ስለምን ከመሬት በታች? ስለምን ከአንድ ድንጋይ? ሕንጻ በድንጋይ አነባብሮ መገንባት አይቀልም ነበር? አንድም ሕንጻዎቹን ዘላለማዊ ለማድረግ መፈለግ። ይህም በመጠኑ የተሳካ ይመስላል። ከብዙ መቶ አመታት በኋላ እኛም የእጅ ስራቸውን ለማድነቅ እነሱም የኛን ዘመን ሰው ለማስደመም በቅተዋል።



ሥዕል 9 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል

በሌላ በኩል ደግሞ አስደናቂ ነገር በመስራት ለአምላካቸው ክብር፣ ታላቅነትን ለማሳየት ሊሆን ይችላል። ሰዎች እምነታቸውን ለአምላካቸው ለማሳየት የማይቻለውን አድርገው፣ የማይሞከረውን ሞክረው ይሰራሉ። ይህም አንድም ለቀጣዩ አለም ክብርን ለመሰብሰብ አንድም ደግሞ ለራሳቸው ውስጣዊ ደስታ እና ለአምላካቸው ክብር የሚያደርጉት ነው። ላልይበላ እና የጊዜው የሕንጻ ጥበበኞች በእምነታቸው እና በመንፈሳቸው ጠንካራ እንደሆኑ ከስራቸው ለማየት እንችላለን።



ሥዕል 10 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል

በሌላ በኩል ደግሞ ከመሬት በታች ቤተክርስቲያኖችን መስራት ከጠላት እይታ ለመሸሸግ ሊሆን ይችላል። ከመሬት በላይ ከተሰራ ማንኛውም ህንጻ ይልቅ ከመሬት በታች የሆነውን ጠረኛ ቢመጣ በቀላሉ እንደማያገኘው አስበው ይሆን? በጊዜው ጦርነቶች የተፋፋሙበት ዘመን እንደመሆኑ፣ ቤተክርስቲያናቱን ከእይታ ውጪ የማድረግን አስፈላጊነት አስበው እንደሆነ ይገመታል።

ከላልይበላ በፊት የተሰሩ እንደሆነ የሚታመኑ ከአንድ ድንጋይ የተፈለፈሉ ውቅር ቤተክርስቲያኖች በላስታ አካባቢ እንዲሁም በሌሎች የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍሎች በመገኘታቸው ነው። ይህ የውቅር ሕንጻ ጥበብ ለብዙ መቶ አመታት ከላልይበላ በፊት ሲሰራበት የኖረ በመሆኑ፣ ጥበቡ ከየትም ሳይሆን አገር በቀል ለመሆኑ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተለያዩ ቦታዎችና አካባቢዎች የታነፁት ውቅር አበያተ ክርስቲያናት፣ ሀውልቶች፣ የመፃፍና የመቅርፅ ጥበባት ተወራራሽነት አላቸው። ይህ የሚያሳየው እንዚህን ጥበባት የመከወንና የመስራት ልምዱ በኢትዮጵያ የቆየና ረጅም እድሜ ያስቆጠረ መሆኑን ነው።

ክርስቲያናት በቁጥር እስከ አስራ አንድ (11) የሚደርሱ ናቸው።

እነርሱም፦

1. ቤተ- መድሀኒያለም
2. ቤተ- ማርያም
3. ቤተ - ደናግል
4. ቤተ - መስቀል
5. ቤተ - ደብረ ሲና
6. ቤተ - ጎለጎታ
7. ቤተ - አማኑኤል
8. ቤተ - አባ ሊባኖስ
9. ቤተ - መርቆርዮስ
10. ቤተ -ገብርኤል ወ ሩፋኤል
11. ቤተ -ጊዮርጊስ



ሥዕል 11 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል



ሥዕል 12 ከላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል

እንደ ላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በግብጽ ምድርም ከአንድ ወጥ አለት ለንግሥት ሐትሸፕሱት ቤተ መቃብር የተሰሩትን መጥቀስ ይቻላል።

ከዚያም በኋላ ብዙ ሀያላን ለራሳቸውም ሆነ ለሚያመልኩት እምነት ተራራ ገምሰው ቋጥኝ ደርምሰው ሕንጻዎችን አሰርተዋል። ለምሳሌ በህንድ አገር የሚገኘውን ከዓለማችን ትልቁ ካሀይሊሳ ውቅር የቡድሂስት ቤተ መቅደስ እንዲሁም በሀገረ ጆርዳን የሚገኘውን ካዝነህ ቤተ መቅደስን መጥቀስ ይቻላል።

**ማስታወሻ፡-**

ሀገር በቀል ጥበባዊ ክዋኔዎች ሲሰሩ የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ ባህል፣ እምነት፣ ሰልጣኔን የሚገልፁ ናቸው። የሚሰሩበት ዓላማ፣ የተሰሩበት ግብዓት፣ የአሰራር ስልት፣ የተሰሩበት ዘመን፣ ወ.ዘ.ተ ከቦታ ቦታና ከሀገር ሀገር በርካታ ልዩነቶች አሏቸው።

## 4.3.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

በሀገራዊ የስነ ጥበብ ውጤቶች እና ስራዎች ስንመለከት በኢትዮጵያ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን የተወሰኑትን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎችን አዘገጃጀትን እንመለከታለን።

### የዋሽንት አዘገጃጀት

**ዋሽንት ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡-**

- ሸንበቆ ወይም ቀርክሃ
- የቧንቧ ቱቦ
- ውስጡ ክፍት የሆነ የፕላስቲክ ቱቦ ወ.ዘ.ተ.

**አሠራር፡-**

- መጠነኛ ርዝመት ያለው ሸንበቆ ተቆርጦ ከተሰረሰረ በኋላ ክፍት ሲሆን በአንጓዎቹ መካከል አራት ቀዳዳዎች ይበጅለታል።
- አጨዋወቱም የትንፋሽን ኃይል የሚጠይቅና በአንጓው ላይ ያሉትን አራት ቀዳዳዎች በጣቶች በመዝጋትና በመልቀቅ የተለያዩ ድምፆችን በማውጣት ነው።
- ዋሽንት በድሮ ጊዜ እረኞች የሚያንጎራጉሩበት የባህል ሙዚቃ መሣሪያ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቲያትር ቤቶች በልዩ ልዩ የባህል የሙዚቃቡድኖች ውስጥ ከልዩ ልዩ የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር ተጨምሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል
- ዋሽንት ለእንጉርጉሮ ጨዋታዎች የሕዝቡን ወኔ ለመቀስቀሻ' ለሽለላዎች' የፍቅር ዘፈኖች ወ.ዘ.ተ. ለመጫወት ምቹነት ያለውና ድምፁ የአድማጭን ልብ የሚማርክ ነው።

ስለዚህ ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን ሠርተው የመጡትን ዋሽንት ለመጫወት እንዲሞክሩ ማድረግ።



ሥዕል 13 ዋሽንት

## የአታሞ አዘገጃጀት፡-

**አታሞን ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡**


- ባለ አንድ ጋሎን የቀለም ቆርቆሮ'
- የለፋቆዳ 'ሽቦ ወይም ጠፍር'
- ለመቁረጫ የሚያገለግል ቢላዋ፡

**አሠራር፡**

- ቆዳው እንዲርስ ለሁለት ቀንያህል ውሃ ውስጥ ዘፍዝፎ የቆዳውን ላይ ናታች መፋቅ'
- ቆዳው ከራሰ በኂላ በቆርቆሮው የታችኛው እና ላይኛው ክብ 4.ሳ.ሜ አስተርፎ መቁረጥ'
- የቆዳውን ዳርናዳር ዙሪያውን መብሳት'
- የተበሳውን ቆዳበ ሽቦ ዙሪያውን ጠላልፎ ማሰር'
- ቆዳውን ከቆርቆሮ ታችና ላይ አድርጎ ቀዳዳወች ውስጥ ገመድ በማስገባት እየቆላለፉ ማሰር'

**አጨዋወት፡** በእጅ ወይም በዱላ መምታት ተማሪዎች በቡድን ያዘጋጁትን ከበሮ በመዝሙርና በባህላዊ የዘፈን ጨዋታ እንዲጠቀሙበት ማድረግና

ማበረታታት።




ሥዕል 14 አታሞ

| ተ.ቁ | የምዕራፉ ይዘቶች | አሳክቻለሁ /አውቂያለሁ/ | አላሳካሁም /አላወኩም/ |
|---|---|---|---|
| 1. | የስነ ውበታዊ ዋጋን ምንነት፣ የነገሮችን ስነ ውበታዊ ዋጋ እንዴት መረዳት፣ መግለፅ እንደሚቻል | | |
| 2. | የእይታዊ ጥበባት ምንነትን እና ጠቀሜታቸውን | | |
| 3. | የሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎች የአሰራር ሂደት፣ የሚያስተላልፉትን መልዕክት፣ ማድነቅ | | |
| 4. | ሙዚቃ ለማህበራዊ ሂወት ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ | | |
| 5. | የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አዘገጃጀትን | | |
| 6. | ሙዚቃ ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያለውን ጠቀሜታ | | |

## ማጠቃለያ

የጥበብ ባለሙያዎች ከጥንት ውበትንና ተያያዥ ሁኔታዎችን እንዲሁም ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ዝምድና ለመፈተሽና ለማወቅ የሚያደርጉና ወደፊትም የሚያደርጉ ናቸው። የሰው ልጅ ውበት የሚለውን ቃል የሚረዳበት ሁኔታ የሚያግባባና የጋራ መሆኑ ግልፅ ነው።

ስነ ውበታዊ ዋጋ ስንል፦ በዋናነት በነገሮች፣ በድርጊቶች (በሁኔታ)፣ ጉዳዮች፣ ስነ ጥበባዊ ስራዎች፣ ተፈጥሯዊ አካባቢዎች ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ነገሮች ስናስብና ተግባራዊ ስናደርግ ውበትን በመፍጠር ጥሩ የትኛው እንደሆነ ጥሩ ያልሆነው ደግሞ የትኛው እንደሆነ ለማሳየት የምንመዝንበት ነው።

ስለዚህ የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ስነ ውበታዊ ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ለመግለፅ፣ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ስነ ውበታዊ ይዘትን የተላበሱ እንዲሆኑ በማድረግ እና ስነ ውበታዊ ዋጋ በመስጠት ኑሮውን ምቹ፣ አስዳሳች፣ ሳቢና ማራኪ ለማድረግ በማያቋርጥ ሂደት ላይ ይገኛል።

- የጋራ ስሜትን በቡድን ለመግለፅ ይህም ሲባል ህዝቦች አንድ የሚያደርጋቸውን የሀገር ስሜት ለመግለፅ ይጠቀሙበታል
- መረጃን ለመለዋመጥ ይጠቀሙበት ነበር ይህም ሲባል ጥንት ባልተማሩ ማህበረሰብ ውስጥ ሀሳብን ለመለዋወጥ እና ለመሸጋገር ይጠቀሙበት ነበር
- የቋንቋ እና የንግግር ክህሎታቸውን እንዲዳብር እንዲሁም በቀላሉ ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታቸውን ያሳድጋል
- በቀላሉ እየተዝናኑ እንዲማሩ እና የማስታወስ ችሎታቸው እንዲዳብር ያደርጋል።

## የማጠቃለያ መልመጃዎች

***ትዕዛዝ አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ጥያቄው ትክክለኛ ሀሳብ ከያዘ እውነት ካልያዘ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ።***

1. ማንኛውም በአካባቢያችን የምንመለከተው (የምናገኘው) ነገር በሙሉ ተመሳሳይ የሆነ ስነ ውበታዊ ይዘት አለው።
2. መሰንቆ ከባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ ይካተታል።
3. የሙዚቃ ትምህርት ለመማር ማስተማር ሂደት ጠቀሜታ የለውም።

***ትዕዛዝ ሁለት፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጭር እና ግልፅ መልስ ስጡ።***

1. ስነ ውበታዊ ዋጋ ማለት ምን ማለት ነው።
2. በአካባቢያችን ከሚገኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች መካከል ጥሩ የሆነ ስነ ውበታዊ ይዘት እና ቅንጅት ካላቸው ውስጥ ሶስት ጥቀሱ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ተናገሩ።
3. እይታዊ ጥበብ ስንል ምን ማለት ነው።
4. በሀገር በቀል ጥበብ እና እውቀት በንጉስ ላልይበላ ዘመን ከተሰሩት ውቅር አብያተ ክርሲቲያናት መካከል 4 ዘርዝሩ።
5. ሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎችን እንዴት ታደንቃላችሁ።
6. ሙዚቃ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ካለው ጠቀሜታ ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ።
7. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በሰንት እንደሚመደቡ በዝርዝር ግለፁ።
8. ሙዚቃ ለማህበራዊ ህይወት ካላው ጠቀሜታ ውስጥ ሁለት ጥቀሱ።

# ምዕራፍ 5

# ሥነ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ☞ መኖሪያ ቤትን እና አካባቢን በሸክላ ውጤቶችና በሴራሚክ ስራዎች ማስዋብን ትገነዘባላችሁ።
- ☞ ስነ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና ትገልፃላችሁ።
- ☞ ስነ ጥበባት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚኖራቸውን ሚና እና ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በዋናነት ስነ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚዳስስ ሲሆን በዋናነት መኖሪያ ቤትን እና አካባቢን በሸክላ፣ በሴራሚክ ስራዎች እንዲሁም በአካባቢ በሚገኙ ግብአቶች ማስጌጥን ተማሪዎች እንዲገነዘቡ እና በተግባርም እንዲሰሩ የሚያበረታታ ስራዎችን የያዘ ነው።

በተጨማሪም ሙዚቃ፣ ቴአትር፣ ውዝዋዜ ወዘተ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና በተመለከተ በሰፊው ያብራራል።በአጠቃላይ ትምህርቱ ከሙዚቃ ውጪ ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር የሚሰጠው ጠቀሜታና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ዘርፈብዙ እና አሁናዊ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲይዙባቸው ሊያደርግ የሚያስችል የተለያዩ የመዝሙር አይነቶች ቀርበዋል።

## 5.1 መኖሪያ ቤትን፣ አካባቢን በሸክላ እና በሴራሚክ ስራዎች ማስዋብ

ተማሪዎች፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. በቤታችሁ እና በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች ቤታቸውን እና አካባቢያቸውን ሲያስዉቡ እና ሲያስጌጡ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ለማስዋብ እና ለማስጌጥ ምን ምን ነገሮችን በግብአትነት መልክ ይጠቀማሉ? እንዴትስ ተግባራዊ ያደርጋሉ?
3. የመኖሪያ ቤቶቻችን እና አካባቢዎቻችን ማስጌጣችን ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

መኖሪያ ቤቶችን እና አካባቢዎችን በልዩ ልዩ ዲዛይኖች ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ግብአቶችን በመጠቀም ማስዋብ (ማስጌጥ) ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአለም ላይ እና በሀገራችንም ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ሁኔታ ነው። የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ መኖሪያ ቤቱን ከዋሻ እና ከአለት አዘጋጅቶ ሲኖር በነበረበት ጊዜም የዋሻውን ውስጥ እና ዙሪያውን ለማሰዋብ፣ ለማስጌጥ፣ ምቹ እና አስደሳች ለማድረግ ስዕሎችን፣ ፁህፎችን፣ ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ያላቸው የመገልገያ ቁሳቁሶችን በማስቀመጥ፣ በመለጠፍ፣ በማንጠልጠል ኑሮው ምቹ እና አስደሳች እንዲሆን ለማድረግ በርካታ ጥረቶችን አድርጓል።

ከዚያም የቀጠለው የሰው ልጅ የሚኖርበትን ቤት እና አካባቢ የማስዋብ ሀሳብ እና ተግባር አሁንም ድረስ ቀጥሎ ዘመኑ ያፈራቸውን እና ሰልጣኔው የቸረውን በርካታ ግብአቶችን በመጠቀም የመኖሪያ ቤትን እና አካባቢን የማስዋብ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛል። ይህ ተግባር ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሰዎች እንዲሁ በዘልማድ ያገኙትን እውቀት በመጠቀም እና ሙያዊ በሆኑ እውቀቶች እና ክህሎቶች በመታገዝ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ዘርፍ ነው።

ለምሳሌ፡- ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች ልዩ ልዩ ሀይማኖታዊ እና ማህበራዊ በዓላቶች ሲደርሱ፣ ክረምት ሲገባ መኖሪያ ቤትን በተለይ ውስጡን እና ውጭውን ለማሳመር (ለማስዋብ) ከሚጠቀሙባቸው ነገሮች መካከል የቤቱን ውስጥ የተለያዩ አፈሮችን፣ የከብቶች ተዋፅኦ፣ አመድ የመሳሰሉትን ነገሮች እንደ ቀለም በማሰብ ቤታቸውን

ያስውባሉ። እንዲሁም የቤቱን ዙሪያዎች ደግሞ ከዋናው ግቢ በር ወይም ከመኖሪያ ቤቱ በር በመጀመር ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ ቤቶች የሚያደርሱ (የሚወስዱ)

ለምሳሌ፦ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ኩሽና(ጭስ) ቤት፣ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ መፀዳጃ ቤት፣ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ አትክልት ስፍራዎች፣ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ውጭ(ወደ ዋናው ) በር የሚያደርሱ መንገዶችን ልዩ ልዩ ይዘት እና መጠን ባላቸው ድንጋዮች፣ አፈር፣ አሸዋ፣ ጠጠር ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ነገሮች በመጠቀም የቤቱን ውጫዊ አካባቢዎች የማስዋብ እና የማሳመር ስራ ይሰራል። አሁን ባለንበት ዘመን ይህ የመኖሪያ ቤትን እና አካባቢውን የማስዋብ ስራ ሳይንሳዊ በሆነ እውቀት እና ክህሎት በመታገዝ በስነ ህንፃ እና የአትክልት እና የመዝናኛ ቦታዎች ዲዛይን ሙያ ታግዞ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።




ሥዕል 1 በመኖሪያ ቤት አካባቢ መንገዶችን፣ የአትክልት ስፍራዎችን የማስዋብ ዘዴ

እንደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች እና የስርዓተ ትምህርት ፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎች የቤቶችን ውስጣዊ የውበት ስራ እና የቤትን ውጫዊ አካባቢ ማስዋብ ጋርደኒንግ ስራዎች በቴክኒክ እና ሙያ እንዲሁም በኪነ ህንፃ የሙያ ዘርፍ ታግዘው ሰፊ የሆነ የሰው ሀይልን ወደ ስራው አለም እንዲካተት በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የገቢ ማስገኛ ዘርፎች በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።




ሥዕል 2 የመኖሪያ ቤትን ውስጣዊ ገፅታ በተለያዩ የሴራሚክ እና የዲዛይን ውጤቶች ማስዋብ

**የመኖሪያ ቤቶችን እና አካባቢዎችን በሴራሚክስ እና በሸክላ ውጤቶች ማስዋብ እና ማስጌጥ ያለው ጠቀሜታ**

- የምንኖርበትን ቤት እና አካባቢውን ለኑሮዋችን ምቹ እና አስደሳች ለማድረግ
- ለሚቀጥለው ትውልድ የተሻለ እሳቤና ተነሳሽነት ለመፍጠር
- በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ሰፊ የስራ እድል ይፈጥራል

## ተግባር

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ፣ በምትኖሩበት ቤት፣ በትምህርት ቤታችሁ አንድ ሳይት(ቦታ) በመምረጥ በቀላሉ በአካባቢ የሚገኙ ግብአቶችን በመጠቀም እንዴት ማስዋብ(ማስጌጥ) እንደሚቻል በአነስተኛ ቡድን እና በቡድን በመሆን ሰርታችሁ አሳዩ።
- በምትሰሩበት ጊዜ በክፍል ውስጥ በንድፈ ሀሳብ የተማራችሁትን ወደ ተግባር በመቀየር ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## 5.2 እይታዊ ጥበብ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለው ትስስር እና ጠቀሜታ

እይታዊ ጥበባት ስንል የሰው ልጅ ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ እይታውን፣ እውቀቱን፣ ማንነቱን ወ.ዘ.ተ ከሚገልፅባቸው እና ከሚያንፀባርቅባቸው በርካታ የስነ ጥበባት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። ስለሆነም የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ እይታዊ ጥበባትን በመጠቀም በጊዜው እና በወቅቱ የነበሩትን እና የሚያስባቸውን (ሀሳብ፣ ስሜት፣ ፈጠራ፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ ልምምድ፣ እይታ ወ.ዘ.ተ.) እንዲሁም በገሀዱ አለም ውስጥ ያሉትን እውነታዎች በተለየ መንገድ በማየት እና በማቅረብ ዘርፉን ሲያስተዋውቅ እና ሲጠቀምበት ቆይቷል እየተጠቀመበትም ይገኛል።

ይህ ዘርፍ በቀጥታም ይሁን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ከሌሎች በርካታ ዘርፎች፣ ሞያዎች፣ እውቀቶች ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት እና መስተጋብር አለው። ስለሆነም ይህንን መስተጋብራዊ ቁርኝት ሊያሳዩን እና ሊያሰረዱን ከሚችሉት መካከል የተወሰኑትን እንመልከት።

- ከሒሳብ
- ከማህበራዊ ሳይንስ
- ከቋንቋ
- ከቱሪዝም
- ከታሪክ
- ከሙዚቃ
- ከፊልም
- ከቴአትር
- ከተግባቦ(ትኮምኒኬሽን)
- ከአንትሮፖሎጅ
- ከማህበረሰባዊ ክዋኔዎች
- ከቴክኖሎጅ (ኢኖቬሽን)
- በትምህርት ዘርፍ ወ.ዘ.ተ.

## እይታዊ ጥበብ ከሒሳብ ጋር ያለው ዝምድና፦

- ስነ ጥበባዊ ፅንሰ ሀሳቦችን፣ ተግባራቶችን፣ ክንውኖችን ማወቃችን እንዲሁም መረዳታችን በሂሳብ ሙያ ውስጥ የሚተገበሩ መላ ምቶችን፣ ስሌቶችን፣ ቴረሞችን ወ.ዘ.ተ. የአዕምሮአዊ እድገት እና ብስለትን በመጠቀም የማሰብ እና የማሰላሰል አቅማችንን እንዲጎለብት ያደርጋል። በተጨማሪም የስኬል ህግን በመጠቀም(በመተግበር) ስዕሎችን፣ ፎቶ ግራፎችን የማሳደግ፣ የማሳነስ ተግባራቶችን እናከናውናልን እንዲሁም ጅኦሜትሪካዊ ቅርፆችን በመጠቀም በመገጣጠም ና በማገናኘት ልዩ ልዩ ዲዛይኖችን እና ምስሎችን እንፈጥራለን፣ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ይዘት ያላቸውን ነገሮች ውስብስብ ከሆነው ይዘት እና ገፅታ ወጥተን ስናያቸው፣ ስናጠናቸው የጅኦሜትሪካል ቅርፆች ድምር ውጤት ናቸው።
- ልዩ ልዩ ስነ ጥበባዊ ተግባራቶችን ስናከናውን ልኬትን እና መጠንን እንጠቀማለን።

## እይታዊ ጥበብ ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ያለው ዝምድና፦

- የአንድ ሀገር ታሪክ እና ማህበረሰባዊ ስሪት እንዲታይ እና እንዲገለፅ፣ እንዲነገር፣ እንዲተዋወቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ከምንጠቀምባቸው ነገሮች መካከል ቀለም ቅብ፣ ፎቶ ግራፍ፣ ኢሉስትሬሽን፣ ቅርፃ ቅርፅ ተጠቃሽ ናቸው።

## እይታዊ ጥበብ ከቴክኖሎጅ (ኢኖቬሽን) ጋር ያለው ዝምድና፦

- በዚህ ዘርፍ ውስጥ የሚታሰቡ እና ተግባራዊ የሚደረጉ አዳዲስ ሀሳቦችን፣ ፈጠራዎችን፣ እሳቤዎችን፣ ግኝቶችን ወ.ዘ.ተ ወደ ማህበረሰቡ ይዞ ለመቅረብ እና ለማስተዋቅ፣ ሳቢ ና ማራኪ(ውብ) የሆነ ገፅታ እና ይዘት እንዲኖራቸው ለማድረግ መሰረታዊ የስነ ጥበብ አለባዊያንን(ቀለም፣ መስመር፣ ፎርም፣ ቴክስቸር ወ.ዘ.ተ.) እና መሰረታዊ የስነ ጥበብ(መሰረታዊ የዲዛይን) ህግጋትን በመጠቀም የሚተገበሩ ናቸው። ተሰርተው ከተጠናቀቁም በኋላ አገልግሎት ከመስጠታቸው በፊት ለማህበረሰቡ የሚቀርቡበት የእግዚቢሽን እና የማስተዋወቅ ሂደት ስነ ጥበባዊ እሳቤን እና መርህን ተከትሎ ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

## እይታዊ ጥበብ ከማህበረሰባዊ ክዋኔዎች ጋር ያለው ዝምድና፡-

የስው ልጅ በእለት ከእለት እንቅስቃሴው እና በህይወት ዘመኑ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው እና የሚከውናቸው በርካታ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ትውፊታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ክውኖች እይታዊ ጥበባት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አላቸው። ለምሳሌ፡-

- በቤታችን ውስጥ የምንጠቀምባቸውን መገልገያ ቁሳቁሶች እና በቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ነገሮችን ለእይታ ደስ የሚል ስሜት እንዲፈጥርልን የማስተካከል፣ የማስዋብ፣ የማደራጀት፣ ዲዛይን የማድረግ ስራዎችን እንተገብራለን።
- የምንለብሳቸውን አልባሳት፣ የምንጫማቸውን ጫማዎች ወ.ዘ.ተ ለመግዛት እና ለመምረጥ ስንፈልግ እንደ መስፈርት ከምንወስዳቸው ነገሮች መካከል የቁሱ የዲዛይን ሁኔታ፣ ቀለሙ፣ መጠኑ፣ ፎርሙ፣ ቴክስቸሩ ወ.ዘ.ተ.
- ማህበረሰቡ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ፍቅሩን ወ.ዘ.ተ ለመግለፅ እና ለማሳየት በሚፈልግበት ጊዜ ለምሳሌ፡- እንደ አብዛኛው የሀገራችን ባህል ቅርብ ቤተሰብ(ዘመድ) በሞት ሲለየን ሀዘናችንን ለመግለፅ ጥቁር ቀለም ያላቸው ልብሶችን እንለብሳለን፣ የምርቃት፣ የሰርግ፣ ክዋኔዎችን ስናከብር ጥቁር ቀለም ያላቸውን ልብሶች እንጠቀማለን፣ ፍቅርን ለመግለፅ ቀይ ቀለም ያለው አበባ የመስጠት ባህል ተግባራዊ ይደረጋል።

## እይታዊ ጥበባት ከታሪክ ጋር ያለው ዝምድና

ታሪክ የአንድ ሀገር፣ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ማንነት ከሚገለፅባቸው እና ከሚተገበርባቸው ወሳኝ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ነው። ስለሆነም ታሪክን የሚገልፁ እና የሚያሳዩ ነገሮችን በቀለም ቅብ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በቅርፃ ቅርፅ፣ በኢሉስትሬሽን በመግለፅ ታሪኩን የማስረዳት እና የመግለፅ ሁኔታዎች ወ.ዘ.ተ ተግባራዊ ይደረጋሉ። የሰው ልጆችን ጥታዊ እሳቤ፣ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ስልጣኔ ወዘተ የመሳሰሉትን ሁኔታዎች የሚገልፁ እና የሚያሳዩ ልየ ልዩ መረጃዎችን በስዕል፣ በፎረቶግራፍ፣ በቅርፃቅርፅ፣ በኪነ ፅህፈት ተሰርተው እና ተደራጅተው ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ እና እንዲጠበቁ ያደርጋል።

## እይታዊ ጥበብ በመማር ማስተማር ትግበራ ሂደት ላይ ያለው ጠቀሜታ

የመማር ማስተማር ሂደት የራሱ በሆነ ሳይንሳዊ ትግበራ እና መርህ የሚከናወን ሲሆን ይሄንንም ሂደት ውጤታማ ለማድረግ እና ግቡን እንዲመታ ለማስቻል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስፈላጊና አጋዥ ከሆኑት ዘርፎች መካከል እይታዊ ጥበብ አንዱ ነው።

እይታዊ ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር በማቀናጀት በመማር ማስተማር ሂደቱ መተግበሩ በዋናት በሚከተሉት ሶስት መንገዶች ጠቀሜታው የጎላ ነው።

- ለትምህርት ተቋማት
- ለመምህራን

  ተግባር ተኮር፣ አይረሴ፣ አሳታፊ እና ተጨባጭ የሆነ ትምህርት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል

- ንድፈ ሀሳባዊ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችን ሊታዩ፣ ሊዳሰሱ፣ ሊደመጡ በሚችሉ የማስተማሪያ ክንውን ለተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል
- ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ከሚያስተምሯቸው ይዘት፣ የክፍል ደረጃ፣ የተማሪዎች እድሜ፣ የመረዳት አቅም ጋር ተያያዥ የሆኑ መርጃ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት (ለመስራት) ያስችላል
- ተለምዶአዊ ከሆነው የመማር ማስተማር ትግበራ በመውጣት አዳዲስ የሆኑ የማስተማር ክዋኔዎችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያስችላል
- ለተማሪዎች

## እይታዊ ጥበብ ከትምህርት ተቋማት ያለው ዝምድና

እይታዊ ጥበባት ለትምህርት ተቋማት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ድርሻ ያለው እና በዋጋ ሊተመን የማይችል ነው። የትምህርት መስጫ ተቋማትን ልዩ ልዩ ይዘት፣ መጠን ባላቸው የእይታዊ ጥበብ ዘርፎች አማካኝነት ማለትም ትምህርት አዘል፣ ትምህርት ሰጭ የሆኑ ፁፎች፣ ሀውልቶች፣ የግድግዳ ስዕሎች(ቀለም ቅቦች) ማሳመር፣ ማስጌጥ ከቻልን በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።

- ሳቢና ማራኪ የሆነ ገፅታ እንዲላበሱ ያስችላል
- በደንበኞች ተመራጭ፣ ተመስጋኝ እንዲሆኑ ያስችላል

- ✍ ተማሪዎች አብዝሀኛውን ጊዜያቸውን በትምህርት ቤቱ ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ ያስችላል
- ✍ የተማሪዎቹን የመቅረት፣ የማቋረጥ ምጣኔ ለመቀነስ ያስችላል

## እይታዊ ጥበባት ለተማሪዎች ያለው ጠቀሜታ

- ➢የሚማሯቸውን ትምህርቶች በብዙ የተግባር፤ የክንውን አማራጮች እንዲማሩ ያግዛል
- ➢የተማሪዎችን የስሜት ህዋሳትን በማነቃቃት፤ በማቀናጀት ነገሮችን የሚረዱበትን እና የሚገነዘቡበትን አቅም በማሳደግ ጥልቅ የሆነ ምዕናባዊ፤ እይታዊ እሳቤ እንዲኖራቸው ያግዛል።
- ➢የሚማሯቸውን ትምህርቶች ተግባር ተኮር፣ አይረሴ፣ ተጨባጭ፣ አሳታፊ እንዲሆን ያስችላል
- ➢በመተባበር፣ በመተጋገዝ የመማር፣ የመስራት አቅምን ያሳድጋል
- ➢ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም፣ ሀላፊነትን መወጣት፣ ለነገሮች ትኩረት የመስጠት አቅምን ያሳድጋል
- ➢ምዕናባዊ(ንድፈ ሀሳባዊ) የሆኑ ነገሮችን ሊታዩ እና ሊዳሰሱ ወደ ሚችሉ ነገሮች የመቀየር አቅምን ያሳድጋል
- ➢ውስብስብ እና አድካሚ የሆኑ ነገሮችን ቀለል ባለ እና ሳቢ በሆነ መንገድ የማቅረብ እና የመስራት አቅምን ያሳድጋል

## 5.3 የሙዚቃ ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና

1. ክውን ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና በምሳሌ በማስደገፍ ሀሳባችሁን ተናገሩ?
2. ክውን ጥበባት ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር ፋይዳው ምንድን ነው?

የክውን ጥበባት በተለይም ሙዚቃ ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ማለትም ከቋንቋ፣ ሒሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ፣ ህብረተሰብ ሳይንስ እና ሌሎችም ትምህርቶች ጋር በተለያየ መልኩ በሚጋሯቸው ይዘቶች ግንኙነት ይኖራቸዋል። ትምህርቱ ራሱንችሎ በተለያዩ የትምህርት ደረጃ የሚሰጥ ቢሆንም ከላይ ከተጠቀሱት የትምህርት ዘርፎች ጋር ከፍተኛ ዝምድና ያለውና ለሌሎች ትምህርቶች ለማስተማር ድጋፍ ያደርጋል። በዚህም መሰረት ሙዚቃ በባህሪው ክውን ጥበብ


ሲሆን ይህም ሲባል የሰውን ልጅ ስሜት እና ሀሳብን በሙዚቃ አማካኝነት በመግለፅ ሰዎችን ለማዝናናት እንጠቀምበታለን። በሌላ በኩል ደግሞ ሙዚቃ ሳይንስ ነው ሲባል በውስጡ የያዘውን ሳይንሳዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ለምሳሌ የድምጽ፣ ስልተምት እና የስነ-ባህሪይ ወይም ስነ-ልቦና ከተመለከትንም በርግጥም ሙዚቃ ሳይንስ ሁኖ እናገኘዋለን።

ከዚህ በመቀጠል ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ግንኙነት እንመለከታለን

1. ሙዚቃ እና ፊዚክስ ትምህርቶች የሚያዛምዳቸው የድምጽ መውጣት እና መውረድ (ፒች) እንዲሁም የድምጽ እርግብግቦሽ መጠን ለመለካት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መጠቀሙ ነው::ለ ምሳሌ የተለያዩ የክርና ሌሎችም የሙዚቃ መሳሪያዎች የድምጽ ውፍረትና ቅጥነት ለመቃኘት(ለማግኘት) እየተጠቀሙበት ይገኛል::







ሥዕል 3 የሙዚቃ ድምፆች እንቅስቃሴ ወደ አድማጭ የሚደርሰበትን ሁኔታ የሚያሳይ

2. በሙዚቃ ትግበራ ወቅት ድምፆች የሚፈጥሩት ውብ ዜማ በጊዜ በተለኩ ምታዊ እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ነው:: ይህ የምት እንቅስቃሴ የስበት ህግን የተከተለ በመሆኑ ከፊዚክስ ሳይንሳዊ ሃሳብ ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል:: ይህንን ተመሳስሎት በሙዚቃ ስራ ላይ ምትን ለመግለፅ የሚረዳውን የሜትሮንየም እንቅስቃሴ መመልከት ይቻላል::





ሥዕል 4 ምታዊ የሙዚቃ እንቅስቃሴን የሚያሳይ


3. ሙዚቃ ከኬሚስትሪ ትምህርት ጋር የሚያገናኘው የሙዚቃ መሳሪያ ለማዘጋጀት የምንጠቀምበት ጥሬ እቃዎች /ማቴሪያል/ ሲሆን እነዚህ ጥሬ እቃዎች የሙዚቃ መሳሪያው ከሚያወጣው ድምጽ ጋር ግንኙነት አላቸው:: ለምሳሌ፦ የኮፐር፣ የዚንክ፣ ነሀስ፣ ከእንጨት እና ከቆዳ እንዲሁም ከብረት የተሰሩ የሙዚቃ መሳሪያዎች የተለያየ ድምጽ እንዲያወጡ ምክንያት ነው::

4. ከሒሳብ ትምህርት ጋር የሙዚቃ ስኬል እና የህብረት ድምጽ፤ ኖታን የማርባት ዘዴን እንዲሁም የሙዚቃ የጊዜን ቆይታን መሰረት ያደረገ ክዋኔን ለማመልከት የሚከተለውን መግለጫ ማየት ይቻላል::

 2 ምት እና 1ምት በአጠቃላይ 3ምት

 4 ምት እና 2 ምት በአጠቃላይ 6 ምት

 1ምት እና ½ ምት በአጠቃላይ 1 ½ ምት





ሥዕል 5 የኖታዎችን ሂሳባዊ ብዜት/አረባብ/ የሚያሳይ

5. ሙዚቃ የሰውን ልጅ የአዕምሮ ደህንነት ከማስጠበቅ እና ስነ ልቦናዊ ህመሞችን ከማከም አንፃር ሚናው የጎላ ነው:: በተለያዩ ባደጉ ሀገሮች የሙዚቃ ህክምና ተቋማት የተበራከቱ ሲሆን የማህበራዊ እና ግለሰባዊ አዕምሯዊ ደህንነቶችን በዜማዊ ባህሪያት ማከም እየተቻለ ነው:: ይህ በሙዚቃ ሰዎችን የማከም ሂደት ሙዚክ ቴራፒ ይባላል::



ሥዕል 6 ሙዚቃ የአእምሮ ደህንነትን ሲያስጠብቅ የሚያሳይ

6. ከስነ-ጥበብ ትምህርት ጋር የተለያዩ የሙዚቃ ኖታዎች፣ የእረፍት ምልክቶች እና የተለያዩ የሙዚቃ ምልክቶችን ለማስቀመጥ የተለያዩ የመስመር አይነቶችን በመጠቀም ነው:: ለምሳሌ፡-




## 5.3.1 ሙዚቃ ትምህርት ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር የሚያደርገው እገዛ

በመማር ማስተማር ሂደት ሙዚቃ ትምህርት እንደሌሎቹ የትምህርት አይነት ራሱንችሎ በተለያየ የትምህርት ይዘት የሚሰጥ ቢሆንም ሙዚቃ ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር የራሱ እገዛ ያደርጋል። ለምሳሌም ያህል

1. ቋንቋ ትምህርቶችን ለማስተማርና የአማርኛና እንግለዘኛን ሆሂያትን በተለያዩ መዝሙሮች ለማስተማር




2. ሒሳብ ትምህርት ውስጥ አራቱን የሒሳብ ስሌት ባህሪያት(መደመር፣ መቀነስ፣ ማካፈልና ማባዛት) በተመለከተ በመዝሙር ለማስተማር




3. ከአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ጋር በተለይ የንጽህና አጠባበቅ፣ አካባቢን ማወቅ፣ የቤተሰብ አባላትን መገንዘብ፣ የስሜት ህዋሳትን ለመረዳት ወዘተ በሙዝሙር በቀላሉ ለማስጨበጥ ያስችላል።

4. ሙዚቃ የፊልም እና የቴአትር ጥበባትን በመስራት ሂደት ውስጥ ቴአትሩን ወይም ፊልሙን ለማድመቅ የሚረዳ ከመሆኑም ባሻገር ሙዚቃዊ ቴአትር ራሱን ችሎ የሚቀርብበት በመሆኑ ጥብቅ ትስስር አላቸው።

## 5.4 ትኩረት የሚሹ እና ወቅታዊ ጉዳዮች

በኢትዮጵያ እንዲሁም በክልላችን ነባራዊ ሁኔታ የተለያዩ ትኩረት የሚሹ እና ወቅታዊ ጉዳዮች በማህበረሰቡ ውስጥ ይከሰታሉ። በመሆኑም እነዚህ ችግሮች በማህበረሰቡ የእለት ከዕለት እንቅስቃሴ እና ኑሮው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣሉ። ስለዚህ እነዚህን ጉዳዮች ማህበረሰቡ ሊረዳው እና ሊገነዘበው በሚችል መልኩ ማስገንዘብ፣ ማሳወቅ፣ ማስተማር ከሚመለከተው አካል እና ከዘርፉ ባለሞያዎች ይጠበቃል። ስለሆነም እነዚህ ወቅታዊ እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ከምንፈጥርባቸው፣ ከምናሳውቅባቸው በርካታ ዘርፎች መካከል እይታዊ ጥበባት፣ ክውናዊ ጥበባት ወ.ዘ.ተ ተጠቃሽ ናቸው። በሀገር አቀፍ እና በክልላችን ደረጃ ትኩረት የሚሹ እና ወቅታዊ ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑንም ዋና ዋናዎቹን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

- የከባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ
- የትራፊክ አደጋ
- ግብር መክፈል
- የህፃናት ህገወጥ ዝውውር እና ጉልበት ብዝበዛ
- ሰላም
- የአደንዛዥ እፅ እና ሱስ አምጭ ነገሮች
- ኤች አይ ቪ ኤድስ ወ.ዘ.ተ

### ተግባር

1. ከዚህ በታች በመዝሙር፣ በስዕል መልክ የቀረቡትን ወቅታዊ ጉዳዮች መዝሙሮቹን ከዘመራችሁ፣ ስዕሎቹንም ከተመለከታችሁ በኋላ የተረዳችሁትን እና የተገነዘባችሁትን ሀሳብ በግል ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
2. ተማሪዎች ከላይ በቀረቡት ወቅታዊ እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ወይም የራሳችሁን ርዕስ በመምረጥ እና በመዘጋጀት በክፍል ውስጥ በቡድን በቡድን ሆናችሁ ጥሩ እና ሞቅ ያለ ውይይት እና ክርክር አድርጉ? ውይይታችሁም በመዝሙር፣ በስዕል፣ በፎቶ ግራፍ፣ በድራማ፣ በቴያትር መልክ እንዲሆን ከመምህራችሁ ጋር በመሆን መነጋገር፣ ማቀድ፣ መዘጋጀት ወ.ዘ.ተ ይጠበቅባችኋል።

## የትራፊክ መብራት

የትራፊክ መብራት ሲያበራ ቀዩን
መኪና ይቆማል ጠብቆ ሕጉን
በመንገድ ላይ ስትሄዱ ግራ ተይዞ ነው
የትራፊክ መብራት ሲበራ አረንጓዴው
መኪና በፍጥነት ይሄዳል በጎዳናው
መንገዱ ይዘጋል ይቆማል እግረኛው::
አዝማች X 2
እባካችሁ ሰዎች ህጉን ተገንዘቡ
ስለ መንገድ ጉዳይ ሁል ጊዜ አስቡ
በጊዜ ተጠቅሞ ይሻላል ማቀድ
በጠባብ መንገድ ላይ አስተውሎ መሄድ::







ሥዕል 7 የትራፊክ ደህንነት ህግ አጠቃቀም

# የትራፊክ መብራት


ሙዚቃ:- አለማየሁ ወ/ዮሃንስ
ግጥም:- ሰለሞን ገላው




## ዕፅዋት

ለሰው ልጅ ዋስትና አረንጓዴ ዕፅዋት
እንደሆኑ እንወቅ ለኛም ለህፃናት
በትምህርት ቤታችን ደግሞም በግቢያችን
ዕፅዋትን ማልማት ይሁን ተግባራችን
ምንጮች እንዳይደርቁ ደኖች እንዳያልቁ
የዱር እንስሳት እንዳይሰደዱ
የኛም ኃላፊነት መኖሩን ተረዱ
በለጋው ዕድሜያችን እኛ የምንወደው
መስክ ላይ መሯሯጥ ውሃ መራጨት ነው

## ዕፅዋት




ለ- ኛም ለ- ህ- ፃ- ናት በ- ትምህ- ርት ቤ- ታ-
ችን ደግ- ሞም በ ግ- ቢያ ችን
ዕ- ፅ- ዋ - ትን ማል- ማት ይ- ሁን ተግ- ባ- ሬ
ችን ምን - ጩች እን-ዳይ:ደር -ቁ ደ - ኖች እን-ዳ- ያ


-ልቁ የ- ዱር እንስ - ሳ - ትም እን- ደ - ይ - ሰ - ደ
-ዱ የ- ኛም ኃ-ላ - ፊ -ነት ሙ- ሆ- ኦን ተ-ረ - ዱ
በ - ለ - ጋው እድ - ሜ ችን እ- ኛ - የ - ምን - ው
-ደው መስ - ክ ላይ ሙ- ሯ- ሯት ው- ሃ ሙ- ራ - ጩት- ነው



ሥዕል 8 የአየር ንብረት ለውጥ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ የሚያሳይ

| ተ.ቁ | የምዕራፉ ይዘቶች | አሳክቻለሁ /አውቂያለሁ/ | አላሳካሁም /አላወኩም/ |
| --- | --- | --- | --- |
| 1. | መኖሪያ ቤቶችን እና አካባቢዎችን በሸክላ፣ በሴራሚክ ውጤቶች የማስዋብ ምንነትን፣ የአተገባበር ሂደቱን፣ ቴክኒኩን | | |
| 2. | እይታዊ ጥበባት ከሌሎች ዘርፎች፣ ሞያዎች ጋር ያላቸውን ዝምድና፣ ጠቀሜታ፣ በመማር ማስተማር ሂደት ያላቸውን ጥቅም | | |
| 3. | ውቅታዊ እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ምንነት፣ ክፍሎች፣ ጠቀሜታ | | |

## የማጠቃለያ መልመጃዎች

**ትዕዛዝ አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ሀሰት በማለት መልስ ስጡ**

1. የመኖሪያ ቤቶችን እና አካባቢያችን ለማስዋብ እና ለማስጌጥ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች ያላቸው ሚና ዝቅተኛ ነው
2. ሙዚቃ ትምህርት ከሒሳብ ትምህርት ጋር በኖታ አረባብ ዘዴ ግንኙነት አለው
3. ትኩረት የሚሹ እና ወቅታዊ ጉዳዮችን እይታዊ እና ክውን ጥበባትን በመጠቀም ማህበረሰቡን ማስተማር እና ማሳወቅ ይቻላል

**ትዕዛዝ ሁለት፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ አጭር እና ግልፅ መልስ ስጡ**

1. የእይታዊ ጥበባት የሌሎች ትምህርቶችን የማስተማር ሂደት በምን በምን መንገድ ሊደግፉ (ሊያጠናክሩ) እንደሚችሉ ተናገሩ?
2. ሙዚቃ ትምህርት ከፊዚክስ ትምህርት ጋር እንዴት ሊገናኝ እንደሚችል በዝርዝር ፃፉ?
3. ትኩረት የሚሹ እና ወቅታዊ ጉዳዮች የምንላቸው ምን ምን ይባላሉ? ለምን ወቅታዊ እና ትኩረትን የሚሹ ተባሉ?

# ዋቢዎች


1. ተስፋየ ለማ። (ግንቦት 2005 ዓ.ም)። የኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ከ 1889 እስከ 1983 ዓ.ም ሻማ ማተሚያ ዋሽንግተን ዲሲ፣ አሜሪካ
2. ስለሞን ተሾመ። (2007ዓ.ም)። የፎክሎር ምንነት እና ትርጉም። ሻማ ማተሚያ ድርጅት
3. በሚካኤል ልዑል ሰገድ።(2006 ዓ.ም)። የፊልም ፁህፍ አፃፃፍ። ብርሀን እና ሰላም
4. ማስተዋል ጌታ። (2009)። ስነ ጥበብን የማስተማር ስነ ዘዴ (TeAr -322)
5. ዲ/ን ሰሎሞን ወንድሙ፣ ቀሲስ ዘ ወንጌል ገብረ ኪዳን፣ ዲ/ን ዝናየ ሀይለ ማርያም። (2013 ዓ.ም) ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ 1። ማህበረ ቅዱሳን
6. ታደስ አለማዩ (2011 ዓ.ም)። የቤተ ክርስቲያን ብርሀን ቅዱስ ያሬድ። ማህበረ ቅዱሳን
7. ጫን ያለው ወልደ ጊየርጊስ። አስታጥቃቸው ይሁን። አለማየሁ ታደሰ። እቴነሽ ካሳው። ተስፋየ ገብረ ማርያም (2001 ዓ.ም)መሰረታዊ የተውኔት አፃፃፍ መርሆች። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር
8. ፍሬህይወትዘውዴ፣ ጥበቡ ወርቅአገኘሁ፣ አበበ መንግስቴ፣ ይገለጡ መብራቴ፣ አሸናፊ ታደሰ። (ባህርዳር 1987 ዓ.ም) ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ እርከን ለመምህርነት ስልጠና የተዘጋጀ የሙዚቃ መማሪያ ማስተማሪያ ፁህፍ። አ.ብ.ክ ትምህርት ቢሮ
9. ኤልያስ ጋሻው ማንኩልህ (ትርጉም)። (2007 ዓ.ም) ስኬታማ የፊልም አሰራር ከህግጋት በሻገር።ነጭ ሳር ማተሚያ ድርጅት
10. Ethiopian History of Art GCTE 199/2006
11. Glmstone Bryan(1997 G.C) Crafts and Design buefs Wood and Related Material (Macmillan/McGraw-Hill )
12. Michele Daz(2000) Children and their Art(SWMLAC and the DfES 1997)
13. Mittler Ragans…GLENCOE(2006 G.C)Understanding Art Macmillan/McGraw-Hill